**DSpace Institution**

**DSpace Repository** | **http://dspace.org**

Folklore/Cultural Studies | Thesis and Dissertations

2015-02

# þÿ " p ¨ s s í • u “ Í % ` f s 5 ë Î } í ` ð 4 ¨

þÿ ë u H • s •

http://ir.bdu.edu.et/handle/123456789/15233

*Downloaded from DSpace Repository, DSpace Institution's institutional repository*

ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ

ሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ

የፎክሎር (ባህል ጥናት) ትምህርት ክፍል

ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር


# "ተከታታይነትና ለውጥ በቦታ ስያሜዎች ላይ በደሴ ከተማ ተተኳሪነት"


በ

ሀያት ፈንታሁን ይመር


በፎክሎር ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት


መጋቢት፤2015 ዓ.ም

ባህር ዳር፣ ኢትዮጵያ

"ተከታታይነትና ለውጥ በቦታ ስያሜዎች ላይ በደሴ ከተማ ተተኳሪነት"


ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ

የፎክሎር (ባህል ጥናት) ትምህርት ክፍል


ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር


በ

ሀያት ፈንታሁን ይመር

አማካሪዎች

ሞላ ጀምበሬ (ዶ/ር)

ረ/አማካሪ፡- አብዩ አስማማዉ(ዶ/ር)


በፎክሎር ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት


መጋቢት፤2015 ዓ.ም

ባህር ዳር፣ ኢትዮጵያ

# ማረጋገጫ

ተከታታይነትና ለውጥ በቦታ ስያሜዎች ላይ በደሴ ከተማ ተተኳሪነት በሚል ርዕስ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ በፎክሎር (ባህል ጥናት) ትምህርት ክፍል በድህረ ምረቃ መርሃ ግብር ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረብኩት ይህ ጥናት የራሴ ስራ መሆኑን በፊርማየ አረጋግጣለሁ፡፡

ሀያት ፈንታሁን ይመር ፊርማ፡ ..............................

ቀን፡ ..............................

ይህ ጥናት ለፈተና የቀረበው እኔ እንደ ተቋም ተቆጣጣሪ ሆኜ በማፅደቁ ነው፡፡

የአማካሪዎች ስም፡- ሞላ ጀምበሬ (ዶ/ር) ፊርማ፡ ..............................

ቀን፡ ..............................

አብዩ አስማማዉ(ዶ/ር) ፊርማ፡ ..............................

ቀን፡ ..............................

**ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ**

**ሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ**

**የፎክሎር (ባህል ጥናት) ትምህርት ክፍል**

**ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር**

**የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ**

"ተከታታይነትና ለውጥ በቦታ ስያሜዎች ላይ በደሴ ከተማ ተተኳሪነት" በሚል ርእስ፣ በፎክሎር ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ በሀያት ፈንታሁን ይመር" የቀረበው ይህ ጥናት፣ የዩኒቨርሲቲውን የጥራትና የወጥነት መስፈርት ስለማሟላቱ በፈታኞች ተረጋግጦ ተፈርሟል፡፡

የአማካሪዎች ስም፡- ሞላ ጀምበሬ (ዶ/ር) ፊርማ ..................................

ቀን፡- ..................................

ረ/አማካሪ፡- አብዩ አስማማዉ (ዶ/ር) ፊርማ ..................................

ቀን፡- ..................................

የውስጥ ፈታኝ ስም፡- አስቴር ሙሉ (ዶ/ር) ፊርማ ..................................

ቀን፡- ..................................

የውጭ ፈታኝ ስም፡- ብርሃኑ አሰፋ(ዶ/ር) ፊርማ ..................................

ቀን፡- ..................................

# ምስጋና

በመጀመሪያ የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር ለሁለተኛ ዲግሪ እንድማር ያመቻቹልኝን የደሴ ከተማን አስተዳደር እና የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲን ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

በመስክ ቆይታየ መረጃ በምሰበስብበት ወቅት ለማነሳቸዉ ጥያቅዎች በሙሉ ቅንነት መልስ በመስጠት እና ሌሎች መረጃ ሰጭዎችን አድራሻ በመጠቆም ለተባበሩኝ ለደሴ ከተማ እና አካባቢዋ ነዋሪዎች፣ ለደሴ ከተማ መንግስት ኮሚኒኬሽን ቢሮ፣ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ሰራተኞች፣ መረጃ በምሰበስብበት ወቅት የመረጃ ሰጭዎቼን አድራሻ በማሳወቅና አብሮኝ በመሆን ከጎኔ ለነበሩት የሰኞ ገበያ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ለአቶ መኮንን አስፋው እና ለሰኞ ገበያ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ሰራተኞች በሙሉ ምስጋናየ ይድረስልኝ፡፡

በመቀጠልም ይህ ጥናት የተሳካ እንዲሆን ከርዕስ ማስተካከል ጀምሮ ተገቢ የሆነ እርማትና ገንቢ አስተያየታቸዉን በመለገስ፣ የተለያዩ ማቴሪያሎችን በመስጠት እንዲሁም በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ሆነዉ ከጎኔ ላልተለዩኝ አማካሪየ ለሞላ ጀምበሬ (ዶ.ር) ልባዊ ምስጋናየን አቀርባለሁ፡፡

የተለያዩ ማቴሪያሎችን በኢሜል በመላክ ጥናቴ የተሳካ እንዲሆን ሀሳብ እና ሞራል በመስጠት ድጋፍ ያደረጉልኝ ሁለተኛ አማካሪየ ለአብዩ አስማማዉ (ዶ.ር) ምስጋናየ ይድረስልኝ፡፡

የመረጃ ሰጭዎችን አድራሻ በማፈላልግበት ወቅት አብሮኝ በመሆን እንዲሁም የመረጃ ሰጭዎቼን መኖሪያ ቤት ወይም አድራሻ በማሳየት ለተባበረኝ አቶ አህመድ እብራሂም ምስጋናየ ይድረስልኝ፡፡

ትምህርቴን እንድቀጥል የነበረብኝን የመንግስት እዳ (የወጭ መጋራት) ክፍያ በመክፈል፣ ላፕቶፕ እና የተለያዩ ቁሳቁሶችን በመግዛት ሞራል የሆነኝ ዉዱ አባቴ ፈንታሁን ይመር ምስጋና ይገባሃል፡፡ ፈጣሪ ረጅም እድሜ ይስጥልኝ፡፡ የተለያዩ ድጋፎችን በማድረግ የጥናቴ መጨረሻ ድረስ ከጎኔ ለነበሩት ለአጎቴ ሰይድ ይመር፣ ለእናቴ ለወ.ሮ ዘነበች ታፈሰ፣ ለዉድ ባለቤቴ ኑሩ ጀማል፣ ለእህቶቼና ወንድሞቼ፣ ለተስሊም ሠይድ፣ለአቶ ሰይፈዲን መሀመድ፣ለአቶ ኤፍሬም አሊ እንዲሁም ለይመር ሚህሙድ እና ለጥሩየ አሊ የልጅ ልጆች ቤተሰብ ማህበር ልባዊ ምስጋናየ ይድረስልኝ፡፡

# አጠቃሎ


*የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በደሴ ከተማ የሚገኙ የቦታ ስሞችን ተከታታይነትና ለውጥ መመርመር ሆኖ ተከታታይነትን ጠብቀው የሚገኙ ቦታዎችን ስያሜዎች መፈተሽ፤ የቦታ ስሞች ለውጥና የለውጥ ምክንያቶችን መለየት፤ የቦታ ስሞችን ፋይዳ መለየት፤ የቦታ ስሞቹ ተከታታይነትና ለውጥ ላይ ማህበረሰቡ ያለውን አመለካከት መፈተሽ የሚሉ ዝርዝር ዓላማዎችን አካትቷል። ጥናቱን ከግብ ለማድረስ የተለያዩ መረጃዎች ከመስክ እና ከተለያዩ ሰነዶች ተሰብስበዋል። ጥቅም ላይ የዋሉት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችም፤ ቃለመጠይቅ፣ ሰነድ ፍተሻ፣ ምልከታ እና ቡድን ተኮር ዉይይት ናቸዉ። ጠቋሚ ናሙናን በመጠቀም ለጥናቱ በመረጃ አቀባይነት የተሳተፉ 21 መረጃ አቀባዮች ተመርጠዋል። ለጥናቱ በተመረጠዉ ደሴ ከተማ የሚገኙ የቦታ ስያሜዎችን ሁሉንም በመዉሰድ ከእነዛ ዉስጥ በእጣ ንሙና የተመረጡት የቦታ ስሞች ለትንተና ቀርበዋል። የተሰበሰቡት መረጃዎችም በተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ እና በስነፍቻዊ ንድፈ ሀሳብ መሰረት ተተንትነዉ በገላጭ እና አይነታዊ የትንተና ዘዴ ተብራርተዉ ቀርበዋል። ከመረጃ ትንተናዉም የቦታ ስያሜ መነሻ ምክኒያቶች እና የቦታ ስያሜ የለውጥ ምክንያቶች የማህበረሰቡ ገጠመኝ፣ የሀይማኖት ተቋማት መስፋፋት፣ ፖለቲካዊ ሁኔታ፣ የመሰረተ ልማት መስፋፋት፣ የንግድ እንቅስቃሴ ወዘተ ሲሆኑ የለውጡ ሰበቦች ደግሞ የፖለቲካዊ ሥርዓት ለውጥ፣ የአካባቢው ማህበረሰብ ስነልቡናዊ ሁኔታዎች መሆናቸውን መለየት ተችሏል፤ በተለወጡ የቦታ ስሞች ላይም የማህበረሰቡ አመለካከት አወንታዊ ስለመሆኑ በመረጃ ትንተና በተገኘው ውጤት ተረጋግጧል። በአንጻሩ ብዙዎቹ የቦታ ስሞች ተከታታይነትን ጠብቀው ለመዝለቃቸው ምክንያቶቹ በማህበረሰቡ ማህበራዊ ህይወት፣ ማንነትና ስነልቡና ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚያሳድር ትርጓሜና አንድምታ የሌላቸው ከመሆኑ ጋር ሊያያዙ እንደሚችሉ መረጃዎች አመላክተዋል።*

# ማዉጫ


ምስጋና ............ I

አጠቃሎ ............ II

ማዉጫ ............ III

የስዕላዊ መግለጫዎች ማውጫ ............ VI

የአባሪዎች ማውጫ ............ VII

ምዕራፍ አንድ፡- መግቢያ ............ 1

1.1 የጥናቱ ዳራ ............ 1

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ............ 4

1.3. የጥናቱ አላማ ............ 5

1.4. ጥናቱ የመለሳቸዉ ቁልፍ ጥያቄዎች ............ 5

1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ ............ 5

1.6. የጥናቱ ወሰን ............ 6

1.7. የጥናቱ ስነምግባር ............ 7

ምዕራፍ ሁለት፡- ክለሳ ድርሳናት ............ 8

2.1. የፅንሰ ሀሳብ ዳሰሳ (Conceptual Fram works) ............ 8

2.1.1. የስያሜ ምንነት ............ 8

2.1.2. የስያሜ አጀማመር ............ 8

2.1.3. የቦታ ስያሜ ምንነት ............ 9

2.1.4. የቦታ ስያሜ መነሻ ምክኒያቶች ............ 10

2.1.5. የቦታ ስያሜ ፋይዳ ............ 10

2.1.5.1. ማህበረ ባህላዊ ፋይዳ ............ 10

2.1.5.2. ታሪካዊ ፋይዳ ............ 11

2.1.5.3. ፖለቲካዊ ፋይዳ ............ 11

2.1.5.4. ትዕምርታዊ ፋይዳ ........ 12

2.1.6. ተከታታይነት ........ 12

2.1.7. ለውጥ ........ 13

2.2. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ........ 13

2.2.1. ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የቀረቡ ጥናቶች ........ 13

2.2.2. ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረቡ ጥናቶች ዳሰሳ ........ 16

2.3. ንድፈ ሀሳዊ ማዕቀፍ (Theoretical Fram works) ........ 19

2.3.1. ጠቀሜታዊነት ንድፈ ሀሳብ ........ 19

2.3.2. ስነ ፍቻዊ ንድፈ ሀሳብ ........ 20

ምዕራፍ ሶስት፡- የአጠናን ዘዴ ........ 22

3.1. የምርምሩ አይነትና የጥናት ንድፍ (Research Type & Design) ........ 22

3.2. ተጠኝዎች ........ 22

3.3. የናሙና አመራረጥ ዘዴ ........ 23

3.4. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ........ 24

3.4.1. ቃለ መጠይቅ ........ 24

3.4.2. መዛግብት (ሰነድ) ፍተሻ ........ 25

3.4.3. ቡድን ተኮር ዉይይት ........ 25

3.4.4. ምልከታ ........ 26

3.5. የመረጃ አተናን ዘዴ ........ 27

3.6. የመስክ ተሞክሮ ........ 27

3.7. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች ........ 30

3.7.1. ያጋጠሙ ችግሮች ........ 30

3.7.2. የተወሰዱ መፍትሄዎች ........ 30

ምዕራፍ አራት፡- የደሴ ከተማ አካባቢያዊ ዳራ ........ 32

4.1. የደሴ ከተማ መልክዓምድራዊ አቀማመጥ ........ 32

4.2. የደሴ ከተማ አመሰራረት ........ 33

4.3. የኢኮኖሚና የመሰረተ ልማት ሁኔታ ........ 34

4.4. የቱሪዝም እና ባህላዊ እሴቶች ሁኔታ ........ 34

ምዕራፍ አምስት፡- የመረጃ አቅርቦት እና ትንተና ........ 36

5.1. የቦታ ስሞችን ተከታታይነትና የተከታታይነት ምክንያቶች የሚመለከቱ መረጃዎች ትንተና፤ ........ 37

5.2. የቦታ ስሞች ለዉጥና የለዉጥ ምክኒያቶቻቸዉን የሚመለከት መረጃዎች ትንተና ........ 54

5.3. በቦታ ስሞች ዙሪያ የማኅበረሰቡን አመለካከት የሚያሳዩ መረጃዎች ትንተና ........ 61

5.3.1. በቦታ ስሞች ተከታታይነት ላይ የማህበረሰቡ አመለካከት ........ 61

5.3.1.1. አዎንታዊ አመለካከት ........ 61

5.3.1.2. አሉታዊ አመለካከት ........ 63

5.3.2. በቦታ ስሞች ለውጥ ላይ የማህበረሰቡ አመለካከት ........ 64

5.3.2.1. አዎንታዊ አመለካከት ........ 64

5.3.2.2. አሉታዊ አመለካከት ........ 66

ምዕራፍ ስድስት፡-ማጠቃለያ እና የይሁንታ ሀሳብ ........ 67

6.1. ማጠቃለያ ........ 67

6.2. የይሁንታ ሀሳቦች ........ 69

ዋቢ ፅሁፎች ........ 70

አባሪዎች ........ 74

# የስዕላዊ መግለጫዎች ማውጫ

ፎቶ አንድ፡ የደሴ ከተማ ካርታ ........................................................................ 32

# የአባሪዎች ማውጫ

አባሪ አንድ፡ ለቁልፍ መረጃ አቀባዮች የቀረበ ጥያቄ ........................................ 74

አባሪ ሁለት፡ የመረጃ አቀባዮች ስም ዝርዝር ................................................ 74

አባሪ ሶስት፡ ተከታታይነታቸዉን ጠብቀዉ የሚገኙ የቦታ ስሞች ......................... 77

አባሪ አራት፡ የተለወጡ የቦታ ስሞች ............................................................ 79

# ምዕራፍ አንድ፡- መግቢያ

ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ በስድስት ምዕራፍ የተዋቀረ ሲሆን በምዕራፍ አንድ መግቢያ፣ የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ አላማ፣ ጥናቱ የሚመልሳቸው ቁልፍ ጥያቄዎች፣ የጥናቱ ጠቀሜታ፣ የጥናቱ ወሰን እና የጥናቱ ስነምግባር ተካትተዋል፡፡ በምዕራፍ ሁለት የጥናቱን ርእሰ ጉዳይ በሚመለከት የተጻፉ የንድፈ ሃሳብ ድርሳናት ክለሳ፣ የቀደምት ተዛማጅ ጥናቶች ዳሰሳ እና የመረጃ መተንተኛ ንድፈ ሀሳቦች ቀርበዋል፡፡ ምዕራፍ ሶስት የጥናቱ ዘዴ፤ የምርምሩ አይነት፣ የጥናቱ ንድፍ፣ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች፣ የናሙና አመራረጥ ዘዴ፣ የመስክ ተሞክሮ፣ በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች የሚሉ ርዕሰ ጉዳዮችን አካቶ ይዟል፡፡ ምዕራፍ አራት ጥናቱ የሚካሄድበት አካባቢ ማለትም የደሴ ከተማ አጠቃላይ መረጃ፣ ካርታዎች፣ መልከአምድራዊ አቀማመጥ፣ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ፣ ባህላዊ ገፅታ ወዘተ የሚሉት ጉዳዮች ተዳሰዉበታል፡፡ ምዕራፍ አምስት የመረጃ ትንተና የቀረበበት ሲሆን ከመስክ የተሰበሰቡ ጥሬ መረጃዎች በመልክ በመልክ ተደራጅተው በትንተና የቀረቡበት ክፍል ነዉ፡፡ ምዕራፍ ስድስት ደግሞ የጥናቱ ግኝት፣ ማጠቃለያ እና የይሁንታ ሀሳብ ቀርቦበታል፡፡

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

በተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች ባህል ውስጥ ለሰው፣ ለእንስሳት፣ ለቦታና ለሌሎችም ነገሮች መጠሪያነት የሚያገለግሉ የተለያዩ ስሞች በልዩ ልዩ ሁኔታዎች መነሻነት ይሰየማሉ፡፡ እነዚህ ለአካባቢው የተለዩና ማኅበረሰቡ በታሪክ አጋጣሚ፣ በአመክንዮ ወይም በተዛምዶ የሚሰይማቸው ስሞች በሀገረሰቡ የተወሰኑ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ ስም ማለት ማንኛዉም ለነገሮች የሚሰጥ መጠሪያ (ስያሜ) ነዉ፡፡ ይህን አስመልክተው ሰሎሞን (2011፡296) ሀገረሰባዊ ስም ሰዉን፣ እንስሳትን፣ እፅዋትን፣ ወይም ቦታን ከሌላዉ የመለየት መሰረታዊ ጠቀሜታ ያለው፣ የማህበረሰቡን ወይም የፎክ ቡድኑን ታሪክ፣ ፍልስፍና፣ ገጠመኝ፣ ባህል፣ የወደፊት ምኞት፣ ስነልቦና፣ ሀይማኖት ወዘተ የሚያሳይ መሆኑን ይገልፃሉ፡፡

ስሞች የትውስታና የተሞክሮ ቁልፍ መሳሪያ ናቸው፤ የአብሮነት ማሳያ ማህበራዊ ትዕምርቶችም ናቸው፡፡ ግለሰቡ ከሌሎች ጋር የሚጋራቸው ስሞች መጠን የአብሮነቱን ጠንካራነትና ልልነት ደረጃ ያመለክታል፡፡ በተለይም የቦታ ስሞች የግለሰቡን የቡድን አካልነት፣ ለአባላቱ የጋራ የሆኑት ስሞች ብዛትም በቡድኑ ውስጥ

ያለውን የትስስር ጥንካሬ የሚያሳዩ ማህበራዊ ምልክቶች (social signals) ናቸው። የቦታ ስሞቹ ሚናም በታላሚው ማህበረሰብና ዓውድ ውስጥ ለተሞክሮዎችና ድርጊቶች ምልክትና ማጣቀሻ ሆኖ ማገልገል ነው። የስሙን ስርዎ ፍጥረት (Etmology) እንዴትነት ሳንመረምር፤ ወካይና ተወካይ በአጠቃላይ፣ የጥናቱ ጉዳይ የሆኑት ስምና ቦታ በተለይ የማይነጣጠሉ መሆናቸውን እንገነዘባለን (Huldén 1994 in Helleland, 2012: 95)።

የቦታ ስም (toponym or place name) አንድ ማህበራዊ ቡድን ለሚኖርበት ከባቢ (environment) ወይም አካላዊ የምድር ቅርጽ (physical topography)፣ እንዲሁም በውስጡ ለሚገኙት ወንዞች፣ ተራራዎች፣ ቀበሌዎች፣ ከተማዎች፣ ጎዳናዎች ወዘተ የሚሰጠው መጠሪያ ነው። የሰው ልጅ በዙሪያው ለሚገኙ የምድር አቀማመጥ መዋቅሮች ስም በመስጠት ከባቢውን ጥቅም ላይ ሲያውል፣ በዚህም ምቹ ሆነው አካላዊና ስነልቡናዊ ደህንነቱን የሚረጋገጥ አወንታዊ ድርሻ እንዲኖራቸው ሲያደርግ ይታያል (Baker, 1972፣ )። ለተጠቀሱት ቦታዎች የተሰጡት ስሞችም በተሰየሙበት ዘመን ያለዉን ማህበረሰብ ታሪክ፣ ባህል፣ አመለካከት፣ ሀይማኖት ወዘተ የሚወክሉ፤ በተጨማሪም አንዱን ቦታ ከሌላዉ ለመለየት የሚያገለግሉ ውክልናዎች ናቸው። ይህን አስመልክተው ሙሉ (2011፡13) "የቦታ ስያሜ አንድ አካባቢያዊ መልክዓምድር ከሌላዉ ተለይቶ የሚታወቅበት መጠሪያ ብቻ ሳይሆን የተሰያሚዉን አካባቢ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበረ-ባህላዊ እሴቶች በያዘ ቋንቋ የተገነባ መኖሪያ ቦታ ነፀብራቅ ነዉ"። በማለት ይገልፃሉ።

ከልሂቃኑ ገለጻ የምንረዳዉ ማህበረሰቡ ስያሜን በመጠቀም አንዱን ከሌላዉ ለመለየት እና ለሚፈልገዉ ነገር ውክልና ወይም መጠሪያ በመስጠት ገጠመኙን፣ እምነቱን፣ አመለካከቱን፣ ታሪኩን፣ ባህሉን፣ ሀይማኖቱን ወዘተ መግለፅ የሚችል መሆኑን ነዉ። ይህም በቦታ ስሞች ላይ የሚደረግ ጥናት ከስያሜው ለውጥና ተከታታይነት ባሻገር የማህበራዊ ቡድኑን ማንነት፣ ስነልቦናና ማህበረ ባሃላዊ ዕሴቶች ገልጦ ማሳያ መሆኑን ያመለክታል።

የቦታ ስሞች በሆነ አጋጣሚ ሊለወጡ ወይም ስማቸዉን እንደያዙ ለዘመናት ሊቆዩ ይችላሉ። ይህም ማለት የቦታ ስሞች የተፈጠሩበትን ዘመን ማህበረሰብ ባህል፣ ታሪክ፣ ስነልቡና፣ ማንነት፣ ስነግንዛቤያዊ፣ ስነስሜታዊ፣ ስነልሳናዊና ርዕዮተ ዓለማዊ ባህሪያት እያንጸባረቁ በተከታታይነትና በቋሚነት ዘመን ሊሻገሩ ይችላሉ፤ በአንጻሩ የማህበረሰቡ ታሪክ፣ ባህል፣ ማህበረ-ስነልቡና ወዘተ ከሚያሳየው ዕድገት

ጋር ሊሻሻሉና ለውጥ ሊካሄድባቸውም ይችላል። ይህም ተከታታይና ለውጥ በሚሉት ቃላት የሚገለጸው ተቃርኖ በዚህ ጥናት የቦታ ስሞች አገልግሎት ላይ የቆዩበትንና የተለወጡበትን ጊዜ፣ የለውጡን ታሪካዊ፣ ባህላዊና ርዕዮተ ዓለማዊ ምክንያቶች ከዘመን አኳያ ለማጥናት ያስችላል፤ የታሪካዊ ሁነቶችን የዘመን ቅደም ተከተል ለመለየትም ይጠቅማል:

ተከታታይነትና ለውጥ በብዝሃ የእውቀት ዘርፎች (multi-discplinary) ላይ ባተኮሩ ጥናቶች የተሰጣቸው ፍች ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ ነው (Helleland, 2012፣ Baker, 1972፣ አስቴር፡ 2007)። በእነዚህ ጽሑፎች የተከታታይነትና የለውጥ ፍች የሚያጠነጥነው በመተካካት (ለውጥ) እና በዘላቂነት (ተከታታይነት) ላይ በመሆኑ አቻ የትርጉም ምስስል እንዳላቸው እንገነዘባለን። በዚህም መሰረት ተከታታይነት (Continity) አንድ ሁነት፣ ድርጊት ወይም ሂደት በያዘው ባህሪ፣ ስያሜና ሁኔታ ሳይለወጥ ለረጅም ዘመናት መቀጠልን ያመለክታል። ይህንም አስቴር (2007) ሌሎች ምሁራንን በመጥቀስ ተከታታይነት በጊዜ ሂደት ዉስጥ ያለማቋረጥ በድግግሞሽ የሚተገበር አንድን ድርጊት ለመግለፅ የምንጠቀምበት ቃል ነዉ በማለት ከገለጹት ጋር ይስማማል። ይህ ማለት ግን የሁነቶች፣ የድርጊቶችና የስያሜዎች ተከታታይና ቋሚ አገልግሎት በሆነ አጋጣሚ የሚለወጥበት ዕድሉ የተዘጋ ነው ማለት አይደለም። ከማህበራዊ ቡድኑ የባህል፣ የታሪክና የስነልቡና እድገት ጋር ሊሻሻልና ሊለወጥ ይችላል።

ለውጥ (Change) አንድ ነባራዊ ወይም ህሊናዊ ሁነት የነበረውን ስም ወይም ቅርጽ ትቶ አዲስ መለያ ሲይዝ ወይም ከነበረበት ቦታ ተንቀሳቅሶ አድራሻውን ሲቀይር የሚሰጠው ስያሜ ነው። በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፣ አማርኛ መዝገበ ቃላት (1993፣ 21) "ለውጥ" የሚለው ቃል አዲስ ሁኔታ፣ የተለየ ነገር፣ ልዩነት የሚል ፍች ተሰጥቶታል። በዚህ መሰረት ለውጥ በሰው ልጅ ህይወት ውስጥ በተለያዩ መንገዶች የሚከሰትና በነገሮች፣ በሁነቶችና ባህሪያት ላይ የሚታይ ያልነበረና አዲስ ክስተት ነው ሊባል ይችላል። የዚህ ምክንያቱ ደግሞ የሰው ልጅ አዲስ ነገርን የመፍጠር ፍላጎትና ጥረት ብቻ ሳይሆን የማህበረሰብ የታሪክ፣ የባህልና ልማድ ዕድገትም ሊሆን ይችላል (https://opentextbc.ca/introductiontosociology2ndedition/chapter/chapter-4-society-and-modern-life)።

በመሆኑም ይህ ጥናት በደቡብ ወሎ ዞን ዉስጥ ከሚገኙት ከተማዎች አንዱ በሆነዉ ደሴ ከተማ አስተዳደር ላይ የተካሄደ ሲሆን ትኩረቱን በከተማው የሚገኙትን የቦታ ስሞች ተከታታይነትና ለዉጥ በመመርመር ላይ አድርጓል፤ የስያሜዎችን ምክንያቶች፣ ወጥና ተለዋጭ ስሞችን፣ የለውጥ ሰበቦችን፣ አሉታዊ እና አዎንታዊ ፋይዳቸውንም ወዘተ. ፈትሿል።

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

አንድን የጥናት ችግር ለመምረጥ ሰበብ ወይም አነሳሽ የሚሆኑ ምክንያቶች በርካታ ናቸው። ከእነዚህ ውስጥ ከንድፈ ሃሳብ ድርሳናት ንባብ የሚገኝ ግንዛቤ፣ ከተግባራዊ ጥናቶች ዳሰሳ የሚታዩ የእውቀትና የመረጃ ክፍተቶችና በጥናቱ ጉዳይ ላይ ተመራማሪው ያካበተው ተሞክሮ በዋናነት ሊጠቀሱ ይችላሉ። በእዚህ መሰረት አጥኚዋ በትምህርት መርሀ ግብሩ የተካተቱትን ኮርሶች ስትማርና የኮርስ ማሟያ ፕሮጀክቶችን ስትሰራ በዳሰሰቻቸው የንድፈ ሀሳብና የምርምር ድርሳናት ስምን ከማንነት (Helleland, 2012)፣ ስምን ከአፈታሪክ (Baker, 1972) እና ተከታታይነትና ለውጥን ከአኗኗር ልማድ (አስቴር፣2007) አኳያ የተመለከቱት ስራዎች ትኩረቷን የሳቡ ሆነዋል። ከድርሳናቱ ባገኘችው ግንዛቤ መሰረትም የቦታ ስምን ከተከታታይነትና ከለውጥ አንጻር መፈተሽ የምርምር ትኩረቷ ሊሆን ችሏል።

ከላይ የተጠቀሱት የውጭ ጥናቶች የቦታ ስምን ያጠኑት ከማንነትና ከአፈ ታሪክ አኳያ ነው፤ አገረኛ ጥናቱም (አስቴር፣ 2007) ተከታታይነትና ለውጥን የፈተሸው ከአንድ ፎክ ቡድን የአኗኗር ልማድ አንጻር ነው። ይህም በተለይ በኢትዮጵያ የቦታ ስሞችን ለውጥና ተከታታይነት በሚመለከት የእውቀትና የመረጃ ክፍተት ሊኖር እንደሚችል አመላካች ይመስላል (አጥኚዋ ባደረገችው የንባብ ዳሰሳ በዚህ ጉዳይ ላይ የተደረገ ጥናት አላጋጠማትም) ። ይህም ርእሰ ጉዳዩን ለመምረጥ ሁለተኛው ምክንያት ሆኗታል።

አጥኚዋ በመኖሪያ አካባቢዋ ምንጫቸውን፣ ታሪካዊ ዳራቸውንና ስነልሳናዊ ባህሪያቸውን (ፍቻቸውን) የማታውቃቸው በርካታ የቀበሌ፣ የወረዳ፣ የጎዳና፣ የመናፈሻ፣ የወንዝና የተራራ ስሞችን ታውቃለች። በታዋቂ ግለሰቦች (ዶር. አረጋ ይርዳው ጎዳና፣ አሸብር ጎራ ወዘተ) እና በወቅታዊ ሁነቶች (የካቲት፣ አብዮት … ትምህርት ቤት) የተሰየሙ ወይም የተለወጡ ቦታዎችንም ታዝባለች። ይህ ተሞክሮዋም በርዕሰ ጉዳዩ ላይ ጥናቱን ለማድረግ ያነሳሳት ሶስተኛው ምክንያት

ሆኗል፡፡ ከእነዚህ ተጨባጭ ምክንያቶች በመነሳትም ለውጥና ተከታታይነት በቦታ ስሞች ላይ የሚለውን ርእሰ ጉዳይ ማጥናት አስፈላጊ ሆኖ አግኝተዋለች፡፡

### 1.3. የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በደሴ ከተማ የሚገኙ የቦታ ስሞችን ተከታታይነትና ለውጥ መመርመር ነው፤ ይህን አጠቃላይ ዓላማ ለማሳካት በመፈተሹ ሂደትም የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች ትኩረት ተደርጎባቸዋል፡፡

- ተከታታይነትን ጠብቀው የሚገኙ ቦታዎችን ስያሜዎችና የተከታታይነት ምክንያቶች መፈተሽ፤
- ለውጥ የተካሄደባቸውን የቦታ ስሞችና የለውጥ ምክንያቶች መለየት፤
- የቦታ ስሞችን ፋይዳ መለየት፤
- በቦታ ስሞቹ ተከታታይነትና ለውጥ ላይ የማህበረሰቡን አመለካከት መፈተሽ፤

### 1.4. ጥናቱ የመለሳቸዉ ቁልፍ ጥያቄዎች

ይህ ጥናት የተነሳበትን አላማ በማሳካት ሂደት የሚከተሉትን መሪ የምርምር ጥያቄዎች ለመመለስ ሞክሯል፡፡

- ተከታታይነትን ጠብቀው የሚገኙ የቦታ ስሞችና የተከታታይነት ምክንያቶች ምንድን ናቸዉ?
- ለውጥ የተካሄደባቸው የቦታ ስሞችና የለውጥ ምክንያቶች የትኞቹ ናቸው?
- የቦታ ስሞቹ ፋይዳ ምንድን ነዉ?
- የቦታ ስሞቹ ተከታታይነትና ለውጥ ላይ የማህበረሰቡ አመለካከት ምን ይመስላል?

### 1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ

ምርምር ችግርን የመፍታት፣ በመስኩ የታየውን የመረጃና የእውቀት ክፍተት የመሙላት ሂደት ነው፡፡ ከዚህ አኳያ የዚህ ጥናት ውጤት ለተለያዩ ተደራሽ አካላት ከዚህ ቀጥለው የተገለጹትን ጠቀሜታዎች ያስገኛል፡፡

- የፎክሎር ጥናት ልማዳዊውን ከዘመናዊው፣ ያለፈውን ከአሁኑና ከወደፊቱ ጋር በማስተሳሰር የፎክ ቡድኑን ታሪካዊ፣ ባህላዊና ፖለቲካዊ ሁነት ይመረምራል፤ በእዚህም ቡድኑ ያለፈውን እንዲገመግመው፣ የዛሬውን እንዲኖረውና ለነገው እንዲተጋ ያደርገዋል፡፡ ከዚህ አንጻር ታላሚው ቡድን

የሚያውቃቸውን ቦታዎች እና ቦታዎቹ የሚታወቁባቸውን ስሞች ከታሪኩ፣ ከባህሉና ከቋንቋ ጋር የተሳሰሩ/የተፋቱ መሆናቸውን ይገነዘብ ዘንድ ያግዘዋል፤ በሌሎች ዘንድም እንዲታወቅለት ያደርጋል፡፡

- የስሞቹ ስነልሳናዊ ባህሪ በሚፈተሽበት ክፍል የተደረሰበት የአንዳንድ ቦታ ስሞች የቋንቋዎችን ውሰት ብቻ ሳይሆን የማህበራዊ ቡድኖችን መስተጋብርም እንደሚያሳዩ ይጠበቃል፤ ይህም የመስተጋብሩን ታሪካዊ ዳራ፤ አዎንታዊ/አሉታዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ምጣኔ ሃብታዊ ወዘተ. ስለመሆኑ የታሪክ ግንዛቤን ያስጨብጣል፡፡

- ለውጥ የተካሄደባቸውን የቦታ ስሞች በመለየት ነባሮቹን ስሞች በመሰነድ አሻራቸው እንዳይጠፋና ለቀጣይ ትዉልድ እንዲተላለፉ በማድረግና ለቀጣይ የታሪክ ጥናቶች የመረጃ ምንጭ በመሆን ሊያገለግል ይችላል፡፡

- በርእሰ ጉዳዩ መጠነ ሰፊነት ብቻ ሳይሆን በጊዜና ገንዘብ ውስንነትም ጭምር በዚህ ጥናት የተዳሰሰው እጅግ ጥቂቱ መሆኑ ይታመናል፤ ይሁን እንጅ በመስኩ ሰፊና ጥልቅ ጥናት ለሚያደርጉ የዘርፉ ባለሙያዎች መነሻ ከመሆን አንጻር ጉልህ አስተዋጽኦ ይኖረዋል ተብሎ ይታሰባል፡፡

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በርዕሰ ጉዳይ እና በቦታ ተገድቦ የተካሄደ ነው፡፡ ከርዕሰ ጉዳይ አንጻር በሀገረሰባዊ ዉክልና ስር የሚካተተውን የቦታ ስያሜዎች ተከታታይነትና ለዉጥ በመመርመር ላይ ያተኮረ ነው፡፡ በዚህም የቦታ ስያሜዎችን ተከታታይነትና ለዉጥ በመመርመር ለለውጡ ምክንያት የሆኑትን የተጠኙውን ማህበረሰብ ታሪካዊ፣ ስነልሳናዊና ርእዮተ ዓለማዊ ዕድገቶች በተጓዳኝነት መርምሯል፡፡ ከቦታ አንጻርም ፈጣንና ተለዋዋጭ ማህበራዊ መስተጋብር የሚዘወተርበትን የከተማ ክልል ተተኳሪ በማድረግ በደሴ ከተማ አስተዳደር ስር የሚገኙትን የክፍለ ከተማዎች፣ የቀበሌዎች፣ የመንደሮች፣ የተራራዎች ወዘተ ስሞች ተደራሽ አድርጓል፡፡ ከእነዚህ ዉስጥ በትንተናዉ ክፍል የተካተቱት በእጣ ናሙና የተመረጡ ስሞች ናቸዉ፡፡

በሌላ በኩል የቦታ ስም ከፎክ ቡድኑ ማንነት፣ ስነልቦና፣ ርዕዮተ ዓለምና ታሪክ ወዘተ አንፃር ሊጠና እንደሚችል ይታወቃል። ይሁን እንጂ አጥኚዋ ባለባት የጊዜና የገንዘብ ውስንነት ምክንያት ብቻ ሳይሆን የጥናቱ አካባቢ የሆነው ደሴ ከተማ ከአራቱም አቅጣዎች የሚመጡ የተለያዩ ብሔረሰባዊ ማንነቶች፣ ባህልና ወግ

ያላቸውን ማህበራዊ ቡድኖች አክቶ የያዘ፣ በወቅታዊ ንግድና መሰል እንቅስቃሴዎች አዳዲስ የማኅበረሰብ ክፍሎች የሚስተናገዱበት በመሆኑ እነዚህን ተለዋዋጮች ጥናቱ ትኩረት አላደረገባቸውም፡፡

በከተማ አስተዳደሩ ስር ከሚገኙት የቦታ ስሞች ብዛት አኳያም በመረጃ ትንተናው የተካተቱት የተወሰኑት ተመርጠው ነው፤ በተለይ ተከታታይነትን ጠብቀው ዘመን የተሻገሩት የጥናቱን ዓላማ በተመለከተ የተለየ ባህሪ የሚታይባቸው ባለመሆኑ የተወሰኑት ተመርጠው ተተነትነዋል፡፡ ለውጥ ከተካሄደባቸውም ሆኑ ተከታታይነትን ጠብቀው ከዘለቁት መካከል በአሰያየም ዳራቸውና በለውጥ ምክንያቶቻቸው በአንጻራዊነት የተሟላ መረጃ የተገኘላቸው ተመርጠው ተተንትነዋል፡፡

## 1.7. የጥናቱ ስነምግባር

መረጃ ለመሰብሰብ መስክ ከመሄዴ በፊት ከተለያዩ ተቋማት ጋር በመሄድ የድጋፍ ደብዳቤ እንዲሰጡኝ አድርጌያለሁ፡፡ መረጃ ከሚሰጡኝ አካላት ጋር ቀጠሮ በማስያዝ እንዲሁም ከቀጠሮ ሰአታችን በፊት ቀደም ብየ ለመገኘት ሞክሬያለሁ፡፡ መረጃ ከመሰብሰቤ በፊት ከመረጃ ሰጭዎቼ ጋር ጥሩ ግንኙነት እንዲኖረኝ አድርጌያለሁ፡፡ መረጃ በምሰበስብበት ወቅት ፎቶ ግራፍ ማንሳት እና የድምፅ ሪከርድ መጠቀም እንደምችል የመረጃ ሰጭዎቼን ፈቃድ ጠይቄያለሁ፡፡ መረጃ ስሰበስብ ምስላቸዉ እንዳይነሳ እና የድምፅ ሪከርድ እንዳልጠቀም የከለከሉኝ አንዳንድ መረጃ ሰጭዎች ነበሩ በመሆኑም ፎቶ ግራፍ ባለማንሳትና መረጃየን በፁሁፍ ብቻ በመያዝ ፍላጎታቸዉን አክብሬያለሁ፡፡

# ምዕራፍ ሁለት፡- ክለሳ ድርሳናት

በዚህ የድርሳናት ክለሳ ምእራፍ የጥናቱ ማጠንጠኛና የባህል ጥናት ዘርፍ የሆነውን የቦታ ስያሜ አወጣጥ፣ ለውጥና ተከታታይነት የሚመለከቱ ንድፈ ሃሳቦች፣ መርሆዎች፣ መስፈርቶችና የተግባራዊ ምርምር ግኝቶች ከመስኩ ድሠርሳናት ተጨምቀው ቀርበዋል፡፡ በእዚህም በአንድ በኩል የቦታ ስያሜ፥ በተለይም የስም ለውጥና ተከታታይነት፣ በሌላ በኩል ከስያሜው ለውጥና ተከታታይነት ጋር የሚከሰቱ ማህበረሰባዊ ዕሴቶች፤ ታሪካዊ፣ ስነልሳናዊ፣ ባህላዊ፣ ስነልቡናዊ ወዘተ ሁነቶች ከዘረፉ የአተያይ አቅጣጫዎችና ትውሮች አኳያ ተተንትነዋል። በተመረጠው የጥናት ችግር ዙሪያ የተደረጉ ቀደምት ተዛማጅ ጥናቶችም ተቃኝተዋል። የተገኙት ተሞክሮዎች ጭምቃሳብም እንደሚከተለው ቀርቧዋል።

## 2.1. የፅንሰ ሀሳብ ዳሰሳ (Conceptual Fram works)

በዚህ ርዕስ ስር የስያሜ ምንነት፣ የስያሜ አጀማመር፣ የቦታ ስያሜ ምንነት፣ የቦታ ስያሜ መነሻ ምክንያቶች፣ የቦታ ስያሜ ፋይዳ፣ የተከታታይነት ፅንሰ ሀሳብ እና የለውጥ ምንነት የሚሉት ንዑሳን ርዕሰ ጉዳዮች ተተንትነዋል፡፡

### 2.1.1. የስያሜ ምንነት

ስያሜ ለሰዎች፣ ለእንስሳት፣ ለግኡዝ ነገሮች፣ ለቦታ ወዘተ. የሚሰጥ ወኪል ወይም መጠሪያ ነዉ፡፡ ይህን አስመልክቶ ሰለሞን (2010 ዓ.ም) አንዳርጌን (1996 ዓ.ም) ገልጾ ስያሜ ወይም ስም የማንኛዉም ነገር መጠሪያ ነዉ፡፡ ያለ ስያሜ አንድን ነገር ከሌላ ነገር ለይቶ ለመጥራትና ለማወቅ አይቻልም፡፡ ስያሜ ማለት ሰዎች፣ እንስሳት፣ ቦታ እና ሌሎች ነገሮች የሚጠሩበት ቃል ነዉ በማለት ይገልፃል፡፡ ከዚህ ሀሳብ እንደምንረዳዉ ስያሜ ለነገሮች መለያ ወይም ወኪል በመስጠት አንዱን ከሌላው ለይቶ ለማወቅ የምንገለገልበት መሆኑን ነዉ፡፡

### 2.1.2. የስያሜ አጀማመር

ለነገሮች ወኪል ወይም ስያሜ መስጠት የተጀመረዉ የሰዉ ልጅ ወደ ምድር ከመምጣቱ ጋር የተያያዘ እንደሆነ ከመፅሀፍ ቅዱስ እና ከቅዱስ ቁርአን መረዳት ይቻላል፡፡ የስያሜ አሰጣጥን አስመልክቶ የሃይማኖት ድርሳናት (ኦሪት ዘፍጥረት 2፣19-20) ሲገልፅ፤ "እግዚአብሄር አምላክም የምድር አራዊትንና የሰማይ ወፎችን ሁሉ ቀድሞ ከምድር ፈጠረ፡፡ በምን ስም እንደሚጠራቸዉ ያይ ዘንድ ወደ አዳም አመጣቸዉ፡፡ አዳምም ህያዉ ነፍስ ላለዉ ሁሉ በስሙ እንዲጠራዉ ስሙ ህያዉ

ሆነ፡፡ አዳምም ለእንስሳት ሁሉ ለሰማይ ወፎችም ሁሉ ለምድር አራዊትም ሁሉ ስም አወጣላቸዉ” በማለት ይገልፃል፡፡ በተጨማሪ ደግሞ ቅዱስ ቁርአን (ሱረቱል በቀራ 2-31) “አላህ ለአደም የሁሉንም ስሞች አስተማረዉ፤ ከዚያም (ተጠሪዎቹን) አቀረባቸዉ፡፡ እዉነተኞችም እንደሆናችሁ የእነዚህን (ተጠሪዎች) ስሞች ንገሩኝ” አላቸዉ፡፡ ሱረቱል በቀራ (2-33) ደግሞ አደም ሆይ ስሞቻቸዉን ንገራቸዉ አለዉ፤ ስሞቻቸዉን በነገራቸዉ ጊዜ እኔ የሰማያትና የምድርን ሩቅ ሚስጥር አዉቃለሁ፡፡ የምትገልፁትንና ያንንም ትደብቁት የነበራችሁትን አዉቃለሁ አላልኳችሁምን?” አላቸዉ፡፡ ከሁለቱ ሀይማኖት አስተምህሮዎች መረዳት የሚቻለዉ ስያሜ አገልግሎት ላይ የዋለዉ የሰዉ ልጅ ወደ ምድር ከመምጣቱ ጋር ተያይዞ መሆኑን ነዉ፡፡ ይህን መነሻ በማድረግም የአሁኑ ሰዉ ለህያውና ግዑዝ ነገሮች ሁሉ ስም በመስጠት መጠቀም እንደቻለ እንገነዘባለን፡፡

### 2.1.3. የቦታ ስያሜ ምንነት

የቦታ ስያሜዎች የጥንት የሰዉ ልጅ ባህላዊ ቅርስ ማሳያዎች ናቸዉ፡፡ የአካባቢ መጠሪያ ስሞች የነዋሪዉ ማህበረሰብ የማይዳሰስ ባህላዊ ቅርሶች አንድ አካል ሲሆኑ በስያሜዎቹ ውስጥም ለምንና በማን እንደተሰየሙ አመላካች እዉቀቶችን ይዘው ይገኛሉ፡፡ በዚህም መሰረት ካለፉት ዘመናት ጋር በተያያዘ ህዝቦች ከኖሩባቸዉ አካባቢዎች የስም አወጣጥና ስያሜ ጋር ተያይዞ የሚኖሩ መረጃዎች ስለአካባቢዉ ተጨማሪ የታሪክ አስረጂ ሆነዉ ያገለግላሉ (Helleland 2012, 95-116)::

የቦታ ስሞች እንደ ሌሎች መጠሪያ ስሞች ሁሉ የሰዉ ልጅ ስነልሳናዊ ማንነትና የቋንቋ አጠቃቀም ማሳያዎች ናቸው፡፡ የሰዉ ልጅ ግኡዝ አካላትን፣ ሰዎችን፣ እንስሳትን፣ ህንጻዎችን፣ ድርጅቶችንና ቦታዎችን ለመለየትና ለመጥራት የተለያየ ስያሜ ይሰጣቸዋል። በአካባቢዉ ለሚገኙ ህይወት ላላቸዉም ሆነ ለሌላቸዉ አካላት ለመለያና ለመጠሪያነት የሚያገለግሉ ስያሜዎችን ሲሰጥ በመነሻነት አንድን ነገር ለማመልከትና ለመግለጽ ቢሆንም ከስያሜነት ባሻገር ዉስጣዊ ስሜቱን ለመግለፅ፣ ስነልሳናዊ ማንነቱን ለማሳየት፣ ሀሳቡን ለማንጸባረቅና ማህበራዊ ራዕዩን ለማጋራትም ይጠቀምበታል (Anderson, 1994)፡፡ ከዚህ ሀሳብ እንደምንረዳዉ ሰዎች ስያሜን የሚጠቀሙት ወይም ስያሜን የሚሰጡት ነገሮችን ለመለየት ብቻ ሳይሆን ውሠታዊ ስሜታቸውንም፤ ማለትም ደስታቸዉን፣ ሀዘናቸውን፣ አግራሞታቸውን ወዘተ. እና መሰል ጉዳዮችን ለማንፀባረቅ ወይም ለሌሎች ለማጋራትም ነዉ፡፡

### 2.1.4. የቦታ ስያሜ መነሻ ምክኒያቶች

የቦታ ስያሜ መነሻ ምክያቶች በርካታ ሲሆኑ ከነዚህም ዉስጥ የመልከአምድር አቀማመጥ፣ ፖለቲካዊ ሁኔታ፣ ሀይማኖታዊ ሁኔታ፣ አስገራሚ ክስተቶችና ተፈጥሯዊ ሁኔታዎች ዋና ዋናዎቹ ናቸዉ፡፡ ማህበረሰቡ የሆነ ሁነትን ወይም ክስተትን መነሻ በማድረግ ለቦታዎች ስያሜ ይሰጣል፡፡ ይህን አስመልክቶ ጥሩአለም (2012፡21) "ለቦታ ስያሜ መነሻ ከሚባሉት መካከል ድርጊት ወይም ክስተት አንዱ ነዉ፡፡ በኑሮ ሂደትና በተለያዩ አጋጣሚዎች ክስተቶች መነሻ ይሆኑና መጠሪያ ስሞች ይፈጠራሉ" በማለት ይገልጻሉ፡፡

ለቦታ ስያሜ መነሻ የሆኑ በርካታ ምክንያቶ አሉ፡፡ ከነዚህም ዉስጥ የማህበረሰቡ ፖለቲካዊ ሁኔታ፣ ማህበራዊ ሁኔታ፣ ባህላዊ ሁኔታ፣ ሀይማኖታዊ ሁኔታ፣ የቦታዉ መልከአምድራዊ አቀማመጥ፣ ቦታዉ ላይ የተከሰተ አስደንጋጭ ወይም አሳዛኝ ሁነቶች ወዘተ ለስያሜ መነሻ ምክንያት ሊሆኑ እንደሚችሉ መረዳት ይቻላል፡፡

### 2.1.5. የቦታ ስያሜ ፋይዳ

ስሞች የሰዉ፣ የእንስሳ፣ የህንፃ፣ የድርጅቶች፣ ሌሎችም በሰዉ ልጆች የተሰሩ ቁሶችን በስም ወክለዉ ሲቆሙ የቦታ ስሞች ደግሞ የሰዉ ልጆች የኖሩበትን ዘመን በዘመናቱም ዉስጥ ያከናወኗቸዉን ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች፣ ታሪካዊ ክስተቶች፣ ባህላዊ ክዋኔዎች፣ ሀይማኖታዊ እሳቤዎች እና ሌሎችም ድርጊቶች ያለፈዉን ወደ ፊት ስበዉ የሚያሳዩን ናቸዉ በማለት ጥሩ አለም (2012፡22) ገልፃለች፡፡ ከዚህ ሀሳብ እንደምንረዳዉ የሰዉ ልጅ በስያሜ አማካኝነት ማህበራዊ ሂወቱን፣ ያሳለፈዉን ታሪካዊ ክስተት፣ ባህሉን፣ ሀይማኖቱን ስያሜን በመጠቀም ወደፊት የሚያሻግርበት ሂደት እንዳለ ነዉ፡፡

የቦታ ስያሜ ለሰዉ ልጅ የተለያዩ ጠቀሜታዎችን ይሰጣል ከነዚህም ዉስጥ ፖለቲካዊ ፋይዳ፣ ማህበራዊ ፋይዳ፣ ትዕምርታዊ ፋይዳ እና ታሪካዊ ፋይዳ ይጠቀሳሉ፡፡

#### 2.1.5.1. ማህበረ ባህላዊ ፋይዳ

የቦታ ስሞች የአንድን ማህበረሰብ ባህላዊ እሴቶች፣ ታሪክ፣ ሀይማኖት፣ ርዕዮተ አለሙን ወዘተ ለመግለፅ ያገለግላሉ፡፡ አሁን ላይ የሚሰጡ የመኖሪያ አካባቢ፣ የመንገዶች፣ የቦታ ስያሜዎች የጋራ አኖማስቲክ አረዳድና ቅርስን የሚያሳዩ እና የሚገልፁ ናቸዉ፡፡ እነዚህ ስያሜዎች የአካባቢዉን ነዋሪ ማንነት ሊገልፁ የሚችሉ

እንዲሁም የነዋሪዉን ማህበራዊ እሴቶችን በዉስጣቸዉ የያዙና በተጨማሪም ማህበረሰቡ በአካባቢዉ ላይ የእኔነት ስሜት እንዲሰማዉ የሚያደርጉ ናቸዉ (Olsen, 1939):: ይህ ማለት ማህበረሰቡ በስያሜ አማካኝነት ባህሉን፣ እምነቱን፣ አስተሳሰቡን፣ ኢኮኖሚዉን ወዘተ ጉዳዮች በስያሜ አማካኝነት ማንፀባረቅ ይችላል ማለት ነዉ።

### 2.1.5.2. ታሪካዊ ፋይዳ

የቦታ ስሞች በአንድ ቦታ ላይ የተከሰተን ታሪክ የመግለፅ ብቃት አላቸዉ። ማህበረሰቡ ታሪኩን በስም አማካኝነት ከትዉልድ ወደ ትዉልድ ያስተላልፋል። በዚህም ታሪኩን ጠብቆ እንዲቆይ ያደርጋል። የቦታ ስሞች የሀዉልቶችን፣ የሙዚየሞችንና ሌሎች ዝክረ ነገሮችን ያህል የገላጭነት ባህሪ ባይኖራቸዉም ያለፈዉን ሂወት በሚዘክሩ ተግባራትና ክስተቶች ርዕዮተ አለማዊ መረጃዎችን ያመላክታሉ። እንደ ተፈጥሯዊ ስርአት ወይም ሁነት የሚከሰቱ እዉነተኛ የታሪክ ቅጅዎችን ይፈጥራሉ (Armada:1998):: በተጨማሪም Tilley,(1994፡18) ለቦታዎች የሚሰጡ ስያሜዎች ቦታን ወይም የሆነ ጂኦግራፊካል አካባቢ ከመግለጽ ባሻገር ታሪክንና የማህበረሰብን የጋራ ልምድ ማሳያ በመሆኑ አስፈላጊነቱ እጅግ የጎላ እና ከፍ ያለ ነዉ በማለት ይገልፃሉ። የአካባቢ መጠሪያዎች የሰዉ ልጅ በተለያየ ጊዜያት ከተፈጥሮ ጋር በነበረዉ የተለያዩ ዉጣ ዉረዶችና አጋጣሚዎች ዉጤቶችም ናቸዉ። በተጨማሪም የሰዉ ልጅ ለተለያዩ አካባቢዎችና ቦታዎች የተሰጡትን ስያሜዎች በደንብ ማስተዋል ከቻለ ያለፉ ጊዜያትን የታሪክ ክስተቶችን መረዳት እንዲችል አስቻይ ሁኔታዎችን ማግኘት ያስችለዋል። በዚህ መሰረትም የቦታ ስያሜዎች በትኩረት ከተመለከትናቸዉ በምንነጋገርበታ ቋንቋ በቀጥታ ባያወሩም በዉስጣቸዉ ሊነበቡ የሚችሉ በእይታ የምንረዳቸዉ ብዙ ሚስጥሮችን አቅፈዉ የያዙ ገላጭ ግኡዛን ናቸዉ። (osla volume 4(2),2012 (102).

### 2.1.5.3. ፖለቲካዊ ፋይዳ

የቦታ ስሞች ፖለቲካዊ ፋይዳ አላቸዉ። ይህ ማለት ስሞች ሲወጡም ሆነ ነባር ስሞች ለፖለቲካ አላማ ታስበዉ ይቀየራሉ። ይህን አስመልክቶ Andersson-Helleland (2002፣1)ን በመጥቀስ "አዳዲስ ስያሜዎች ሲፈጠሩ ነባር ስሞች ሊጠፉ ይችላሉ። ማህበረሰቡ እያደገና ዘርፈ ብዙ እየሆነ ሲመጣ የቦታ ስያሜዎችም በአዳዲስ እየተተኩ የፖለቲካ እሳቤያቸዉ ትርጉሙ እየተቀየረ ይሄዳል። ይህን ጠብቆ ለማቆየት ባለስልጣናት የሰሯቸዉን በጎ ተግባራት ለማስጠበቅ ፣ ለመቆጣጠርና

ስማቸዉን ለመትከል ይጠቀሙበታል" በማለት ያብራራሉ፡፡ ይህ ጥናት በተደረገበት አካባቢ በፖለቲካ ምክንያት የተለወጡ ስሞች እንዳሉ ለማየት ተሞክሯል፡፡ ለአብነትም ቀድሞ እቴጌ መነን የነበረዉ ስያሜ በደርግ ጊዜ ተለዉጦ ወደ ፍሬ አብዮት እንደተቀየረ፣ ወ/ሮ ስህን ት/ቤት ወደ የካቲት 17 እንደተቀየረ አሁንም በፖለቲካ ሽግግር ምክንያት ወደ ቀድሞ ስሙ እንደተቀየረ የተገኙት መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ በወቅቱ ያለዉን የፖለቲካ ሁኔታ ወደ ማህበረሰቡ ዘንድ ለማድረስ ስያሜን እንደ መሳሪያ ይጠቀሙ እንደነበር ለማወቅ ተችሏል፡፡

#### 2.1.5.4. ትዕምርታዊ ፋይዳ

የቦታ ስሞች ትዕምርታዊ ፋይዳ ያላቸዉ ሲሆን አንድን ነገር በመወከል ለማህበረሰቡ መልዕክት የማስተላለፍ ስራ ወይም የማስተማር አገልግሎት አላቸዉ፡፡ ማህበረሰቡም ማንነቱን የሚገልፅበትም መንገድ ነዉ፡፡ ይህን አስመልክቶ Giddens (1996) የቦታ ስያሜዎች የአንድን ማህበረሰብ ትዕምርታዊ ወይም ተምሳሌታዊ በሆነ መንገድ ማንነቱን የሚያንፀባርቅበት ስልት ነዉ በማለት ያስረዳሉ፡፡ በተጨማሪም Guyot and Seethal (2007፣3) የቦታ ስሞች የጋራ ማንነት የሆኑ ታሪክ፣ ፖለቲካና ማህበራዊ ግንዛቤዎችን ማንቂያ እና ማሳደጊያ ትዕምርቶች ሆነዉ ሊያገለግሉ ይችላሉ በማለት ይገልፃሉ፡፡ በዚህ ጥናትም ትዕምርታዊ ፋይዳ ያላቸዉ የቦታ ስያሜዎች እንዳሉ ለማወቅ ተችሏል፡፡

### 2.1.6. ተከታታይነት

ተከታታይነት ስንል በጊዜ ሂደት ውስጥ ያለማቋረጥ በድግግሞሽ የሚተገበር አንድን ልማድ ወይም ድርጊት ለመግለፅ የምንጠቀምበት ቃል ነው፡፡ Sims and stephens (2005, 65) የተከታታይነት ጽንሰ ሃሳብ በልማድ ውስጥ የጊዜንና የመደጋገም አስፈላጊነትን ይጠቁማል በሚል ይገልጹታል፡፡ ከዚህ ሀሳብ እንደምንረዳዉ የተከታታይነት ፅንሰ ሀሳብ አንድ ድርጊት ወይም ሁነት ያለማቋረጥ እየተደጋገመ የሚተገበር ወይም የሚቆይ መሆኑን የምንገልፅበት መንገድ እንደሆነ ነዉ፡፡ የቦታ ስሞች ለረጅም ጊዜ ስያሜያቸዉን እንደያዙ ይቆያሉ፡፡ በዚህ ጥናትም የቦታ ስያሜዎችን ተከታታይነት ወይም ለረጅም ጊዜ ስያሜያቸዉን ሳይቀይሩ የቆዩትን የቦታ ስሞችን በተመለከተ ትንተና ተደርጓል፡፡

### 2.1.7. ለውጥ

ለውጥ የሰው ልጅ ህይወት ውስጥ በተለያየ መንገድ ሊከሰት እና ሊታይ ይችላል፡፡ ነገሮችን ሁልጊዜ አዲስ ለማድረግ መሞከር የሰው ልጅ ዘላለማዊ ወይም ቀጣይነት ያለው ፀባይ እስከሆነ ድረስ ለውጥ በዚህ ምድር ላይ ሊቆም የሚችል ነገር አይደለም፡፡ የኢትዮጵያ ቋንቋ ጥናትና ምርምር ማዕከል አማርኛ መዝገበ ቃላት (1993፣21) ለውጥ የሚለዉን ቃል አዲስ ሁኔታ፣ የተለየ ነገር፣ ልዩነት በማለት ይተረጉመዋል፡፡ ለውጥ በቦታዎችና በአካባቢዎችም ላይም የሚከሰት፣ የሚስተዋልና የሚቀጥል ነው፡፡ ይህን አስመልክቶ Stewart (1967,7) "ሰዎች አዳዲስ ነገሮችን መስራት ይፈልጋሉ፡፡ ፈልገዉም አይቀሩም ይሰራሉ፡፡ ለሚሰሯቸዉም አዳዲስ ነገሮች ስያሜ ይሰጣሉ፡፡ የቆዩ ስሞች ደግሞ አዲስ ነገር በተፈጠረ ቁጥር መልካቸዉ እየደበዘዘ ይሄድና መበጨረሻም ይጠፋሉ በዚህ ምክንያት ስያሜ ቶሎ የመለወጥ እድል ወይም ባህሪ ይኖረዋል" በማለት ይገልፃሉ፡፡ በሰው ልጅ አዲስ ነገርን የመፈለግ ባህሪና እንዲሁም በተለያየ ማህበራዊ፣ ታሪካዊ፣ ፖለቲካዊና ሀይማኖታዊ አጋጣሚዎችን ተከትሎ በርካታ ቦታዎችና አካባቢዎችም የለውጥ ሰለባ ወይም ተቋዳሽ ለመሆን ችለዋል፡፡ የዚህ ሰለባ ከሆኑት ወስጥ ደግሞ ይህ ጥናት የተካሄድበት ደሴ ከተማ አንዱ ነው፡፡

## 2.2. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

የዚህ ጥናት ርእስ ተከታታይነትና ለውጥ በቦታ ስያሜዎች ላይ ሲሆን ከዚህ በፊት የተሰሩ የተለያዩ ጥናቶች ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡ ተዛማጅ ጥናቶች ዳሰሳ ባደረኩበት ወቅት ከዚህ ጥናት ጋር ግንኙነት ያላቸዉ በመጀመሪያ ዲግሪና በሁለተኛ ዲግሪ ደረጃ የተሰሩ ጥናቶችን አግኝቻለሁ፡፡ በመሆኑም በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ በመጀመሪያ ዲግሪ የተሰሩ ሶስት ጥናቶች በሁለተኛ ዲግሪ የተሰሩ ሁለት ጥናቶች በድምሩ አምስት ጥናቶች በዳሰሳዉ ወቅት ተገኝተዋል፡፡ የተገኙት ጥናቶች ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስላቸዉን ወይም ልዩነቶቻቸዉን የመፈተሸ ስራ ተከናዉኗል፡፡ ጥናቶቹ በአላማቸዉ፣ በአጠናን ዘዴ፣ ከመረጃ መተንተኛ ንድፈ ሀሳብ እና ከጥናት ግኝት ወይም ዉጤት አንፃር ክለሳ በማድረግ እንደሚከተለዉ ቀርበዋል፡፡

### 2.2.1. ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የቀረቡ ጥናቶች

በዚህ ስር ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የቀረቡ ሶስት ጥናቶች ላይ ዳሰሳ ለማድረግ ተሞክሯል፡፡

የመጀመሪያዉ ጥናታዊ ፁሁፍ የሰሎሞን ይርጋ በዋልድባ ገዳም ዉስጥ የሚገኙ የቦታ ስያሜዎች አሰጣጥ ይዘታዊ ትንተና በሚል ለፎክሎር ትምህርት ክፍል ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ በ2010 ዓ.ም የተጠና ነዉ፡፡ የሰሎሞን ጥናት ቦታ ስያሜ ላይ ትኩረት ማድረጉ ከእኔ ጋር ያመሳሰለዉ ሲሆን የጥናቱ አላማም፡- በዋልድባ ገዳም ዉስጥ ያሉት ቦታዎች ምን ምን እንደሆኑ በዘዉግ መተንተን፣ በገዳሙ ዉስጥ የሚገኙ የቦታ ስያሜዎች እና የስያሜ አጋጣሚዎችን ይዘት መግለጽ እና ቦታዎቹ የተሰየሙበት አጋጣሚ ወይም አዉድ ማሳየት የሚል ነዉ፡፡ ከቃለመጠይቅ እና ከምልከታ የሰበሰባቸዉን መረጃዎች በመልክ በመልክ በማደራጀት ገላጭ የመተንተኛ ዘዴን በመጠቀም የይዘት ትንተና አድርጓል፡፡

በጥናቱ ዉስጥ የቦታ ስያሜ አጋጣሚዎችን ያሳየ ሲሆን፡- ከቦታዉ መልክዓምድራዊ አቀማመጥ አንፃር የተሰየሙ የቦታ ስያሜዎች፣ በአካባቢዉ በነበሩ ነገስታት መነሻነት የተሰየሙ የቦታ ስያሜዎች እና ከሀይማኖት ጋር በተያያዘ የተሰየሙ የቦታ ስያሜዎች በማለት ለትንተና አቅርቧል፡፡

በጥናቱ ዉጤትም ዋልድባ ገዳም ስያሜ በድንግል ማሪያም ምክንያት እንዳገኘ የመጀመሪያ መናኒያን ከሸዋ ክፍለ ሀገር ከብሄር ቡልጋ እንደመጡና ሲመጡም ጌታ እየሱስ ክርስቶስ እየመራቸዉ እንደመጣ በጉዟቸዉ ወቅትም ላገኙዋቸዉ ቦታዎች ካላቸዉ መልክአምድራዊ አቀማመጥ መሰረት አድርገዉ ስያሜ እየሰጡ እንደመጡ አረጋግጧል፡፡

የሰለሞን ጥናት ጠንካራ ጎን እንዳሉት ሁሉ ክፍተትም አለዉ፡፡ እንደ ጥንካሬ ያየሁት መረጃን ለመሰብሰብ ምልከታ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴን መጠቀሙ እና የቦታ ስያሜ አጋጣሚዎችን ለይቶ ለትንተና ማቅረቡ መልካም ነዉ፡፡ ለዝርዝር አላማዎቹም መልስ የሰጠበት መንገድ ጥሩ ነዉ፡፡ በክፍተት ያየሁት ደግሞ በጥናቱ ዉጤት ላይ ያስቀመጠዉ ሀሳብ ስለ ዋልድባ ገዳም ስያሜ አመጣጥ እንጅ በዋልድባ ገዳም ዉስጥ ስለሚገኙ ቦታዎች ምንም ያለዉ ነገር አለመኖሩ እንደ ድክመት ወስጄዋለሁ፡፡

የሰሎሞን እና የእኔን ጥናት የሚያመሳስላቸዉ ሁለታችንም የቦታ ስያሜ ላይ ትኩረት ማድረጋችን ሲሆን የሰሎሞን ትኩረቱ የቦታ ስያሜ አሰጣጥ ይዘታዊ ትንተና ሲሆን የእኔ ጥናት ደግሞ ተከታታይነት እና ለዉጥ በቦታ ስያሜ ላይ ነዉ፡፡

ልዩነትን በተመለከተ የጥናታችን አላማና የጥናቱ ዉጤት የተለያየ ነዉ፡፡ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴን በተመለከተ እኔ ቃለመጠይቅ ፣ሰነድ ፍተሻ፣ ምልከታና ቡድን

ተኮር ዉይይት የተጠቀምኩ ሲሆን ሰሎሞን ግን ቃለ መጠይቅና ምልከታን ብቻ መጠቀሙ እንዲሁም የጥናቱ ቦታ የተለያየ መሆኑ ልዩነት እንዲኖረዉ አድርጓል፡፡

ሁለተኛዉ ጥናት የአዴ ወርቁ በጎንጅ ቆለላ ወረዳ የቦታ ስያሜዎች አፈታሪካዊ አመጣጥ ይዘታዊ ትንተና ሲሆን በ2005 ዓ.ም ለፎክሎር ትምህርት ክፍል ለመጀመሪያ ዲግሪ ከፊል ማሟያት የቀረበ ጥናታዊ ፁሁፍ ነዉ፡፡

የአዴ ጥናት አላማም የቦታ ስያሜዎች ይዘት ምንድን ነዉ፣ በጎንጅ ቆለላ ወረዳ ዉሰጥ የሚገኙ የቦታ ስያሜዎች የስያሜ አጋጣሚዎችን መጠቆም እና የቦታ ስያሜዎቹ በማህበረሰቡ ዉስጥ ምን አይነት ፋይዳ ይሰጣሉ የሚሉ አላማዎችን ይዞ በመነሳት ጥናቱን አካሂዷል፡፡ የተሰበሰቡትን መረጃዎች ገላጭ የመተንተኛ ዘዴን በመጠቀም መረጃዎን ተንትኗል፡፡ በጥናቱም ከሀይማኖት ጋር በተያያዘ የተሰጡ የቦታ ስያሜዎች፣ ለሰዉ ልጅ መኖሪያነት ካላቸዉ ምቹነትና አስቸጋሪነት ጋር በተያያዘ የተሰጡ የቦታ ስያሜዎች፣ ፖለቲካዊ ወይም አስተዳደራዊ የሆኑ ጉዳዩችን መሰረት በማድረግ የተሰጡ የቦታ ስያሜዎች እና ከዉበት ወይም ከቁንጅና ጋር በተያያዘ የተሰጡ የቦታ ስያሜዎች መኖራቸዉን በጥናቱ አረጋግጧል፡፡

የአዴ እና የእኔ ጥናት የሚያመሳስለዉ ሁለታችንም ቦታ ስያሜ ላይ ትኩረት ማድረጋችን እና ሁሉንም አይነት ቦታዎች ማለትም የቀበሌ፣ የመንደር፣ የተራራ ወዘተ ስሞችን መዳሰሳችን በተጨማሪም የቦታ ስያሜ ፋይዳ መግለፅ እና የስያሜ አጋጣሚዎችን መፈተሽ የሚለዉ አላማ ያመሳስለናል፡፡ በጥናት ዉጤትም የተወሰነ ተመሳስሎሽ አለን፡፡

ልዩነትን በተመለከተ ሁለታችንም የቦታ ስያሜ ላይ ትኩረት እናድርግ እንጅ የእኔ ተከታታይነትና ለዉጥን ማጠንጠኛ ሲያደርግ የአዴ ደግሞ የቦታ ስያሜ ይዘት ትንተና ዋና አላማ ማድረጉ ልዩነት እንዲኖረዉ አድርጓል፡፡ የጥናት ቦታችን መለያየትም ለልዩነታችን አንዱ ምክንያት ነዉ፡፡

በሶስተኛነት የምናገኘዉ የሰሚራ ሰይድ ጥናት ነዉ፡፡ ይህ ጥናት በአንጋጫ ወረዳ ዉስጥ ባሉ የቦታ ስያሜዎች የተነገሩ አፈታሪኮችን ይዘት መመርመር ሲሆን የቦታ ስያሜዎች ምክኒያት እና አፈታሪኩ ምን ምን ጉዳዮች ላይ ትኩረት ያደርጋል የሚሉ ሁለት ጥያቄዎችን መነሻ አድርጋለች፡፡ ለጥናቷም መረጃን ከምልከታ እና ከቃለመጠይቅ በመሰብሰብ ለትንተና አቅርባለች፡፡

ሰሚራ በጥናቷ ዉጤት ለቦታ ስያሜዎች ምክኒያት ወይም መንስኤ የሆኑ ነገሮች የነዋሪዎቹ ባህል፣ ወግ፣ ታሪካዊ አጋጣሚዎች እና የቦታዉ መልክአምድራዊ አቀማመጥ እንደሆነ አረጋግጣለች፡፡

የሰሚራ ጥናት የይሁንታ ሀሳብ ያልቀረበበት መሆኑ እንደ ክፍተት ወስጄዋለሁ፡፡

የሁለታችንን ጥናት የሚያመሳስለዉ ቦታ ስያሜ ላይ ትኩረት ማድረጋችን ሲሆን ከጥናቱ ዉጤት ጋርም የተወሰነ ቅርርብ አለዉ ማለትም ለቦታ ስያሜ መነሻ ምክንያቶች ባህል፣ መልከአምድራዊ አቀማመጥ፣ ታሪካዊ አጋጣሚዎች ወዘተ እንደሆኑ የሁለታችንም ዉጤት ነዉ፡፡

የሰሚራ ጥናት እና የእኔ ጥናት ቦታ ስያሜ ላይ ትኩረት ያድርግ እንጅ ከአጠናን ዘዴ፣ ከአላማ፣ አንፃር ሰፊ ልዩነት አለን፡፡ ለምሳሌ እኔ ተከታታይነትና ለውጥን በመፈተሸ የለውጥ ምክንያቶችን፣ የተከታታይነት ምክንያቶች ፣የቦታ ስሞች መነሻ ምክንያቶች እና ፋይዳቸዉን በሚመለከት ትንተና አድርጌያለሁ፡፡ የጥናት ቦታችንም የተለያየ መሆኑ ልዩነት እንዲኖረን አድርጓል፡፡

### 2.2.2. ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረቡ ጥናቶች ዳሰሳ

በዚህ ስር ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረቡ ሁለት ጥናቶች ላይ ቅኝት በማድረግ እንደሚከተለዉ ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

በመጀመሪያ በጥሩአለም ስማቸዉ ማንነት በእነብሴ ሳርምድር ወረዳ የቦታ ስያሜ ዉስጥ ለፎክሎር ትምህርት ክፍል 2012 ዓ.ም የተሰራ ጥናት ተዳሷል፡፡ የዚህ ጥናት ዋና አላማ በእነብሴ ሳርምድር ወረዳ በሚገኙ ቀበሌዎች የቦታ ስያሜ መነሻ ቃል ትረካዎች የማህበረሰቡን ማንነት በመግለፅ በኩል ያላቸዉ ፋይዳ እና የስያሜዎች አሰጣጥ ስነቃላዊ ተስተላልፎ መነሻ ምክኒያቶች ምን ምን እንደሆኑ መመርመር ሲሆን፤ የቦታ ስሞች የማህበረሰቡን ማንነት በመግለፅ ረገድ ምን ጠቀሜታ እንዳላቸዉ ማሳየት፣ የቦታ ስሞችን እና የስያሜ ምክኒያቶች ምን ምን እሳቤዎችን መነሻ እንዳደረጉ መመርመር እና ማህበረሰቡ የሚያወጣቸዉ የቦታ ስሞችና የስያሜ ምክኒያቶች ገፅታን ለሌሎች ለማስተዋወቅ ፋይዳቸዉ ምን ያህል ነዉ የሚሉ ንኡሳን አላማዎችን አንስታለች፡፡ ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅ እና ሰነድ ፍተሻን በመጠቀም መረጃዎቿን ሰብስባለች፡፡ የተሰበሰቡትን መረጃዎች ማህበራዊ ማንነት ትዉር እና ተግባራዊ ትዉርን በመጠቀም ይዘታዊና ገላጭ በሆነ የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች ተጠቅማ መረጃዎቿን ተንትናለች፡፡

ጥሩአለም ከጥናቷ ማደማደሚያ የስያሜ መነሻ ምክኒያቶች ሀይማኖታዊ ተረኮች መሆናቸዉን አረጋግጣለች። አብርሃ ወአጽብሃ እና ሊቀጳጳስ አባ ሰላማ የኦርቶዶክስ ክርስትና ሀይማኖት ትምህርት ለህዝቡ ለማድረስ በተለይም ከክርስቶስ መወለድ በኋላ የሀዲስ ኪዳንን የክርስትና አስተምህሮት ለማስፋፋት ባደረጉት እንቅስቃሴ በወረዳዉ በርከት ያሉ ቦታዎች ስያሜያቸዉን እንዲያገኙ መነሻ መሆናቸዉን አሳይታለች። ሌላዉ ማህበረሰቡ በወቅቱ ያጋጥሙት የነበሩ ማህበራዊ ገጠመኞች እና ታሪካዊ ክስተቶች በወረዳዉ ለሚገኙ አንዳንድ የቦታ ስያሜዎች መነሻ ምክንያቶች እንደሆኑ አመላክታለች። ታሪካዊ ክስተቶች ከትዉልድ ወደ ትዉልድ እንዲተላለፉ እንዳይረሱ እና ነባሩን ማህበረሰብ ማንነቱን እንዲያስታዉሱት ለቦታዎች ስያሜዎችን እየሰጠ በቃል ትረካ አማካኝነት ራሱን ለሌሎች በማስተዋወቅ እንደሚያልፍ በጥናቷ አረጋግጣለች።

የእኔና የጥሩ አለም ጥናት ከሞላ ጎደል የሚያመሳስለዉ የቦታ ስያሜ ላይ ትኩረት ማድረጉ፣ገላጭ የምርምር ዘዴን በመጠቀም መረጃን መተንተናችን፣ ምልከታ፣ ቃለመጠይቅ እና ሰነድ ፍተሻን ለመረጃ መሰብሰቢያነት ማዋላችን ነዉ። በተጨማሪም ከጥናቱ ዉጤት አንፃር ለቦታ ስያሜ መነሻ ምክንያቶች ሀይማኖት፣ ታሪካዊ ክስተቶች፣ ማህበራዊ ገጠመኞች ወዘተ መሆናቸዉን ማረጋገጣችን ያመሳስለናል።

ጥናታችን የቦታ ስያሜ ላይ ትኩረት ያድርግ እንጂ ፤ ብዙ ልዩነቶች አሉን። ጥሩአለም ማንነት በቦታ ስያሜ ዉስጥ ዋና አላማ አድርጋ የተነሳች ሲሆን የእኔ ጥናት ተከታታይነትና ለውጥ በቦታ ስያሜ ላይ ትኩረት አድርጓል። ከቦታ አንፃርም ልዩነት አለን። በተጨማሪም ጥሩ አለም በመረጠቻቸዉ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የሰበሰበቻቸዉን መረጃዎች የቦታ ስሞች ከሰዎች ሀይማኖታዊ እይታ ፣ ማህበራዊ እንቅስቃሴና ከታሪካዊ ክስተቶች ጋር ያላቸዉን ቁርኝት ለመለየት በማህበራዊ ማንነት ትዉር እና ተረኮች የማህበረሰቡን ማንነት በማጉላት በኩል ያላቸዉን ፋይዳ ለመመርመር ተግባራዊ ትዉርን በመጠቀም መረጃዎችን ተንትናለች። የእኔ ጥናት መረጃዎች የተተነተኑት ጠቀሜታዊ እና ስነፍቻዊ ንድፈ ሀሳብን በመጠቀም ነዉ።

የጥሩአለም ጥናት ላይ ያገኘሁት ጠንካራ ጎን ለመረጃ መተንተኛ የተጠቀመቻቸዉ ንድፈ ሀሳቦች ተገቢ መሆናቸዉ ሲሆን እንደ ክፍተት ያየሁት ደግሞ የቦታ ስያሜ ለዉጥን በተመለከተ ትንተና ያደረገችበት ክፍል ላይ የቦታ ስሞች ማን ወደ ማን

ተቀየረ የሚለዉን አስቀምጣ ከማለፍ ባሻገር ለእያንዳንዱ የስያሜ ለውጥ መነሻ ምክኒያት በዝርዝር አለማቅረቧ ነዉ፡፡ የእኔ ጥናት ደግሞ ይህንን ክፍተት ይሞላል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ የሙሉ አየለ የቦታ ስያሜዎችና የማህበረሰቡ ማንነት ትስስር በሁለት እጁ እነሴ ወረዳ 2011 ዓ.ም ለፎክሎር ትምህርት ክፍል የተሰራ ጥናት ነዉ፡፡

የሙሉ ጥናት ዋና አላማ የቦታ ስያሜዎች ከማህበረሰቡ ማንነት ጋር ያላቸዉ ትስስር መመርመር ሲሆን፤ የማህበረሰቡን ማንነት ከቦታዎች ስያሜ ጋር ያለዉን ተዛምዶ መፈተሽ፣ የቦታ ስሞቹ አሰያየም ጥንታዊ አመጣጥ መግለጽ እና የቦታ ስያሜዎቹ ለውጥ እና የማህበረሰቡን ስሜት መመርመር የሚሉ ንኡሳን አላማዎችን አካታለች፡፡ ለጥናቱ ግብአት የሚሆኑ መረጃዎች በቃለ መጠይቅና ከመዛግብት ሰብስባለች፡፡ ጥናቱ አይነታዊ የጥናት ዘርፍ ሲሆን መዋቅራዊ ንድፈ ሀሳብን በመጠቀም መረጃዎቹን በፍካሬያዊና በትረካ መልክ ተተንትነዉ ቀርበዋል፡፡ በጥናቱ ግኝት እንዳረጋገጠችዉ የቦታ ስያሜዎች የስያሜ ምንጮቻቸዉ ትርጉምና ድርጊት መሆኑን አመላክታለች፡፡

የቦታ ስሞች የአካባቢዉ ማህበረሰብ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ሀይማኖታዊ እሴቶች የተገለፁ መሆኑን በመግለፅ ለእሴቶቹ መፈጠር የጀርባ አጥንት የሆኑ እንደ ጥልቅ እምነት፣ አልሞት ባይ ተጋዳይት፣ ችግር የማይበግረዉ ጥንካሬና ለራስ በራስ ፍርድ መስጠት የሚሉ ርእሰ ጉዳዩች በጥናቱ አረጋግጣለች፡፡ በተጨማሪም የማህበረሰቡን ጥልቅ እምነት የሚያሳዩ የቦታ ስሞች መካከል አይጠፋ ዘር፣ አጋምዉሃ፣ ድመት ገደልና የመሬት የሚሉ ስሞች፤ የማህበረሰቡን አልሞት ባይ ተጋዳይነት የሚያሳይ ስላሴ ገዳም እንዲሁም ለራስ በራስ የተሰጠ ፍርድ መቃ ማሪያም በሚለዉ የቦታ ስያሜ እና ችግር የማይበግረዉ ጠንካራ ማህበረሰብ መኖሩን ደግሞ አንሸባራ በሚለዉ ስያሜ ዉስጥ አመላክታለች፡፡ ለጥናቱ በተመረጠዉ ወረዳ አብዛኛዎቹ የቦታ (የቀበሌ) ስሞች በአዳዲስ ስያሜ መለወጣቸዉ እና የለውጣቸዉ ምክኒያት ደግሞ መንግስት ለአሰራር ያመቻል ያለዉን አዲስ የቀበሌ መዋቅር በመዘርጋቱ መሆኑን ጠቁማለች፡፡ በቦታ ስያሜ ለውጥ ማህበረሰቡ በቦታ ስሞች ዉስጥ ያከማቻቸዉ ዘርፈ ብዙ እሴቶች ህልዉና አደጋ ላይ የሚጥል በመሆኑ በአብዛሃኛዉ ማህበረሰብ ዘንድ ተቀባይነት ያጣ መሆኑን በጥናቱ አረጋግጣለች፡፡

የሙሉ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለዉ በቦታ ስያሜ ላይ ትኩረት ማድረጉ እና የቦታ ስያሜ ለውጥ የሁለቱም ጥናቶች አንዱ አላማ መሆኑ ነዉ፡፡

ይህ ጥናት ከሙሉ የሚለየዉ ተከታታይነትና ለውጥ ላይ ትኩረት በማድረጉ፣ ገላጭ የመረጃ መተንተኛን ዘዴ በመጠቀም መረጃዎቹ ጠቀሜታዊ ንድፈሀሳብ እና ስነፍቻዊ ንድፈሀሳብን መሰረት በማድረግ ትንተና ማካሄዱ ነው፡፡ በተጨማሪም ጥናቱ በተካሄደባቸው ቦታዎች መሰረታዊ ልዩነት አለ፡፡

ከጥናት ዉጤት አንፃር የሙሉ ጥናት ዉጤት የቦታ ስያሜ ለዉጥን በተመለከተ የቦታ (የቀበሌ) ስሞች በአዳዲስ ስያሜ መለወጣቸዉ እና የለውጣቸዉ ምክንያት ደግሞ መንግስት ለአሰራር ያመቻል ያለዉን አዲስ የቀበሌ መዋቅር በመዘርጋቱ እንደሆነ አሳይታለች፡፡ የእኔ የጥናት ዉጤት ደግሞ የቦታ ስሞች የለውጥ ምክንያቶች ፖለቲካዊ ሁኔታ፣ የሀይማኖት ተቋማት መስፋፋት፣ የማህበረሰቡ ገጠመኝ፣ የመሰረተ ልማት መስፋፋት እና የንግድ እንቅስቃሴ መስፋፋት መሆናቸው ልዩነት እንዲኖር አድርጓል፡፡

## 2.3. **ንድፈ ሀሳባዊ ማዕቀፍ** (Theoretical Fram works)

አንድን የፎክሎር ጥናት ለማጥናት መረጃዎችን ከመሰብሰብ እስከ መተንተን ባለው ሂደት ውስጥ የተለያዩ ደረጃዎችን ያልፋል፡፡ በዚህም ሂደት የተሰበሰበውን መረጃ በመለየት፣በመመደብና በመተርጎም ሂደት ዉስጥ እንደ ጥናቱ ርእሰ ጉዳይ ዓላማ ተስማሚ እና ምቹ የሆነ ንድፈ ሀሳብ መምረጥ ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም በዚህ ጥናት ውስጥ የተሰበሰቡ ልዩ ልዩ መረጃዎች ከተግባራዊ እና ስነ-ፍቻዊ ንድፈ ሀሳቦች አንጻር ተተንትነዋል፡፡

### 2.3.1. **ጠቀሜታዊነት ንድፈ ሀሳብ**

ጠቀሜታዊነት ንድፈሀሳብ የሚከወነው ፎክሎራዊ ጉዳይ ለማህበረሰቡ የሚኖረውን ፋይዳ የሚመለከት ነው፡፡ ፎክሎርና የፎክሎር ትርጉም ከሰው ጋር የተሳሰረ መሆኑንና ፎክሎር የማስተማር፣ የማዝናናት እንዲሁም ማህበረሰቡ የተገነባበት ባህላዊ ማንነቱ ህልውናው ተጠብቆ እንዲዘልቅ አድርጎ የማስተላለፍ ጠቀሜታ እንዳለው Bascom (1954:346) ያስረዳሉ፡፡ ከዚያም በላይ የጠቀሜታዊነት ንድፈ ሃሳብ እሳቤን ማወቅ አንድ የሰዎች ቡድን በአንድ ውስን ሁነትና ውስን ክዋኔ ውስጥ ምን እየሰራ እንደሆነ ለመረዳት ያግዛል፡፡ ጠቀሜታዊነት ንድፈ ሃሳብ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የሚከወን ማንኛውም ነገር ያለውን ተግባርና አገልግሎት ለመመርመር ይረዳል (Okpewho, 1992,173)::

ሰሎሞን (2011፣75) የጠቀሜታዊነት የፎክሎር ንድፈ ሀሳብ በአንድ ማህበረሰብ ወይም ፎክ ቡድን ዉስጥ ያሉ የተለያዩ ሎሮች ለማህበረሰቡ ወይም ፎክ ቡድኑ

የሚሰጡትን ጠቀሜታና በቡድኑ ዉስጥ ያላቸዉን አዉዳዊ ትርጓሜ በማሳየት ላይ ትኩረት የሚያደርግ ነዉ በማለት ያስረዳሉ።የዚህ ንድፈ ሀሳብ አራማጆችም ተረቶች፣ ሚቶች፣ ምሳሌያዊ አነጋገሮች፣ እምነቶችና ሎሎቹም ማናኛዉም ሎሮች ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያሚ፣ ፖለቲካዊ፣ ባህላዊ፣ ስነልቡናዊ ወይም ሌላ ጥቅም መስጠትና የማህበረሰቡን ፍላጎት ሚሟላት ይኖርባቸዋል የሚል አስተሳሰብ የሚያራምዱ ሲሆን፣ ፎክሎር በማህበረሰቡ ዉስጥ ምን አይነት ትርጓሜና ጠቀሜታ አለዉ የሚለዉ አብይ ጥያቄያቸዉ ነዉ በማለት ያብራራሉ።

ሶስት አይነት የጠቀሜታዊነት አስተሳሰቦች አሉ። የመጀመሪያዉ የብሮኒስላዉ ማሊኖስኪ ንድፈ ሀሳብ ሲሆን የሰዉን ልጅ ስነልቦናዊና ስነ ህይወታዊ ተግባራትን ከግለሰቦች መሰረታዊ ፍላጎቶችና እርካታዎች በመነሳት የፎክሎሩን ሚና የሚመረምር ነዉ በማለት ሀሳቡን ያራምዳሉ። ሁለተኛዉ አስተሳሰብ የራድክሊፍ ብራዉን ንደፈሀሳብ ሲሆን በቡድን ዉስጥ ያሉ ማህበራዊ መዋቅሮች ባላቸዉ ጠቀሜታና ሚና ላይ ትኩረት ያደርጋል። ሶስተኛዉ የኤሚል ድርካሂምና የማርሴል ማኡስ አስተሳሰብ የሆነዉ የሰዉ ልጅ አእምሮ መዋቅር ባለዉ ንቃተ ህሊናዊ አያያዥ አማካኝነት ለማህበራዊ ትስስር ወይም ጥምረት እና ለባህላዊ ክበብ የሚሰጠዉን ጠቀሜታ የሚገልፅ ነዉ። ለዚህ ጥናት የራድክሊፍ ብራዉን አስተሳሰብ ጥቅም ላይ በማዋል የቦታ ስሞቹ ተከታታይነትና ለውጥ ለማህበረሰቡ ያለውን ፋይዳ ለመመርመር ከላይ የተጠቀሰዉ ንድፈ ሀሳብ ተግባራዊ ተደርጓል።

### 2.3.2. ስነ ፍቻዊ ንድፈ ሀሳብ

በአንድ ማህበረሰብ ባህል ውስጥ አንዱ ነገር ሌላውን ወክሎ ስለሚቆም ተምሳሌታዊ የሆኑ ጉዳዮችን ፈልጎ ማግኘት የዚህ ንድፈ ሃሳብ መነሻ ነው። Posner (2004, 56) እንደሚገልጹት "ስነፍች ስለ ምልክቶች የሚያጠና ሳይንስ ሲሆን ምልክቶቹም የሆነ ጉዳይን ወክለው በመቆም አንዳች መልዕክትን ማስተላለፍ የሚጠበቅባቸው ናቸው"። በማለት በባህል ነክ ጥናቶች ውስጥ ስነ ፍችን ስንጠቀም የተወሰኑ ምልክታዊ ስርዓቶችን ትዕምርታዊ ቅርጽ እና ማህበረሰቡ በባህሉ ውስጥ ያበጃቸውን ተምሳሌታዊ ጉዳዮች ፈልፍሎ በማውጣት መግለጽ ተገቢ እንደሆነ ያስረዳሉ።

Frank proschan (1997, 760) "የስነ ፍቻዊ ንድፈ ሀሳብና የፎክሎር ጥናት እርስ በርስ የሚደጋገፉና ተዛማጅነት ያላቸዉ የማህበረሰቡን ተግባቦታዊ እይታዎች የሚገልፁ ናቸዉ" በማለት ይገልፃሉ። በተጨማሪም Danesi (2004, 12) የስነ ፍች

ንድፈ ሀሳብ ከፎክሎር ጋር የጠበቀ ትስስር እንዳለዉ በመግለፅ የፍች አሰጣጥን፣ ቁሶችን ትዕምርታዊ ፍች፣ ድርጊቶችን፣ አካላዊ እንቅስቃሴዎችን፣ የአሰያየም አይነቶችን፣ ጥቆማዎችን፣ ዘይቤያዊ አጠቃቀምን የሚያመለክት ነዉ በማለት ይገልፃሉ።

በመሆኑም በዚህ ጥናት ስነ ፍቻዊ ንድፈ ሃሳብ በአጋዥነት አገልግሎት ላይ ይውላል። ምክንያቱ ደግሞ ማህበረሰቡ የሚሰጣቸዉ የቦታ ስያሜዎች የራሱ የሆነ ዉክልና ስላላቸዉ ስያሜዎቹ በማህበረሰቡ ዘንድ ያላቸውን ውክልና ለመተንተን ነው።

# ምዕራፍ ሶስት፡- የአጠናን ዘዴ

ይህ ምዕራፍ የምርምሩ አይነትና የጥናት ንድፍ፣ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች፣ የናሙና አመራረጥ ዘዴ፣ የመረጃ አተናተን ዘዴ፣ የመስክ ተሞክሮ፣ በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ ሀሳቦችን በተመለከተ ገለፃ የተደረገበት ነዉ፡፡

## 3.1. የምርምሩ አይነትና የጥናት ንድፍ (Research Type & Design)

ይህ ጥናት በአይነቱ ከዓይነታዊ (Qualitative) የምርምር ዘዴ ይመደባል፤ የባህል ጥናት ዘርፍ የሆነውን የቦታ ስያሜ የሚመረምር በመሆኑም ከዓይነታዊ ምርምር የሚመደበው ገላጭ (Descriptive) ሊባል ይችላል፡፡ ለዚህም በምክንያትነት ከሚጠቀሱት አንዱ የጥናቱን ዓላማዎች መሳካት/አለመሳካት ለመፈተሽ የሚሰበሰቡት መረጃዎች በመጠን ወይም በአሃዝ የሚገለጹ ሳይሆኑ ዓይነታዊና ትረካዊ መሆናቸው ነው፡፡ ይህን አስመልክቶ ያለዉ (1998) "ተመራማሪዉ ለማጥናት የፈለገዉ ጉዳይ በመጠን ሳይሆን በአይነት የሚገለፅ ይሆናል፡፡ ስለዚህ በአይነታዊ ምርምር ተመራማሪዉ የሚያጠናቸዉ ጉዳዮች ሁሉ በመጠን ይህን ያህል ማለት ሳይሆን መረጃዎቹን ተንትኖ የጥናቱን ዉጤት ለአንባቢ የሚያቀርበዉ ትረካዊ ወይም ገለፃዊ በሆነ መንገድ ነው‘ በማለት ይገልፃሉ፡፡ ዓይነታዊ የምርምር ዘዴ ኢመጠናዊ መረጃዎች ተሰብስበው በገለጻና በትረካ የሚተነተኑበት ነው፡፡ ይህም ለዚህ ጥናት ገላጭ (Descriptive) የጥናት ንድፍ አገልግሎት ላይ መዋሉን ያመላክታል፡፡

## 3.2. ተጠኝዎች

የጥናቱ አካላይ ወይም ተጠኚ በደሴ ከተማ አስተዳደር ስር ለሚገኙ ክፍለ ከተሞች፣ ቀበሌዎችና ሰፈሮች የተሰጡ መጠሪያ ስሞች ናቸው፡፡ የደሴ ከተማ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ራሱን የቻለ የመስተዳድር አካል ቢሆንም የደቡብ ወሎ ዞን ዋና ከተማነቱንም እንደያዘ ይገኛል፡፡ ይህን ተከትሎ የነዋሪው ህዝብ ቁጥር እየጨመረ፣ ከተማው እየሰፋ በመምጣቱ በዙሪያው የሚገኙ የገጠር መንደሮች በመዋቅር ደረጃ በከተማ አስተዳደሩ ስር እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡ ይሁን እንጂ አስፈለጊ የመሰረተ ልማት አውታሮች፤ መብራት፣ ውሃ፣ ስልክ፣ መንገድ ወዘተ. ባለመዘርጋታቸው መንደሮቹ እስካሁንም በነበሩባቸው የገጠር ቀበሌዎች (በገበሬ ማህበራት) ስር እንዲቆዩ ተደርገዋል፤ በዚህም ምክንያት ስለእነዚህ መንደሮች አስፈላጊው የሰነድ መረጃ ላይገኝ ስለሚችል በዚህ ጥናት አልተካተቱም፡፡

ከገጠር መንደሮቹ በስተቀር በከተማ አስተዳደሩ ስር የሚገኙትና በስፋት በህዝቡ ዘንድ የሚታወቁት የክፍለ ከተማ፣ የቀበሌና የመንደር ስሞች በተጠኚነት ተመርጠዋል፤ ከተሰበሰቡት የቦታ ስሞች መካከል ተከታታይታቸዉን ጠብቀዉ የሚገኙትንም ሆነ የተለወጡ ስሞችን በእጣ ንሙና በመምረጥ በመረጃ ትንተናው ሲካተቱ ቀሪዎቹ በአባሪነት ተይዘዋል፡፡

## 3.3. የናሙና አመራረጥ ዘዴ

የናሙና ምርጫ የተካሄደው በሁለት የጥናቱ ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ነው፤ የመጀመሪያው ተጠኚዎቹን የቦታ ስሞች ሲሆን ሁለተኛው ተሳታፊዎችን (መረጃ አቀባዮችን) ለመምረጥ ነው፡፡ ከቦታ አኳያ ጥናቱ በአማራ ክልል ደቡብ ወሎ ዞን ስር በሚገኘው ደሴ ከተማ አስተዳደር የተካሄደ መሆኑ ቀደም ሲል ተገልጿል፡፡ በአዲስ መዋቅር በከተማ አስተዳደሩ ስር የተካተቱትንና ገና የከተማ አስተዳደር መዋቅር ያልተዘረጋላቸውን መንደሮች በመተው የከተማው ነባር ክፍለ ከተማዎች፣ ቀበሌዎችና መንደሮች በጠቅላይ ንሞን ዘዴ በጥናቱ ተካትተዋል፡፡ ይሁን እንጅ በተለይም ተከታታይነትን ጠብቀዉ የዘለቁት የቦታ ስሞች በርካታ በመሆናቸዉ፣ ሁሉንም በትንተናዉ ማካተት በጥናቱ መጠነ ርዕይ ላይ ከሚኖረው ተጽእኖና ለውጥ ከተካሄደባቸው መረጃዎች አንጻራዊ ውስንነት አኳያ ተመጣጣኝነትን ለመጠበቅ በማሰብ የተወሰኑት በእጣ ተመርጠዉ በትንተናው ተካትተዋል፡፡

በዚህ ጥናት በመረጃ አቀባይነት የተሳተፉት ሰዎች ለመምረጥ ጠቋሚ ወይም አመልካች የናሙና አመራረጥ ዘዴ (Snow ball Sampling) ተግባራዊ ሆኗል፡፡ ይህ ዘዴ በሚጠናው ጉዳይ ዙሪያ ከአንድ ሰው ወይም ቡድን መረጃዎችን በመቀበል፤ እርሱ ደግሞ ሌላውን እንዲጠቁም የሚደረግበት እና የጥቆማ ሂደቱም በቂ መረጃ እስከሚገኝ ድረስ የሚቀጥልበት ነው (ያለው 2009፡137-138)፡፡ በዚህ ጥናትም ይህ ዘዴ ተግባራዊ የተደረገበት ምክንያት ሁሉም መረጃ በአንዴ ከአንድ ሰው ወይም ቡድን የሚገኝበት ሁኔታ ባለመኖሩ አንዱ ያወቀውን መረጃ በመቀበል እና እሱ የሚያውቃቸውን ሌሎች ሰዎች እንዲጠቁም በማድረግ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ተመራጭ በመሆኑ ነው፡፡ በዚህ መሰረት በተለያዩ አካባቢዎች ታዋቂ ግለሰቦችን በማፈላለግ እና በጉዳዩ ላይ እዉቀት ያላቸዉን ሰዎች እንዲጠቁሙ በማድረግ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

## 3.4. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

ለምርምር ስራ ትክክለኛ እና ተጨባጭ መረጃ ለመሰብሰብ ከሚረዱት መስፈርቶች መካከል አንዱ ተገቢ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ መምረጥ ነው። በመሆኑም ይህን ጥናት ለማካሄድ መረጃዎች ከቀዳማይ (በቀጥታ ከመስክ ከመረጃ ሰጪዎች የሚገኙ) እና ካልዓይ (ከተለያዩ ሰነዶችና ካርታዎች) የመረጃ ምንጮች ተሰብስበዋል።

በካልዓይ የመረጃ ምንጭነት የደሴ ከተማ ቀበሌዎችና ማህበራዊ ቡድኖች በተመለከተ የተጻፉ ሰነዶችን፣ የአስተዳደር መዛግብትን፣ የወረዳና የቀበሌ ወሰኖችን የሚያሳዩ ካርታዎችን በመጠቀም መረጃዎች ተሰብስበዋል። በቀዳማይ ምንጭነት ደግሞ በአስተዳደር ስራ የተሰማሩ ግለሰቦችን፣ በአካባቢው በታሪክ አዋቂነት እውቅና ያላቸው የእድሜ ባለጸጋዎችን በማፈላለግ የጥናቱን ጉዳይ በሚመለከት መረጃዎችን እንዲሰጡ ተደርጓል። ለዚህም የሰነድ ፍተሻ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ቡድን ተኮር ዉይይት እና ምልከታ በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት ጥቅም ላይ ዉለዋል።

ለጥናቱ ከላይ ከተጠቀሱት ምንጮች አስፈላጊውን መረጃ ለመሰብሰብ ቃለመጠይቅ፣ ሰነድ ፍተሻ፣ ምልከታና ቡድን ተኮር ዉይይት ተግባር ላይ ውለዋል።

### 3.4.1. ቃለ መጠይቅ

ቃለ መጠይቅ በፎክሎር የጥናት መስክ በአብዛኛዎች ዘንድ የሚሰራበት እና የተለመደ የመስክ የመረጃ መሰብሰብያ ዘዴ ነው (Goldstein 1964:104)። በተመራማሪውና በመረጃ ሰጪው የፊት ለፊት ግንኙነት የሚከናወን፣ መረጃ ሰጭውን ያልተገደበ መረጃ ለመስጠት፣ ጠያቂው ጣልቃ በመግባት ተጠያቂውን ወደ ዓላማው ለማስገባት ዕድል የሚሰጥ በመሆኑ በተለይ ለመስክ መረጃ አሰባሰብ ተመራጭነቱ የጎላ ነው። ከዚህ ጠቀሜታው አንጻርም ለዚህ ጥናት በዋና መረጃ መሰብሰቢያነት ቃለ መጠይቅ ተመርጧል። ከተለያዩ የቃለ መጠይቅ አይነቶች መካከልም ነፃ ቃለ መጠይቅ ተግባራዊ ሁኗል። ይህም የሆነበት ምክንያት ነጻ ቃለ መጠይቅ መረጃ አቀባዮች ስለ አንድ ጉዳይ ያላቸውን አስተሳሰብ፣ እምነት፣ ግንዛቤ፣ አተያይ ወዘተ ያለማንም አስገዳጅነት በመረጡት ፍስት ነጻ ሆነው እንዲመልሱና በጉዳዩ ዙሪያም የተሻለ መረጃ ለመሰብሰብ ስለሚያስችል ነው።

በባህል ጥናት በመረጃ አቀባይነት ለቃለ መጠይቅ የሚመረጡት ተጠኝዎች በቦታዉ ላይ ረጅም እድሜን ያካበቱ ባህል እና ታሪክ የሚያውቁ እንዲሆኑ ይጠበቃል። በዚህ ጥናትም በቃለ መጠይቅ የሚሳተፉ ሰዎች በተለያዩ መስፈርቶች የተመረጡ ሲሆን

ከመምረጫ መስፈርቶች መካከል በአካባቢው ለረጅም ጊዜ የኖሩና የዕድሜ ባለጸጋ የሆኑ፣ታሪክ የሚያዉቁ ዋና ዋናዎች ናቸው፡፡ይህን መስፈርት ያሟላሉ ተብለዉ በማህበረሰቡ የተጠቆሙ ሀያ አንድ መረጃ ሰጭዎች ማለትም አስራ ስምንት ወንዶች እና ሶስት ሴቶች ተሳትፈዋል፡፡ የቃለ መጠይቅ መረጃዎች ከመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አንጻር በመቅረጸ ድምጽ እና በማስታወሻ ደብተር በመመዝገብ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

## 3.4.2. መዛግብት (ሰነድ) ፍተሻ

በዚህ ጥናት መዛግብት ወይም ሰነድ ፍተሻ በሁለተኛ የመረጃ ምንጭነት ውሏል፡፡ መዛግብት ወይም ሰነድ ፍተሻን የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ የምንለዉ የተለያዩ ሰነዶችን እንደ ደብዳቤዎች፣ ቃለጉባኤዎች፣ አዋጆች ወዘተ በመጠቀም መረጃ የምንሰበስብበት ዘዴ በመሆኑ ነዉ፡፡ ይህን አስመልክቶ ያለዉ (2009፡196-197) 'መዛግብት ተመራማሪዉ ስላለፈም ይሁን ወቅታዊ ጉዳይ መረጃ ለመሰብሰብ ሲነሳ ሊጠቀምባቸዉ የሚችሉ ጠቃሚ ነገሮች ናቸዉ፡፡ መዛግብት በፁሁፍ መልክ ከየቤተመፃህፍቱ፣ ቤተመዛግብቱ፣ ወይም ከሌሎች መሰብሰቢያ ቦታዎችና እንደ ሁኔታዉም ከግለሰቦች ሊገኙ የሚችሉ የመረጃ ምንጮች ናቸዉ፡፡" በማለት ይገልጻሉ፡፡ ለዚህ ጥናትም መረጃዎችን ከመዛግብት ወይም ከሰነዶች ለመሰብሰብ ሰነድ ፍተሻ በመረጃ መሰብሰቢያነት አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡

## 3.4.3. ቡድን ተኮር ዉይይት

በዚህ ጥናት ቡድን ተኮር ውይይት በሶስተኛ ደረጃ ለመረጃ መሰብሰቢያነት ዉሏል፡፡ ይህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ከላይ በተገለጹት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች በአግባቡ ያልተመለሱና አጠራጣሪ የሆኑ ጉዳዮችን አጥጋቢና ዝርዝር መረጃዎችን ፈልፍሎ ለማስገኘት የሚያስችል ስልት ነው፡፡ ይህን አስመልክቶ Lindlof.T. R and Taylor. B.C (2011) አሳታፊ የሆነ ቡድን ዉይይት በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ የተለያዩ ሰዎችን በአንድ ላይ ሰብስቦ በማወያየትና በመጠየቅ የሚከወን ሲሆን የአንድን ማህበረሰብ አመለካከት ወይም ፍልስፍና ለመመርመር የሚያስችል ነዉ በማለት ይገልፃሉ፡፡

ስለሆነም ይህን ጥናት እውን ለማድረግ በተጠቀምኳቸው የመረጃ መሰብስቢያ ዘዴዎች የተገኙትን መረጃዎች ምን ያህል ተዓማኝና ትክክለኛ ናቸው የሚለውን ለማረጋገጥ ወሳኝነት ያለው ዘዴ ነው፡፡ ስለዚህ ሙሉ መረጃዬን ለመሰብሰብ ስለ

ጉዳዩ እውቀት አላቸው የሚባሉትን እና በቦታዉ ላይ ከሀያ አመት በላይ የኖሩና የአካባቢዉ ተወላጅ የሆኑ መረጃ ሰጭዎችን በቡድን በማዋቀር ማለትም 7 አባላት ያሉት ሁለት ቡድን በማደራጀት ተመሳሳይ የሆኑ ጥያቄዎችን እያነሳሁ በማወያየት የቦታ ስያሜ ተከታታይነት፣ የቦታ ስያሜ መነሻ ምክኒያቶች፣ የስያሜ ለውጥ እና የለዉጥ ምክኒያቶች፣ የቦታ ስያሜ ተከታታይነትና ለውጥ ላይ የማህበረሰቡ አመለካከትን በተመለከተ መረጃ ለመሰብሰብ ሞክሬያለሁ፡፡ ሁለቱ ቡድኖች የተዋቀሩበት መስፈርት ከመኖሪያ አካባቢ አኳያ ሲሆን ተቀራራቢ ሰፈር ላይ ያሉትን አንድ ላይ በማድረግ ቡድኑ እንዲመሰረት ሆኗል፡፡

### 3.4.4. ምልከታ

ምልከታ በአይን መመልከትን ብቻ ሳይሆን ጉዳዮቹን እና ሁኔታዎችን በሁሉም የስሜት ህዋሳቶቻችን መከታተልን እና መገንዘብ የሚጨምር ነው፡፡ ይህንንም አስመልክተው Goldstein (1964:77) ‹‹The term observation … is not limited only to visual aspects of the situation, but also involves a full range of sensual experience including hearing, feeling, smelling, and tasting, whenever these may be appropriate.››ይላሉ፡፡ ‹‹ምልከታ የሚለው ቃል የሁኔታዎች እይታዊ ገጽታዎች ላይ ብቻ የሚገደብ ሳይሆን እንደ መስማት፣ ማሽተት፣ በነገሮች ላይ ያለ ስሜት እና ጣዕም የመሳሰሉትን ስሜታዊ ልምዶችን ጨምሮ ማጤን ተገቢ የሚሆንበት ዘዴ ነው፡፡›› በማለት ምልከታ በእይታ ብቻ የማይወሰን መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

ሆኖም በዚህ ጥናት ማህበረሰቡ ለቦታ ስያሜዎችን ሲሰጥ እንዴት እና በምን ምክኒያት እንደሆነ ለማረጋገጥ ምልከታ የሚያስፈልግበት ሁኔታ በመኖሩ ቦታዉ ላይ በመገኘት ከመመልከት ባሻገር በሁሉም የስሜት ህዋሳቶቹ በመረዳት በኢተሳትፏዊ ምልከታ መረጃዬን ለመሰብሰብ ሙከራ አድርጌያለሁ፡፡ በዚህም ከቦታው አቀማመጥ፣ ተዋሳኝነት፣ ኗሪ መገለጫዎች እንዲሁም ተካታች ነገሮች አንጻር የመነጨ የቦታ ስያሜና ለውጥ ሂደቶችን በምልከታ በመቃኘት ከሌሎች የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች ከተገኙ መረጃዎች ጋር ለማመሳከር እና ለመረጃ አተናተን ግብዓት እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡

## 3.5. የመረጃ አተናን ዘዴ

በምርምር ስራ የመረጃዎች መሰብሰብ ብቻዉን የጥናቱን ጥያቄዎች ለመመለስና የተደረሰበትን ዉጤት ለማግለፅ አያስችልም። መረጃዎች ስለተሰበሰቡም በቀጥታ ወደ ትንተና መግባት የዓላማን መሳካት አያመለክትም። መረጃዎቹን ከመተንተን በፊት የቅድመ ትንተና ተግባራትን ማካሄድ መሰረታዊ ጉዳይ ነዉ። በዚህም መሰረት በዚህ ጥናት የተሰበሰቡትን መረጃዎች የመምረጥ፣ በአይነታቸዉ የመመደብና በጥናቱ ዓላማዎች (ጥያቄዎች) መሰረት በቅደም ተከተል የማደራጀትና የማጣራት ተግባራት ተከናዉነዋል።

ጥናቱ በአንድ በኩል የተጠኘዉን መልከዓምድራዊ አካባቢዎች ስያሜ አሰጣጥና የስያሜዉን ምክንያቶች፤ በሌላ በኩል የስሞቹን ተከታታይነትና ለውጥ፤ በዚህ ስርም ስነልሳናዊ፣ ማህበራዊ፣ ርእዮተአለማዊና ባህላዊ ፋይዳቸዉን መሰረት ያደረገ ነዉ። በመሆኑም የቦታ ስሞች ተከታታይነትና ለውጥ የሚሉትን አላማዎች መሪ በማድረግና ማህበራዊ፣ ስነልሳናዊ፣ ባህላዊና ርዕዮተአለማዊ ፋይዳዎቻቸዉን በማስከተል መረጃዎች በገላጭ ወይም ትረካዊ የመተንተኛ ዘዴ ተተንትነዋል።

ገላጭ ወይም ትረካዊ የመተንተኛ ዘዴን ለጥናቱ ተመራጭ ያደረገው የተሰበሰቡት መረጃዎች መጠናዊ ሳይሆኑ ዓይነታዊና በቋንቋ የሚገለጹ መሆናቸው ነው። የመረጃ ትንተናውን ተከትሎም ዉጤት የመተርጎም፣ የማብራራትና የማጠቃለል ተግባራት ተከናዉነዋል።

## 3.6. የመስክ ተሞክሮ

ይህ ጥናት የተደረገዉ በደቡብ ወሎ ዉስጥ ከሚገኙ ከተሞች አንዷ በሆነችዉ ደሴ ከተማ ነዉ። በመሆኑም በ2013 ዓ.ም የአመቱን ሴሚስተር አጋማሽ በመጨረሴ ከባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፎክሎር ትምህርት ክፍል ጥናቴን ወደማደርግበት አካባቢ ማለትም ለደሴ ከተማ አስተዳደር ፅ/ቤት የድጋፍ ደብዳቤ አጻፍኩኝ። በቀን 25/06/2013 ከባህር ዳር ወደ ደሴ ከተማ ጉዞ አደረኩኝ። ደሴ ከተማ እንደደረስኩም ከዩኒቨርሲቲዉ የተፃፈልኝን የድጋፍ ደብዳቤ በመያዝ ወደ ደሴ ከተማ ከንቲባ ፅ/ቤት አመራሁ። ደብዳቤዉን ለፅ/ቤቱ ከንቲባ ፅ/ቤት ሀላፊ ለሆኑት ለአቶ ሰይድ እሸቱ ሰጠሁ። በመቀጠልም ከንቲባ ፅ/ቤት ሀላፊዉ ምን እንደሚረዱኝ ጠየቁኝ እኔም ለደሴ ከተማ ባህልና ቱሪዝም፣ ለደሴ ከተማ መንግስት ኮሚኒኬሽን ጽ/ቤት እና ለሰኞ ገበያ ክፍለ ከተማ የትብብር ደብዳቤ እንዲፅፉልኝ ጠየኩ። በጠየኩት መሰረት ደብዳቤዉ

ተዘጋጅቶ ተሰጠኝ። ደብዳቤየን ይዤ ወደ ደሴ ከተማ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ አመራሁ። ከዚህ ቀደም ለዶክመንተሽን እና አርካይቪንግ ኮርስ ማሟያ የሚሆን አሳይመንት ለመስራት ወደ ቢሮዉ ሂጄ ስለነበር ከሀላፊዉ ጀምሮ እስከ ባለሙያዎቹ ትዉዉቅ አድርጌ ስለነበር በሚገባ ነበር ያስተናገዱኝ። ከንቲባ ጽ/ቤቱ የሰጠኝን ደብዳቤ ለፅ/ቤቱ ቡድን መሪ ለሆኑት ለአቶ ገዛኸኝ አበራ ሰጠሁ። ስለሄድኩበት ጉዳይም በደንብ አወራን። አቶ ገዛኸኝ ከፅ/ቤቱ ባለሙያዎች ጋር ማለትም ከአቶ መረሳ እና ከአቶ ፀጋ ጋር በድጋሜ አስተዋወቁኝ። አቶ መረሳም ለምፈልገዉ ማንኛዉም ጉዳይ መረጃ በመስጠት ሊተባበረኝ እንደሚችል በደስታ ነገረኝ። ወዲያዉም ቢሮዉ ዉስጥ አሉ የተባሉትን የተለያዩ መፅሄቶችና ብሮሽሮች ሰጠኝ። የደሴ ከተማ ባህልና ቱሪዝም ሰራተኞች መልካምነት ዉስጤን አስደሰተዉ ለሁለተኛ ጊዜ ስለተገናኘንም ልክ እንደ ጓደኞች ሆንን። የአቶ መረሳን እና የአቶ ገዛኸኝን ስልክ ቁጥር ተቀብየ ለመልካም ትብብራቸዉም አመስግኜ ተለያየን።

በማግስቱ ለክፍለ ከተሞች የተፃፈልኝን ደብዳቤ ይዤ ወደ ሰኞ ገበያ ክፍለ ከተማ አመራሁ። አጋጣሚ ይህ ክፍለ ከተማ እኔ የምሰራበት ቦታ በመሆኑ አዲስ አልሆነብኝም። ደብዳቤዉንም ለክፍለ ከተማዉ አስተዳደር ዋና ስራ አስፈፃሚ ለሆኑት ለአቶ አህመድ ሰጠሁ። ሀላፊዉም የምፈልገዉን ሁሉ መጠየቅ እንደምችል እና በማንኛዉም ሁኔታ ሊተባበሩኝ እንደሚፈልጉ ነገሩኝ። ከዛም ወቅቱ ትንሽ ግርግር ወይም ጦርነት የነበረበት ጊዜ በመሆኑ ለሚመለከተዉ አካል ሁሉ የሚል ደብዳቤ በመፃፍ ሰላማዊ ነዋሪ መሆኔ እና ለምርምር ስራየ የሚሆኑ መረጃ ለማግኜት በምሄድበት ቦታ ሁሉ ትብብር ይደረግላት የሚል ደብዳቤ አዘጋጂተዉ ሰጡኝ። ከዛም የክፍለ ከተማዉ አስተዳደር ፅ/ቤት ሀላፊ የሆኑት ከአቶ መኮነን አስፋዉ ጋር አገናኙኝ። አቶ መኮነን አስፋዉ ለጥናቱ የሚያስፈልገኝን ጠየቁኝ እኔም በክፍለ ከተማዉ ዉስጥ ስለሚኖሩ ታሪክ አዋቂ እና ታላላቅ ሰዎች ያዉቁ እንደሆን ጠየኩ። አቶ መኮነንም ለጊዜዉ በወቅታዊ ስራ እንደተጠመዱ በመንገር ከሳምንት በኋላ ግን የሚያዉቃቸዉ ሰዎች ጋር እንደሚወስዱኝ ቃል ገብተዉልኝ ስልክ ቁጥራቸዉንም ተቀብየ በማመስገን ተለያየን።

በቀን 8/07/2013 በደሴ ከተማ የመንግስት ኮሚኒኬሽን ቢሮ አመራሁ። እዛም እንደደረስኩ የደሴ ከተማ መንግስት ኮሚኒኬሽን አይሲቲ ባለሙያ ከሆኑት ከ/ሮ አልማዝ ገ/መስቀል ጋር ተገናኘን የያዝኩትን ደብዳቤ በመስጠት ስለምፈልገዉ ጉዳይ ሁሉ አወራን ከዛም አሉ የተባሉ መረጃዎችን በፍላሽ በመስጠት ቀሪ መረጃዎችን

ደግሞ ፕላን እና ኮሚሽን ቢሮ እንደሚሰጡኝ በመንገር እኔም ስለትብብራቸዉ አመስግኜ ተለያየን፡፡ በዚሁ ቀን ፕላንና ኮሚሽን ቢሮ በመግባት ስለ ደሴ ከተማ መረጃ እንደምፈልግ በመንገር የተለያዩ መፅሄቶችን ተቀብየ በማመስገን ወጣሁ፡፡

ለአቶ መረሳ ስልክ በመደወል ይመቸዉ እንደሆነ ጠይቄ ተገናኘን፡፡ ደሴ ላይ ለረጅም ጊዜ የኖሩ እና ስለ ከተማዋ መረጃ ያዉቃሉ ከሚባሉት ሰዎች መካከል የተወሰኑትን ነግሮኝ ተለያየን፡፡ በመቀጠልም ስለተሰጡኝ መረጃ ሰጭዎቼ ማጠያየቅ ስጀምር አቶ አህመድ እብራሂም የተባለ የከተማዋ ነዋሪ የምፈልጋቸዉን መረጃ ሰጭዎች እንደሚያዉቃቸዉ እና ቤታቸዉንም እንደሚያዉቀዉ ነገረኝ፡፡ ከዛም እለተ ቅዳሜ ጧት ላይ አብረን በመሄድ ከአቶ ተፈራ መላኩ ጋር አስተዋወቀኝ፡፡ መረጃ ሰጭየ ጋር በደንብ ከተዋወቅን በኋላ ስለደሴ ከተማ የቦታ ስያሜዎች ጥናት እንደማደርግ ስነግራቸዉ በጣም ደስ አላቸዉ፡፡ አይዞሽ የማዉቀዉን ሁሉ እነግርሻለሁ እኔ ለሁሉም ነዉ መረጃ የምሰጠዉ ለዶክተር አሰፋ ባልቻ እንኳን ብዙ መረጃ ሰጥቼዋለሁ ያዉ በሬ ያርሳል አህያ ምርቱን ያፍሳል አይደል ነገሩ ብለዉ ረጅም ሳቅ ሳቁ፡፡ ችግሩ ጥናታችሁ ሲያልቅ እኛን ትረሳላችሁ አሉኝ፡፡ እኔም ጥናታችን የተሳካ እንዲሆን የመረጃ ሰጭዎቻችን አስተዋጽኦ ከፍተኛ እንደሆነ እና ጥናታችን መጀመሪያ ገፅ ላይ እንደምናመሰግናቸዉ ስነግራቸዉ ተደሰቱ፡፡ አቶ ተፈራ መላኩ ጋር ለቃለ መጠይቅ ቀጠሮ በመያዝ እና ስለሌሎች መረጃ ሰጭዎች አድራሻ ነግረዉኝ ተለያን፡፡

ከሳምንት በኋላ ከአቶ መኮንን ጋር በመገናኘት ወደ መረጃ ሰጭዎቼ ጋር አመራን እዛ እንደደረስንም ከሸህ ዑመር ሁሴን ጋር ተገናኘን፡፡ ሸህ ዑመር ሁሴን ገራዶ አካባቢ ተወልደዉ ያደጉ ናቸዉ፡፡ ከሸህ ዑመር ጋር ከተዋወቅን በኋላ የመጣሁበትን አላማ በመንገር እንዲተባበሩኝ ጠየኳቸዉ፡፡ እሳቸዉም ሊተባበሩኝ ፈቃደኛ እንደሆኑ ነግረዉኝ ከእሳቸዉ የተሻለ መረጃ የሚያዉቁ ሰዎች እንዳሉ በመንገር አድራሻቸዉን ሰተዉኝ ለቃለ መጠይቅ ቀጠሮ በመያዝ ተለያየን ፡፡ መረጃ ይሰጡኛል ከተባልኳቸዉ ሰዎች ጋር እየተዋወኩ ቀጠሮ አስያዝኩ፡፡ ለቃለ መጠይቅ የሚያስፈልጉ ድምጽ መቅጃ ፣ ፎቶ ግራፍ ማንሻ፣ ማስታወሻ ደብተር እና እስክርቢቶ በመያዝ በቀጠሮየ መሰረት ሁሉም ጋር እየሄድኩ ቃለመጠይቅ በማድረግ መረጃ መሰብሰብ ጀመርኩ፡፡

ከቃለ መጠይቅ ያገኘሁትን መረጃ ለማጠናከር ቡድን በማዋቀር ማለትም አንድ አካባቢ የሆኑትን 7 አባላት ያሉት ቡድን በመመስረት እና ስለ ርእሰ ጉዳዩ የተለያዩ

የመወያያ ጥያቄዎችን እያነሳሁ እንዲወያዩ በማድረግ አስፈላጊዉን መረጃ ለመሰብሰብ ሞክሬያለሁ፡፡

የተለያዩ ተቋማት ዘንድ በመሄድም የተለያዩ መፅሄቶች፣ጋዜጦች፣ብሮሸሮች፣ሰነዶች ወዘተ በመቀበል ልዩ ልዩ መረጃዎችን ሰብስቤያለሁ፡፡

## 3.7. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች

በዚህ ስር ጥናት በማደርግበት ወቅት ያጋጠሙኝ ችግሮች እና ለገጠሙኝ ችግሮች የተወሰዱ መፍትሄዎች ከዚህ በታች ቀርበዋል፡፡

### 3.7.1. ያጋጠሙ ችግሮች

በጥናቴ ወቅት መረጃ ለመሰብሰብ ወደ መስክ በሄድኩበት ጊዜ አንዳንድ ችግሮች ገጥመዉኝ ነበር፡፡ ወቅቱ ሀገር አቀፍ የምርጫ ምዝገባ የሚካሄድበት በመሆኑ እና በሀገራችን አሳሳቢ የሆነዉ የኮሮና በሽታ መስፋፋት አስቸጋሪ ሆኖብኝ ነበር፡፡ በደሴ ከተማ አስተዳደር የተለያዩ ጽ/ቤቶች በምሄድበት ወቅት ብዙ ጊዜ ስብሰባ ላይ መሆናቸዉ ፈተና ሆኖብኝ ነበር፡፡

መረጃ ሰጭዎቼ ጋር በምገናኝበት ወቅት የኮሮናን በሽታ እየፈሩ ከኔ ጋር መቀራረብ የከበዳቸዉ መረጃ ሰጭዎች አጋጥመዉኝ ነበር፡፡

መረጃ በምሰበስብበት ወቅት ርቀቴን ለመጠበቅ በምሞክርበት ወቅት ከመረጃ ሰጭዎቼ ጋር ያለመደማመጥ ችግር አጋጥሞኝ ነበር፡፡

በጦርነቱ ምክኒያት ከሰሜን ወሎ ተፈናቅለዉ የመጡ ዜጎች ደሴ ከተማ ላይ በመብዛታቸዉ እና ማህበረሰቡ ጭንቀት ዉስጥ ስለነበር መረጃ ለመስጠት የመጠራጠር እና የፍርሀት ስሜት ስላደረባቸዉ አስቸጋሪ ሆኖብኝ ነበር፡፡

### 3.7.2. የተወሰዱ መፍትሄዎች

መረጃ እንዲሰጡኝ የምፈልጋቸዉን ሴክተር መስሪያ ቤቶች መቼ እንደማገኛቸዉ እና ስብሰባ በማይኖርበት ወቅት ቀጠሮ እንዲይዙልኝ በማድረግ የምፈልገዉን መረጃ ወስጃለሁ፡፡

ከመረጃ ሰጭዎቼ ጋር በምገናኝበት ወቅት በኔ ላይ እምነት እንዲኖራቸዉ ማስክ በመልበስ እና እጆቼን በሳኒታይዘር በማፅዳት እንዲሁም ርቀቴን ጠብቄ በመቀመጥ አስፈላጊዉን መረጃ ለመሰብሰብ ሞክሬያለሁ፡፡


መረጃ ሰጭዎቹ በተቻላቸዉ መጠን ድምፃቸዉን ከፍ እንዲያደርጉ በመጠየቅ የተፈጠረዉን ክፍተት ለመሙላት ሞክሬያለሁ፡፡

መረጃ ለመሰብሰብ መስክ በምሄድበት ወቅት እንዳልቸገር የሰኞ ገበያ ክፍለ ከተማ የወቅቱን ሁኔታ በማገናዘብ ሰላማዊ ነዋሪ መሆኔን እና ለጥናትና ምርምር መረጃ እየሰበሰብኩ እንደሆነ የሚገልፅ የድጋፍ ደብዳቤ እንዲፅፍልኝ አድርጌያለሁ፡፡ ለመረጃ ሰጭዎቹ የተሰጠኝን የድጋፍ ደብዳቤ እያሳየሁ በእኔ እርግጠኛ እንዲሆኑ በማድረግ መረጃየን በአግባቡ ለመሰብሰብ ሞክሬያለሁ፡፡

በጦርነቱ ምክንያት ያጋጠመኝን የመረጃ ሰጪዎች የመጠራጠር እና የፍርሀት ስሜት ችግር የጥናቱን ዓላማ በግልጽ በማስረዳትና በተሻለ ስሜት መረጃ ሊሰጡ የሚችሉበትን ተለዋጭ ቀጠሮ በማመቻቸት ችግሩ ሊቀረፍ ችሏል፡፡

# ምዕራፍ አራት፡- የደሴ ከተማ አካባቢያዊ ዳራ

በዚህ ምዕራፍ የጠናቱ ተተኳሪ የሆነው የደሴ ከተማ ዳራዊ መግለጫ ቀርቧል፤ በዚህ ገለጻም የደሴ ከተማ አመሰራረት፣ የመሰረተ ልማትና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ፣ የህዝቡ የቋንቋ እና የሀይማኖት ሁኔታ፣ የቱሪዝም መስህቦችና ባህላዊ እሴቶች ሁኔታ በአጭሩ ተቃኝተዋል፡፡




ፎቶ አንድ፡ የደሴ ከተማ ካርታ

ምንጭ፡- የደሴ ከተማ ፕላን ኮሚሽን ቢሮ፡፡

## 4.1. የደሴ ከተማ መልክዓምድራዊ አቀማመጥ

ደሴ ከተማ በአማራ ብሄራዊ ክልል ዉስጥ ከሚገኙ ዋና ዋና ከተሞች አንዷ ስትሆን ከባህር ዳር 480 ኪሎ ሜትር እንዲሁም ከሀገራችን ርዕሰ መዲና አዲስ አበባ ሰሜን አቅጣጫ 400 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ትገኛለች፡፡ በ11°05 ሰሜን ኬክሮስ እና በ39°40 ምስራቅ ኬንትሮስ ከባህር ወለል በላይ በ2470 እና 2250 ከፍታ ላይ በአስደናቂዎቹ የጦሳና የአዝዋ ተራሮች ተከባ በግርጌያቸው ተንጣላ ትታያለች፡፡ የአየር ንብረቷ በአብዛኛዉ ወይና ደጋ ሲሆን፣ ለሰዉ ልጆች መኖሪያ በእጅጉ ተስማሚ ናት፡፡

ከተማዋን በምስራቅ የቃሉ ወረዳና ኮምቦልቻ ከተማ አስተዳደር፣ በስተደቡብ አልብኮና ደሴ ዙሪያ ወረዳዎች ፣ በስተምዕራብ ሰንሰለታማዉ የጦሳ ተራራ እና ደሴ ዙሪያ ወረዳ፣ በስተሰሜን የኩታበር እና ተሁለደሬ ወረዳዎች ያዋስኗታል፡፡ የደሴ ከተማ አስተዳደር ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት መምሪያ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተዉ በ2013 በጀት አመት የከተማና የገጠር ጠቅላላ የህዝብ ብዛት 481442 ይደርሳል፡፡ የቆዳ ስፋቷም የገጠር ቀበሌን ጨምሮ 16800 ሄክታር ነዉ፡፡ ምንጭ፡- ደሴ የፍቅር፣ የዉበትና የጥበብ አምባ ለ7ኛዉ የከተሞች ሳምንት የተዘጋጀ መፅሄት፡፡

## 4.2. የደሴ ከተማ አመሰራረት

በተለያየ ወቅት በጀሜ ተራራ ላይ ቆይታቸዉን ያደረጉ ነገስታትና የነገስታት ቤተሰቦች ለደሴ ከተማ መመስረት ዋነኛ ፈር ቀዳጆች ነበሩ፡፡ በዋነኛነት የሚጠቀሱት ደግሞ ንጉስ ሚካኤል ናቸዉ፡፡ ንጉስ ሚካኤል ወሎን ለማስተዳደር የንግስና ማዕረግ ሲሰጣቸዉ በጀሜ ተራራ ላይ መቀመጫቸዉን አድርገዋል፡፡ እርሳቸዉ ግን ቦታዉን ለጊዜያዊ መቆያ ብቻ ሳይሆን ቋሚ መቀመጫቸዉ በማድረግ ቤተ መንግስታቸዉን እዚያዉ መሰረቱ፡፡ በ1885 ዓ.ም አካባቢ የንግስና ማዕረጋቸዉን የያዙት ንጉስ ሚካኤል ደሴን ዋና መቀመጫ አድርገዉ ሲመርጡ በርካታ ምክንያቶች ነበሯቸዉ፡፡ ከእነዚህ ምክንያቶች መካከልም የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፡፡

- አካባቢዉ ጠላት ሲመጣ በሩቅ ለመቆጣጠር አመች መሆኑ፤
- የዘመኑ የሲራራ ንግድ እንቅስቃሴ መተላለፊያና ዋነኛ ማዕከል መሆኑ፤
- አየሩ ለኑሮ ተስማሚ እና አስፈላጊ የሆኑ የግብርና ምርቶች የሚመረቱበትና በቂ ዉሃ የሚገኝበት መሆኑ፤
- ከተማዋን ዙሪያ ጥምጥም ያቀፏት የጦሳና የአዘዋ ተራሮች አስደሳችና ማራኪነት ብቻ ሳይሆን በስትራቴጂካዊ ምቹነትም አካባቢውን ተመራጭ ሊያደርጉት ችለዋል፡፡

  (ምንጭ፡- ደሴ የፍቅር፣የዉበትና የጥበብ አምባ ለ 7ኛዉ የከተሞች ሳምንት የተዘጋጀ መፅሄት፡፡)

## 4.3. የኢኮኖሚና የመሰረተ ልማት ሁኔታ

የከተማዉ ህዝብ የሚተዳደረዉ በንግድ፣በግብርና እና በመንግስት ስራዎች ነዉ።በከተማዉ በአብዛኛዉ የሚመረተዉ ስንዴ፣ በቆሎ፣ ጤፍ፣ ገብስ እና ባቄላ ሲሆኑ በተጨማሪም ሌሎች አትክልቶች ይመረታሉ። ማህበረሰቡ ከእንስሳት እርባታ ማለትም የጋማ ከብቶች፣የቀንድ ከብቶች ፣በግ፣ፍየል እና ዶሮ በማርባት ከፍተኛ የሆነ ጥቅም ያገኛል።

ትምህርትን በተመለከተ በደሴ ከተማ 1998 የተመሰረተዉ ወሎ ዩኒቨርሲቲን ጨምሮ በርካታ የመንግስት እና የግል 36 አፀደ ህፃናት ፣81 አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ 36 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና 4 የመሰናዶ ትምህርት ቤቶች፣ በርካታ ኮሌጆች እና የግል ዩኒቨርሲቲዎች እንዲሁም አንድ የመንግስት አዳሪ ትምህርት ቤት በከተማዋ ይገኛሉ።

ጤናን በተመለከተ የአንድ ሀገር እድገት አመላካች ከሆኑት መካከል አንዱ ጤና ነዉ። በደሴ ከተማም ሁለት የመንግስት ጠቅላላ ሆስፒታሎች ማለትም ደሴ ሪፈራር ሆስፒታል፣ እና ቦሩ ሆስፒታል እንዲሁም 8 የመንግስት ጤና ጣቢያዎች ያሉ ሲሆን፤ በግሉ የጤና ዘርፍም 34 ክሊኒክ እና 6 ሆስፒታሎች ባቲ ጠቅላላ ሆስፒታል፣ኢትዮ ጠቅላላ ሆስፒታል፣ሰላም ጠቅላላ ሆስፒታል፣ጦሳ ጠቅላላ ሆስፒታል፣ መሰረት ጠቅላላ ሆስፒታል እና ወ/ሮ ስህን ጠቅላላ ሆስፒታሎችን ጨምሮ በርካታ የግል ክሊኒኮችን ጨምሮ በድምሩ 50 የጤና ተቋማት ይገኛሉ።
(ምንጭ:- የደሴ ከተማ አስተዳደር የ2012 ዓ.ም የልማት አመልካቾች መፅሄት። )

## 4.4. የቱሪዝም እና ባህላዊ እሴቶች ሁኔታ

ኪነጥበብ፡-የዉቦች ከተማ እንደሆነች የሚነገርላት ደሴ ከተማ በኪነ ጥበቡ ረገድ በሀገሪቱ ዉስጥ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ካላቸዉ ከተሞች አንዷ ናት። በከተማይቱ መሀል እምብርት የሚገኙ ወሎ ባህል አምባ እና ምንትዋብ አዳራሾች ለከተማዋ የኪነጥበብ እድገት ከፍተኛዉን ድርሻ ይወስዳሉ።

ሙዚቃ፡- የአራቱም የሙዚቃ ቅኝቶች መፍለቂያ የሆነችዉ ደሴ ከተማ በሙዚቃዉ ዘርፍ በሀገር ከፍተኛ ድርሻ ካላቸዉ ከተሞች አንዷ ናት። ለዚህም ተጠቃሽ የሚሆነዉ ከከተማይቱ የሚወጡ በርካታ ድምፃዉያንን መጥቀስ ይቻላል።በተጨማሪም ከተማይቱን አስመልክቶ የተዘፈኑ ከመቶ ሃያ በላይ የአማርኛ ዘፈኖች እንዳሉ ይነገራል።አብዛኛዎቹ ዘፈኖች በከተማዋ ለሚገኙ ቆነጃጅቶች

የተዜሙ ናቸዉ። ባህሩ ቃኘዉ፣ ማሪቱ ለገሰ፣ ዚነቱ ሙሃባ፣ መስፍን አበበ፣ አያሌው መስፍን ወዘተ የሚባሉት የባሃልና ዘመናዊ ዘፋኞች የተገኙት ከደሴ ነዉ።

መዝናኛ፡- በከተማይቱ ዉስጥ በ1996 የተገነባ ግዙፍ የወጣቶች ማእከል ይገኛል።ይህ ማእከል ከፍተኛ አገልግሎት እየሰጠ ቢሆንም በቂ እንዳልሆነ ግን ይታመናል። የቤተሰብ መምሪያ እና ሰርከስ ደሴን ጨምሮ በርካታ መካከለኛ እና አነስተኛ የሙዚቃ ባንዶች እንዲሁም ቃተኛ የተባለ የባህል ምሽት ቤት ይገኛሉ። ከተገነባ በርካታ አመታትን ያሳለፈዉና ተገቢዉን እድሳት ያላገኘዉ የደሴ ከተማ ስታዲየም በከተማይቱ እምብርት ይገኛል።
(ምንጭ፡- የደሴ ከተማ አስተዳደር የ2012 ዓ.ም የልማት አመልካቾች መፅሄት)

## ምዕራፍ አምስት፡- የመረጃ አቅርቦት እና ትንተና

በዚህ ምዕራፍ ትኩረት የተደረገው በደሴ ከተማ አስተዳደር የሚገኙትን የቦታ ስሞች አሰያዬም፣ ለውጥ፣ ተከታታይነትና ማህበረሰባዊ ፋይዳ ለመፈተሽ በተሰበሰቡት መረጃዎች ትንተናና በተገኙት ውጤቶች ማብራሪያ ላይ ነው፡፡

ስለሆነም በከተማ አስተዳደሩ ስር ከሚገኙት የክፍለ ከተማ፣ የቀበሌ፣ የመንደርና የመልከዓምድር አካባቢዎች (ተራራ፣ ጎራ፣ ገበያ ወዘተ) ስሞች የተመረጡት አሰያዬም፣ በስሞቹ ላይ በዘመን፣ በርዕዮተ ዓለምና በታሪክ መለዋወጥ ምክንያት የተካሄደውን የለውጥ ሂደትና ሳይለወጡ ዘመን የተሻገሩትን ለማጥናት በቃለ መጠይቅ፣በምልከታ፣ በቡድን ተኮር ውይይትና በሰነድ ፍተሻ በተሰበሰቡት መረጃዎች ላይ የተካሄደው ትንተና፣ በተከታይም የውጤት ማብራሪያና የተደረሰባቸው ግኝቶች በገለፃ ቀርበዋል፡፡

የስም አወጣጥ ወይም ስያሜ አሰጣጥ እንደየ ማህበረሰቡ ባህል፣ ልማድ፣ እምነትና የህይወት ተሞክሮ የሚለያይ ቢሆንም የማህበረሰቡን ማህበረ ባህላዊ ዕሴቶች መሰረት አድርጎ የሚነሳ መሆኑ ተመሳሳይ ባህሪን እንዲጋራ ያደርገዋል፡፡ ለማንኛውም ሰዋዊም ሆነ ቁሳዊ አካልና ስሜታዊ ሁነት የሚሰጡት ስሞችና በስሞቹ ላይ የሚካሄዱት ለውጦች መነሻ ምክንያቶች የታላሚው ማህበረሰብ እምነት፣ ርዕዮተ ዓለም፣ ባህላዊና ምጣኔ ሃብታዊ ዕድገት፣ የማህበራዊ ቡድኑ እንቅስቃሴና መስፋፋት (ፍልሰት) ወዘተ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

በተጠቀሱትና በሌሎችም ምክንያቶች ከሚፈጠሩት ስሞች መካከል አንዳንዶቹ ከትውልድ ትውልድ እየተሸጋገሩ አገልግሎት ይሰጣሉ፤ ተከታታይነትን ጠብቀው ዘመን ይሻገራሉ፡፡ ከፊሎቹ ደግሞ በተለያዩ አጋጣሚዎች የለውጥ ሂደት ይከናወንባቸዋል፤ በአዳዲስ ስሞችም ይተካሉ፡፡ አዳዲሶቹም ሆኑ ነባሮቹ ስሞች የታላሚው ማህበረሰብ የስነቃል ማጠንጠኛ፣ የርዕዮተ ዓለም ለውጥ መጠቆሚያ፣ የቋንቋ ውስትና ዕድገት ማገናዘቢያ ወዘተ ሆነው ያገለግላሉ፤ በተጠቀሱት ዘርፎች ለሚደረጉ ምርምሮችም በመረጃነት ሊያገለግሉ ይችላሉ፡፡ ጥቂት ማሳያዎችን እንጥቀስ፡-

<u>አይጠየፍ</u> ሆነን <u>ሙጋድን</u> አየነው፣

እንዲህ ነች አዱኛ ነካ አርጋ እልፍ ነው፡፡

<u>ደሴ</u> <u>ደረቅ ወይራ ገራዶ</u> <u>ቢለን፣</u>

የስንቱ ወሬዛ ለከፈኝ እኔን።

በእነዚህ የዘፈን ቃል ግጥሞች ውስጥ የተገለጹትና ሰረዝ የተደረገባቸው ቃላት በደሴ ከተማና በገጠር ቀበሌዎች የሚገኙ ቦታዎችን የሚወክሉ ስሞች ናቸው። ከዚህም በተጨማሪ ማህበረሰቡ የተለያዩ ስሜቶቹን ለሚገልጽባቸው የዘፈን ቃል ግጥሞች ማጠንጠኛ በመሆን አገልግለዋል።

በተመረጠው የጥናት አካባቢ ከሚገኙት የቦታ ስሞች መካከል ተከታታይነትን ጠብቀው የዘለቁት፣ ለለውጥ የተጋለጡትና በለውጡ ሂደት የተተኩት የትኞቹ ናቸው? የስያሜዎቹ ምክንያቶችና የስሞቹ ታሪካዊ፣ ትዕምርታዊ፣ ፖለቲካዊ፤ ስነልሳናዊና ባህላዊ ፋይዳዎችስ ምንድን ናቸው? የሚሉትን ጥያቄዎች መመለስ ያስችሉ ዘንድ የተሰበሰቡት መረጃዎች ትንተና እና ግኝቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

## 5.1. የቦታ ስሞችን ተከታታይነትና የተከታታይነት ምክንያቶች የሚመለከቱ መረጃዎች ትንተና፤

በደሴ ከተማ አስተዳደር ስር የሚገኙት አምስት ክፍለ ከተማዎች፣ በየክፍለ ከተማዎቹ ስር የሚገኙት አስራ ስምንት ቀበሌዎችና በእያንዳንዱ ቀበሌ ስር ከሚገኙት ሰፈሮች ብዙዎቹ ሥያሜያቸውን እንደያዙ የዘለቁ ናቸው (ዝርዝሩን በአባሪ 3 እና 4 ይመልከቱ) ። ከመረጃ አቀባዮች በተገኙት መረጃዎች መሰረት ተከታታይነትን ጠብቀው እስካሁን ከዘለቁት ወይም ለውጥ ካልተካሄደባቸው የቦታ ስሞች መካከል በእጣ ንሙና የተወሰዱት እንደሚከተለው ተተንትነዋል።

*ሰኞ ገበያ፡-*

ቀደም ሲል ለተወሰነ የገበያ ሥፍራ፣ ከዚያም በገበያው የቅርብ ርቀት ለሚገኝ ሰፈርና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ በስሩ ሶስት ቀበሌዎችን ለያዘ የክፍለ ከተማ አስተዳደር የተሰየመ መጠሪያ ነው። በቃለ መጠይቅ በተገኘው መረጃ መሰረት የወሎ ጠቅላይ ግዛት ዋና ከተማ ሆና የተቆረቆረችው ደሴ ከተማ እያደገችና የነዋሪዎቿም ቁጥር እየጨመረ በመሄዱ ለህዝቡ ቋሚ የግብይት ማእከል አስፈላጊ ሆነ። ይህን የተገነዘቡት ንጉስ ሚካኤል በከተማዋ የመጀመሪያ የሆነዉን የገበያ ስፍራ አቋቋሙ። ገበያዉ በየሳምንቱ በዕለተ ሰኞ እንዲቆም ስለተወሰነም ለገበያ የተመረጠው ቦታ ሰኞ ገበያ የሚል ስያሜ ተሰጠው። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሰኞ ገበያ የሚለው ስያሜ የገበያውና የሰፈሩ ብቻ ሳይሆን አገልግሎቱን በማስፋት ለክፍለ ከተማው፣ በክፍለ

ከተማው ስር ለተቋቋሙት ተቋማትም፤ ትምህር ቤት፣ ጤና ጣቢያና ባንክ መጠሪያ ሆኖ እያገለገለ ይገኛል። (አቶ ተፈራ መላኩ፣ አቶ እብራሂም ሁሴን፣ አቶ ሁሴን አየለ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ነሀሴ 29/2013 ዓ.ም)።

ሰኞ ገበያ ከአብዛኞቹ የወሎ ጠቅላይ ግዛት አውራጃዎች ገበሬው ያመረተውን እህል ለማቅናትና ያረባውን የቁም ከብት ለመሸጥ፣ በምትኩም የፋብሪካ ምርቶችን ለመግዛት ለቀናት ተጉዞ የሚደርስበት ትልቅ የግብይት ማዕከል ነው። ሰኞ የገበያው ጥቅል መጠሪያ ይሁን እንጂ የእህሉም ሆነ የእንስሳቱ ዓይነት መገበያያ ራሱን የቻለ ተራ ወይም መደብ አለው፤ ለአብነትም ዶሮ ተራ፣ በሬ ተራ፣ ፈረስ ተራ …፤ ጤፍ ተራ፣ ገብስ ተራ፣ ድበላ ተራ…፤ ጥጥ ተራ፣ ጥብቆ ተራ፣ ስፌት ተራ … የሚሉት ይጠቀሳሉ። ይህ ስም በአሁኑ ጊዜ ውክልናውን አስፍቶ ሰኞ ገበያ ሰፈር፣ ሰኞ ገበያ ክፍለ ከተም፣ ሰኞ ገበያ ትምህርት ቤት፣ ሰኞ ገበያ ጤና ጣቢያ፣ ሰኞ ገበያ ቅርንጫፍ ባንክ ለሚሉት ተቋማት መጠሪያ በመሆን እያገለገለ ይገኛል። እዚህ ለይ ለስነልሳን ቡድኑ ብቻ ሳይሆን ለቋንቋው የቃላት መድብልም ጉልህ አስተዋጽዖ ማድረጉን ከቀረበው መረጃ መገንዘብ ይቻላል።

በዘውዳዊው አገዛዝ ሰኞ ገበያ ከመገበያያ ማዕከልነቱም በላይ የአዋጅ ማስነገሪያ፣ የፍርድ ውሳኔ ማስፈጸሚያ ሆኖ ሲያገለግል ኖሯል። በገበያው መካከል ከብት ተራ ተብሎ በሚጠራው ቦታ በኳስ መጫዎቻ የጎል በር ቅርጽ የተዘጋጀ ብረት ነበር። ይህ የብረት ቋሚ እስከ አምስት የሚደርሱና በሰሩት ወንጀል የሞት ፍርድ የተበየነባቸውን ሰዎች በስቅላት ለመቅጣት የተዘጋጀ ነበር። ከጥዋቱ አስራ ሁለት ሰዓት እስከ ምሽቱ አስራ ሁለት ሰዓት (ሰንደቅ ዓላማ ከሚሰቀልበት አስከሚወርድበት ጊዜ) ተሰቅሎ የሚቆየውን አስክሬን ለገበያ የመጣው ሰው ሁሉ እያዬ" ነገ በእኔ" እያለ እንዲማርበት የታሰበ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል። ይህ ተግባር እስከ 1966 ዓ. ም የስርዓት ለውጥ ድረስ በስፋት ሲፈጸም ቆይቷል። (አቶ ተፈራ መላኩ፣ አቶ ፈንታሁን ይመር፣ ሸህ ሰይድ የሱፍ፣ ቃለመጠይቅ፣ ሀምሌ 29/2013 ዓ.ም)

**ሆጤ፦**

ሆጤ በከተማዋ ሰሜናዊ አቅጣጫ የሚገኝ ሜዳማ ስፍራ ነዉ። ይህን ስፍራ ንጉስ ሚካኤል እንደ ጥምቀት ያሉ ታላላቅ በአላትን ለማክበርና ወታደራዊ ትእይንትን ለማካሄድ ይጠቀሙበት ነበር። የንጉስ ሚካኤል የንግስና ስርአት የተከናወነዉም በዚሁ በሆጤ ሜዳ ነዉ። በስነስርአቱ ላይ የተገኘዉ አምሳ ሺ ያህል ህዝብ ስለነበር የሜዳዉን የመያዝ አቅም ለመግለጽ"ያን ሁሉ ሰዉ እኮ ዋጠዉ፤ ዋጤ የሆነ ሜዳ"

ተብሎለታል፡፡ ከዚሁ የሕዝብ አገላለጽ በመነሳት አካባቢው ሆጤ ሜዳ የሚለዉን ስያሜ እንዳገኘ ይነገራል፡፡(ሰነድ ፍተሻ ፦ ምስጋናዉ ታደሰ፣ 2013ዓ.ም )

ከሰነድ ፍተሻዉ የተገኘዉ መረጃ እንደሚያመላክተዉ ሆጤ የሚለዉ ስያሜ በንጉስ ሚካኤል አገዛዝ እንደተሰየመ እና አሁን ድረስ ስያሜዉን እንደያዘ የዘለቀ ቦታ ነዉ፡፡ በአሁኑ ወቅት በደሴ ከተማ ከሚገኙት ክፍለ ከተሞች የአንዱ መጠሪያ በመሆን እያገለገለ ይገኛል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በአካባቢዉ ላይ የተገነቡት ጤና ጣቢያ፣ ትምህርት ቤትና ስታዲየም ሆጤ በሚለው ስያሜ እየተጠሩ ይገኛሉ፡፡ ቦታዉ ሰፊ እና ሜዳማ በመሆኑ አሁንም ቢሆን የተለያዩ ሀይማኖታዊ እና ብሄራዊ ክብረ በዓላት ይከወኑበታል፡፡ ከሚከወኑት ክብረበአላት መካከል እንደ ጥምቀትና የመስቀል ደመራ ያሉት በዋናነት ሲጠቀሱ የብሄር ብሄረሰቦች ቀን፣ የባንዲራ ቀን እና የተለያዩ የድል በአላትም በድምቀት ቦታዉ ላይ ይከበራሉ፡፡ ሆጤ የሚለው ስያሜ የቦታው መጠሪያነቱን እንደያዘ ለረጅም ጊዜ የቆየ፣ አገልግሎቱን እያሰፋ ተከታታይነትን ጠብቆ የዘለቀ መሆኑን የተገኘው መረጃ ያመላክታል፡፡ የስያሜው ዘላቂነት ምክንያቱ ቃሉ በእማሬም ሆነ በፍካሬ ፍችው ከማንነት ጋር የማይያያዝ፣ ፖለቲካዊም ሆነ ርዕዮተ ኣለማዊ አንድምታ የሌለው፣ በማንኛውም ማህበራዊና ስነልሳናዊ ቡድን ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚያሳድር አለመሆኑ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል፡፡

**ስልክ አምባ፡-**

በዚህ ስም የሚጠራው አካባቢ (ሰፈር) በከተማው ምስራቃዊ ክፍል፣ ከአይጠየፍ ቤተመንግስት በቅርብ ርቀት የሚገኝና ኮረብታማ ቦታ ነው፤ አምባ የሚለው ተጣማሪ ቃልም የቦታውን ከፍታማነት ለመግለጽ የተመረጠ ይመስላል፡፡ የዘመናዊ ስልጣኔ መገለጫ ከሆኑት አንዱና ወደ አገራችን በዳግማዊ ምኒልክ እንደገባ የሚገለጸው፣ በወቅቱ በነበረው ማህበረሰብ (በንጉሱ ዙሪያ ባሉትም ጭምር) ተቀባይነት እንዳልነበረው የሚነገረው ስልክ በደሴ ከተማ ለመጀመሪያ ጊዜ በንጉሥ ሚካኤል ቤተ መንግሥት መዘርጋቱን መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

ከሰነድ ፍተሻ በተገኘ መረጃ መሰረት ከአስመራ እስከ አዲስ አበባ የተዘረጋዉ የስልክ መስመር የደሴ ከተማንም የስልክ አገልግሎት ተጠቃሚ አድርጓታል፡፡ ለቤተመንግስቱ ከሚሰጠው አገልግሎት ባሻገርም በቤተ መንግስቱ አቅራቢያ ለሚኖረው ህዝብ (በተለይም ለአንጋችና ሹማምንቱ) አገልግሎት ይሰጥ ዘንድ ከቤተመንግስቱ በስተምዕራብ አቅጣጫ ባለዉ መንደር የስልክ አገልግሎት መስጫ

ማዕከል ተቋቁሞ ነበር። ይህን ተከትሎም መንደሩ ስልክ አምባ እየተባለ ይጠራ ጀመር (ሰነድ ፍተሻ፡-ምስጋናዉ ታደሰ፣ 2013 ዓም) ።

ቃለ መጠይቅ ከተደረገላቸው መረጃ ሰጪዎች በተገኘው መረጃ መሰረትም፤ መጀመሪያ ንጉስ ሚካኤል አይጠየፍ ቤተመንግስታቸዉን እና እልፍኛቸዉን አሰርተዉ ሲቀመጡ በወሎ ጠቅላይ ግዛት ለመጀመሪያ ጊዜ ስልክ የገባዉ እዚህ ቦታ ላይ ነበር። በዚህም የሰፈሩ ስም ስልክ አምባ ተባለ፤ አሁንም ድረስ የቀበሌ መጠሪያ ሆኖ እያገለገለ ይገኛል (ሸህ ሰይድ የሱፍ፣ ወ/ሮ ዙሪያሽ ካሳ፣ አቶ ተፈራ መላኩ፣ ቃለመጠይቅ፣ መስከረም 16/2014 ዓ.ም)

ከሰነድ ፍተሻዉ እና ከቃለመጠይቁ መረጃ እንደምንገነዘበዉ ስልክ አምባ ስያሜዉን ያገኘዉ አካባቢዉ ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ የስልክ መስመር ተዘርግቶ አገልግሎት በመስጠቱ ምክንያት ነዉ። ቦታዉ ከፍታ ላይ ያለ በመሆኑ እና የስልክ መስመር በመዘርጋቱ ስልክ አምባ የሚል ስያሜ ተሰጥቶታል። በአንድ በኩል የስልክ መጀመሩ፣ በሌላ በኩል አካባቢው መሃል ከተማውን ወደታች መመልከት የሚያስችል ኮረብታማ መሆኑን በማየትና ሁለቱን ቃላት በማጣመር ለቦታው (ለሰፈሩ) እንዲወከል ተደርጓል። ስያሜዉ ለትምህርት ቤት መጠሪያ ማለትም ስልክ አምባ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና ለቀበሌ መጠሪያ በመሆን እያገለገለ ይገኛል።

ስልክ አምባ የሚለው የቦታ ስም ከተሰየመበት ጊዜ እስካሁን ለለውጥ ሳይጋለጥ በማገልገል ላይ ያለና ተከታታይነትን ጠብቆ የዘለቀ ነው፤ ለዚህም በአንድ በኩል መልከዓምድራዊ ተፈጥሮን፣ በሌላ በኩል በዘመኑ እንግዳ የሆነውን የቴክኖሎጂ ውጤት መጠሪያዎች አጣምሮ መያዙና ማናቸውንም አሉታዊ የስነልቡናና የስሜት ተጽእኖዎች አለመፍጠሩ በምክንያትነት ሊጠቀሱ ይችላሉ። የታሪክ መረጃነትና ስነልሳናዊ ፋይዳውም የተከታታይነቱ ትሩፋት ሆነው ዘመን ሊሻገሩ እንደሚችሉ መረጃዎቹ ያመላክታሉ።

**አረብ ገንዳ፡-**

የንጉስ ሚካኤልን ቤተ መንግስት እና በግቢዉ የሚገኙ ግብረ ህንፃዎችን የሰሩት የግንባታ ባለሙያዎች ከግሪክ፣ ከአርመንና ከተለያዩ የአረብ ሀገራት የመጡ መሆናቸው ይነገራል። በተለይም ከየመን የገቡት አረቦቹ ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመምጣቱ ንጉሱ ቤት እየሰሩ በከተማዋ እንዲኖሩ በማበረታታት የቤት መስሪያ ቦታ ሰጥተዋቸዋል ይባላል። እነዚህ የውጭ በተለይም የአረብ ዜጎች መኖሪያቸውን በአንድ አካባቢ፤ በተለይም በከተማው ሰሜናዊ ክፍል አደረጉ።

የአገሬው ሰው ይህንኑ አካባቢ ወይም መንደር አረብ ገንዳ (የአረቦች መኖሪያ መንደር) እያለ መጥራት ጀመረ። (ሰነድ ፍተሻ፡- ምስጋናዉ ታደሰ፣ 2013 ዓ.ም)

ይህ መረጃ እንደሚያመላክተዉ በዘመኑ የወሎ ጠቅላይ ግዛት ገዢ ነበሩት ንጉስ ሚካኤል (መሐመድ አሊ) አረቦች በከተማው እንዲኖሩ ፈቃድ በመስጠታቸው ምክንያት አረብ ገንዳ የተባለው መንደር ሊመሰረት ችሏል። የስያሜው ምንጭም የነዋሪዎቹ ዜግነት ሲሆን ሰፈሩ ከከተማው ዋና አደባባይ ወይም ፒያሳ ጀምሮ ወደሰሜን አጣጫ መናኸሪያ ወይም ቶታል እስከሚባለው አካባቢ ይደርሳል።

በዚህ ሰፈር ይኖሩ የነበሩት የውጭ ዜጎች ከ1960ዎቹ መጀመሪያ ጀምሮ በተለያዩ ሁኔታዎች (በአብዛኛው በፖለቲካዊ እንቅስቃሴና ለውጥ) ምክንያት ለቀዋል፤ የአገሬው መኖሪያና የንግድ ማዕከልም ሆኗል፤ ይሁን እንጂ ሰፈሩ አሁንም አረብ ገንዳ የሚለውን ስያሜ እንደያዘ ይገኛል። በዚህም ስያሜዉ ተከታታይነትን ጠብቋል ማለት ይቻላል።

አረብ ገንዳ የሚለዉ የቦታ ስያሜ አረብ እና ገንዳ ከሚሉት ሁለት የውሰት ቃላት (ከአረብኛና ከኦሮምኛ ቋንቋዎች) ጥምረት የተገኘ ሲሆን የአረቦች መኖሪያ ሰፈር ለሚለዉ ሃሳብ በውክልና ቆሟል። የቋንቋውን የቃላት መድብል በማስፋት ረገድም ጉልህ ስነልሳናዊ ፋይዳ እንዳለው መገንዘብ ይቻላል። ይህ ስያሜ በቀድሞ ነዋሪዎቹ መልቀቅና በአገሬው ሰዎች መተካት ምክንያት ሳይለወጥ ዘልቋል። የዘላቂነቱ ምክንያት በማህበረሰቡ ማህበረ ባህላዊም ሆነ ስነልቡናዊ ሁኔታ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳደረ ሆኖ አለመገኘቱ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል።

**ሳላይሽ፡-**

የደሴ ከተማ መስራች የሆኑት ንጉስ ሚካኤል ከገራዶ የጦሳን ተራራ ጥግ ይዘዉ ይጓዙ በነበረበት ጊዜ የሚጓጓዙባቸው እንስሳት የሚጠጡት ውሃ በአካባቢው እንዳለ ሲጠይቁ አንዲትን ምንጭ ይጠቁሟቸዋል። ከጦሳ ተራራ ስር የሚመነጨውን ኩል የመሰለ ውሃ ባዩ ጊዜ “እንዴት እስካሁን ሳላይሽ” በማለት አድናቆታቸውን ገለጡ፤ ይህን ተከትሎ የአካባቢው ነዋሪ ሰፈሩን ሳላይሽ በማለት መጥራት እንደጀመሩ መረጃዎች ይጠቁማሉ (አቶ አያሌዉ ይማም፣ ወ/ሮ ዙሪያሽ ካሳ፣ አቶ ፈንታሁን ይመር፣ ሸህ ሰይድ የሱፍ…የቡድን ዉይይት፣ መጋቢት 10/2014 ዓም)።

በዚሁ ጉዳይ ላይ ሌሎች መረጃ አቀባዮች የሰጡት መረጃ እንደሚከተለዉ ቀርቧል። ንጉስ ሚካኤል ገራዶ በበቅሎ ደርሰዉ ሲመለሱ ፉልል ፉልል የምትል የምንጭ ዉሃ አዩ። አሽከራቸዉን "አንተ እስኪ ከዚህ ዉሃ በኮዳ ጠልቀህ ስጠኝ" አሉት እና ዉሃዉን ግጥም አድርገዉ ጠጡ።" ድገመኝ" አሉ አሽከራቸዉም (አገልጋያቸዉ) ዉሃዉን በድጋሜ ጠልቆ ሰጣቸዉ። ንጉሱም ከጠጡ በኋላ አቀበቱን ይዘዉ ወደ ላይ ወጡ። አካባቢዉ በጣም ልለምለም በመሆኑ "ኧረግ ኧረግ እስከዛሬ ሳላይሽ የትነበርሽ" በማለት ተናገሩ፤ በዚያዉ የቦታዉ ስም ሳላይሽ ተባለ። (አቶ ሁሴን አየለ፣ አቶ ኢብራሂም ሁሴን፣ አቶ ተፈራ መላኩ፣ ቃለመጠይቅ፣ ግንቦት 15/2013 ዓ.ም)

ከላይ በቀረቡት መረጃዎች ላይ መጠነኛ የአገላለጽ ልዩነት ቢኖርም ማዕከላዊ ጭብጡ ንጉስ ሚካኤል ለምንጭ ውሃው ወይም ለአካባቢው አድናቆትና አግራሞታቸውን የገለጹበት ቃል በነዋሪው ህዝብ የሰፈሩ መጠሪያ ተደርጎ መወሰዱን የሚያስረግጥ ነው። ሳላይሽ የሚለዉ ቃል እስካሁን ድረስ ሳላስተዉልሽ፣ ሳልመለከትሽ የሚል ፍች የያዘ የአማርኛ ቃል ነው። በሁኔታዉ የንጉሡ መገረም እና መደነቅ ለስሟ መነሻ ምክንያት መሆኑን ከመረጃው እንገነዘባለን። በአሁኑ ጊዜ ሳላይሽ የሚለዉ መጠሪያ ከሰፈርም አልፎ የቀበሌ አስተዳደርና የዕድር መጠሪያ በመሆን እያገለገለ ይገኛል። ስያሜዉ ለውጥ ያልተካሄደበት በመሆኑ ተከታታይነትን ጠብቆ እስካሁን የዘለቀ ነዉ ማለት ይቻላል።

ሳላይሽ በከተማዋ ደቡባዊ አቅጣጫ በር በመሆኑ በከተማው ኗሪ ባልሆኑ ማኅበረሰቦችም ዘንድ በስፋት የሚታወቅ ስያሜ ነው። ከዚህ በተጨማሪ አካባቢውንና ታሪካዊ ሁነቶች ላይ የሚያተኩሩ የተለያዩ ስነቃሎችና የዘፈን ግጥሞች የሳላይሽ ስም የተካተተባቸው ናቸዉ።

ለምሳሌ፡- እንዴት ነዉ ሳላይሽ ሰኞ ገበያዉ፣

ሁሉን አገናኝቶ የሚያጣቅመዉ።

ከላይ ያነሳናቸው ምክንያቶች ስያሜው ተከታታይነቱን ጠብቆ የመቆየቱ መላምታዊ ማስረጃዎች ናቸው።

**ሸዋ በር፡-**

ይህ ሰፈር የሚገኘዉ ከአይጠየፍ በታች ከደሴ ሙዚየም ፊት ለፊት ነዉ። ከደሴ ከተማ ወደ ደቡብ አቅጣጫ ለመውጣት በቅርብ ጊዜ ተለዋጭ መንገድ ከመሰራቱ

በፊት በጣሊያኖች (1928 “1933) ከአሥመራ እስከ ሞያሌ የተሰራው አስፓልት መንገድ የሚያልፍበት አካባቢ ነው። ደሴ እንዳሁኑ ሳትስፋፋ የከተማዋ ዳርቻ፣ በደቡብ አቅጣጫ የከተማዋ መዳረሻ ወይም ወደሸዋ መውጫ (መግቢያም ጭምር ነው) በር ነው። አሁንም ከደሴ ወደ ደቡብ አቅጣቻ የመኪናም ሆነ የእግረኛ መግቢያና መውጫ ሆኖ እያገለገለ ይገኛል። ይህ ስያሜ የመውጫ በሩ ብቻ ሳይሆን ሰፊ አካባቢን የሚሸፍን ሰፈርንም ጭምር የሚወክል ነው። ሸዋ በር የሚለውን የሰፈር ስያሜ በተመለከተ በቃለ መጠይቅ የተሰበሰበው መረጃ እንደሚከተለው ቀርቧል።

ሸዋ በር ብለዉ የጠሩት አጼ ሚኒሊክ ናቸዉ። እንዴት አዉቀዉ ጠሩት? ቢባል ለአድዋ ዘመቻ ከሸዋ ተነስተው ወደ ሰሜን ከሰራዊታቸው ጋር ሲሄዱ ወላሞ ሰፈር ወይም አሁን መንበረ ፀሀይ በሚባለው አካባቢ አድርገዉ ነበር የሄዱት። ድል አድርገው ወደ ሸዋ ሲመለሱ ጡርንባ እየተነፋ፣ ነጋሪት እየተጎሰመ በበቅሎ ሆነዉ ደሴ ከተማን ሲያልፉ በየት መጡ? በመስጊዱ ግርጌ መጡ። ይሄ ነገር ስንሄድ በምስራቁ በኩል አይደል እንዴ የመጣነዉ? ይሄ ነገር ዞረብኝ እሳ ብለዉ ጠየቁ። አብረዋቸዉ ያሉትም ዋናዉ በር ይሄ ነዉ፤ ለአዲስ አበባ (ለሸዋ) ትይዩ ይሄ ነዉ አሏቸዉ። ይሄማ ሸዋ በር ነዋ አሉ። ከዛን ጊዜ ጀምሮ የሰፈሩ ስያሜ ሸዋ በር ተብሎ መጠራት ጀመረ። (አቶ ተፈራ መላኩ፣ አቶ እብራሂም ሁሴን፣ ወ/ሮ ዙሪያሽ ካሳ፣ ቃለመጠይቅ፣ ሀምሌ 29/2013 ዓ.ም)

ሸዋበር ለሚለዉ መጠሪያ የመጀመሪያዉን ስያሜ የሰጡት አጼ ሚኒልክ እንደሆኑ ከቀረበው ቃላዊ መረጃ መረዳት ይቻላል። ይሁን እንጂ በተለያዩ አካባቢዎች ከሚታየው ተሞክሮ አኳያ ሲታይ አገሬው ወይም የአካባቢው ነዋሪ አቅጣጫን መሰረት አድርጎ ቦታዎችን ሲሰይም ይስተዋላል፤ ለምሳሌ ሰሜን በር፣ ጎጃም በር፣ ጎንደር በር ወዘተ። ከዚህ አንጻር ሲታይ አገሬው መልከዓምድራዊ አቅጣጫውን መሰረት አድረጎ ስያሜውን የሰጠበት አጋጣሚም እንደሚኖር ማሰብ የሚቻል ይመስላል። በተጠቀሱት አስረጅዎች ሲመዘን የስያሜው መነሻ ምክንያት መልከዓምድራዊ አቅጣጫ ሲሆን ለለውጥ ሳይጋለጥ ተከታታይነትን ጠብቆ እስካሁን ቆይቷል። በአሁኑ ወቅትም ሸዋ በር የሚለዉ ስያሜ ለሰፈሩ ብቻ ሳይሆን ለሃይማኖት ተቋም (ሸዋ በር መስጅድ) እና ለተለያዩ የንግድ ድርጅቶች (ሱቅ) በውክልና ያገለግላል።

**ካራጉቱ፡-**

ካራ ጉቱ የኦሮምኛ ቋንቋ ቃል ሲሆን ካራ እና ጉቱ የሚሉት ራቸውን የቻሉ ቃላት ተጣምረዉ የፈጠሩት ነው፡፡ በደሴ ከተማ ሰሜናዊ ጫፍ ላይ ለሚገኝ አካባቢ የተሰጠ ስያሜ ነው፡፡ የዚህን ቦታ ስም አሰያየምና ትርጓሜ በሚመለከት ከመረጃ አቀባዮች የተገኘው መረጃ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡ ኦሮሞዎች በተለያዩ አካባቢዎች ሰፍረዉ ይኖሩ ነበር፤ በዚያን ወቅት ጉታ የሚባል አንድ የኦሮሞ ተወላጅ በቦታዉ ላይ ኑሮውን እንደመሰረተ ይነገራል፡፡ ይህ ሰው የሚኖርበት ቦታ ከአውራ መንገድ ገባ ብሎ ስለነበር የአካባቢው ነዋሪዎች ወደ ግለሰቡ ቤት የሚያመራዉን መንገድ (ካራ) ከስሙ ጋር በማጣመር ካራጉቱ የሚል ስያሜ እንደሰጡት ይረነገራል፡፡ ትርጉሙም የጉቱ ወይም ወደ ጉቱ ቤት የሚወስደው መንገድ ማለት ነው፤ በዚህ መነሻነት ካራ ጉቱ የሚለዉ ስያሜ ለአካባቢው መጠሪያ ሆኖ እስካሁንም እያገለገለ ይገኛል (አቶ ተፈራ መላኩ፣ አቶ ሰይድ አበጋዝ፣አቶ ሰይድ የሱፍ፣ ቃለመጠይቅ፣ ሀምሌ 29/2013 ዓ.ም) ፡፡

ከቀረበው የቃል መረጃ መረዳት እንደሚቻለው ካራ ጉቱ የሚለው ስያሜ ታሪካዊ ሁነትን መነሻ ያደረገ ይመስላል፡፡ ከታሪክ እነደምንረዳው በኦሮሞዎች መስፋፋት ምክንያት በበርካታ አካባቢዎች ኦሮሞዎች ከአማራው ጋር ወይም ብቻቸውን በኖሩበት የታሪክ አጋጣሚ ብዙ ቦታዎች ከኦሮምኛ ወይም ከአማርኛና ኦሮሞኛ ቋንቋ ተወስደው በተጣመሩ ቃላት ተወክለው ይገኛሉ፤ ለአብነትም ወረባቦ፣ ወረሂመኑ፣ ለገሂዳ፣ አጣሪ ገንዳ፣ በርበሬ ገንዳ ወዘተ የሚለት በወሎ የሚገኙ የቦታ ስሞች ይጠቀሳሉ፡፡

መረጃ አቀባዮቹ እንዳሉት ካራ ማለት በኦሮምኛ መንገድ ሲሆን ጉታ ኦሮሞ ለሆነ ተባዕታይ ጾታ የሚሰጥ መጠሪያ ስም ነው፤ ቃላቱ ሲጣመሩ ጉታ ወደ ጉቱ የተቀየረበት ስነልሳናዊ ሂደት በቋንቋ ጥናት የሚታይ ሆኖ የማህበረሰቡ መስተጋብር የቋንቋዎችን መዋዋስ፤ ይህም ለቋንቋ ዕድገት ያለውን አበርክቶ ከቀረበው መረጃ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህ ዘመናትን የተሻገረ ሁነት በአንዳች ምክንያት ሳይስተጓጎል፣ ለአካባቢው ያለው ውክልናም ተከታታይነቱን እንደጠበቀ እስካሁን ዘልቋል፡፡ እንደ እነዚህ ዓይነቶቹ የቦታ ስሞች ለማህበረሰብ፣ ለታሪክና ለስነልሳን ጥናቶች የመረጃ ግብዓትነት ፋይዳቸው የጎላ ሊሆን እንደሚችል ይታሰባል፡፡

**አይጠየፍ፡-**

አይጠየፍ በደሴ ከተማ ምስራቃዊ ክፍል ለሚገኝ ሰፈር፤ በአሁኑ ጊዜ ለአንድ የቀበሌ መስተዳደር የተሰጠ መጠሪያ ነው። የስያሜውን ጊዜ፣ ምክንያትና ትርጉም በሚመለከት የሚያዉቁትን እንዲገልጹ የተጠየቁት መረጃ አቀባዮች የሚከተለውን ብለዋል፡- አይጠየፍ ንጉስ ሚካኤል በ1907 ዓ.ም ያሰሩት የግብር አዳራሽ ነዉ። ንጉሱ ግብር ለማብያ ያሰሩትን አዳራሽ አገሬው አይጠየፍ በማለት ይጠራው ነበር፤ አዳራሹ አይጠየፍ የተባለበት ምክንያት በአንድ በኩል እጅግ ሰፊ በመሆኑ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ግብር ለመብላት የሚገኘውን ሹማምንትና ወታደር፣ ባለርስትና ጪሰኛ፣ ሀብታምና ድሃ ሁሉንንም በአንድ አሰባስቦ የሚይዝ መሆኑ ነው። የታዳሚዎቹ ቦታ እንደ ደረጃቸው ሊለያይ ቢችልም ሁሉም እየገቡ የሚበሉበትና የሚጠጡበት በመሆኑ፣ ወደ አዳራሹ ለመግባት ገደብ የሚጣልበት አለመኖሩን ለመገለጽ አይጠየፍ ተብሎ ተጠራ። ከዚያ በኃላ ለአዳራሹ በተሰጠው ስም አካባቢው፣ አሁን ደግሞ የቀበሌ መስተዳድሩ ይጠራበት ጀመረ (አቶ ሁሴን አየለ፣ አቶ ሰይድ የሱፍ፣ አቶ ተፈራ መላኩ፣ ቃለመጠይቅ፣ ግንቦት 15/2013 ዓ.ም) ።

በዚህ መረጃ መሰረት አይጠየፍ በህዝብ ትዝብትና ግራሞት ለአንድ ትልቅ አዳራሽ የተሰጠ ስም ነው። በቀን 12/10/2013 ዓ.ም ምልከታ ማረጋገጥ እንደተቻለው አዳራሹ በቁመትና በወርዱ እጅግ በጣም ትልቅ የሚባል ነው፤ አልፎ አልፎ ለየት ያሉ ህዝባዊ ስብሰባዎች ይደረጉበታል፤ ለጎብኝዎችም ክፍት ነው። ንጉስ ሚካዔል ለተጠቀሰው ተግባር አዳራሹን ባሰሩበት ጊዜ የአካባቢውን መጠሪያ የሚገልጽ መረጃ ባይገኝም አገሬው ለአዳራሹ የሰጠው ስያሜ የቦታው መጠሪያ ሆኖ መዝለቁ ይነገራል።

እንደመረጃው ከሆነ በንጉስ ግብር ላይ ለመታደም ሀብትም ሆነ ሥልጣን፣ ፀዓዳም ሆነ አዳፋ መልበስ ወዘተ መስፈርት አይደሉም፤ ማንም ማንንም መንቀፍም ሆነ መጠየፍ አይችልም፤ ለዚህ ተግባር የተዘጋጀውና የተገለጹት ትዕይንቶች በተግባር የታዩበት አዳራሽ አይጠየፍ የሚል ስያሜ እንደተሰጠዉ መረጃዉ ያሳያል። ከዚህ በመነሳት አይጠየፍ ውክልናውን አስፍቶ ዛሬ አይጠየፍ አዳራሽ ብቻ ሳይሆን አይጠየፍ ሰፈር፣ አይጠየፍ ቀበሌ መስተዳደር እየተባለ ይገለጻል፤ ቃሉ ውክልውን ማስፋት ብቻ ሳይሆን ለለውጥ ሳይጋለጥ ተከታታይነቱን ጠብቆ እስካሁን መዝለቅም ችሏል።

**ጦሳ ተራራ፡-**

ጦሳ ለተራራ የተሰጠ ስያሜ ሲሆን በምስራቅ አቅጣጫ ደሴ ከተማን ቁልቁል እያየ፣ አዘዋ ገደልን በአሻጋሪ እየተመለከተ በሰሜን ከአምባሰል ተራሮች ጋር የሚገጥም ሰንሰለታማ ተራራ ነው። ለተራራው ስያሜ ምክንያቱና ትርጉሙ ምንድነው? ተብለው የተጠየቁት መረጃ አቀባዮች የሰጡት ምላሽ እንደሚከተለው ቀርቧል።

"ጦሳ በተለያዩ ዕጽዋት የተሸፈነ ተራራ ነበር፤ በተለይ አናቱ ደጋማ ስለሆነ ከፍተኛ ዝናብና ብርድ ስላለው ጦስኝ የሚባል ዕጽዋት በብዛት ይበቅልበት እንደነበር ይነገራል። የአካባቢዉ ነዋሪዎች ጦስኝን በቅመምነት ለመጠቀም ወደተራራው እየሄዱ ይለቅሙ ነበርና ተራራዉ የጦስኝ መገኛ ነው የሚል ግንዛቤ በመያዛቸው ምክንያት ተራራው ጦሳ የሚል ስያሜ እንዳገኘ አባቶች ይነግሩን ነበር" (አቶ ሁሴን አየለ፣ አቶ ጋሹ ሀይሌ፣ አቶ ሰይድ የሱፍ፣ ቃለመጠይቅ፣ ግንቦት 15/2013 ዓ.ም)።

ጦሳ የሚለው ስም ጦስኝ ከሚለው ነባር ስም የተመሰረተ ይመስላል፤ የምስረታው ሂደት ስነልሳናዊ ድጋፍ ባይኖረውም። የመረጃ ሰጪዎቹ ሃሳብም ይህንኑ የሚያረጋግጥ ነው። ለስያሜው መነሻ ምክንያት የሆነው የዕጽዋቱ (ጦስኝ) በተራራው ላይ መገኘት ነው። የተራራዉ ከፍታ በውል የሚታወቅ ባይሆንም ለደሴ ከተማ ግርማ ሞገስነቱ ጥያቄ ውስጥ አይገባም፤ ጦሳ የከተማዋ ዉበት ነዉ ይባላል። የዚህ ስያሜ ጥንታዊነት ለለውጥ አለመጋለጡንና ተከታታይነቱን ያመላክታል። በአሁኑ ጊዜ ጦሳ የሚለው ስም ውክልናው ለተራራው ብቻ የተወሰነ አይደለም፤ ለተለያዩ የንግድ ተቋማት፤ ለምሳሌም ለህክምና ተቋም፣ ለትምህርት ቤት፣ ለሆቴል (ጦሳ ሆስፒታል፣ ጦሳ ፔንሲዮን፣ ጦሳ ትምህርት ቤት፣ ጦሳ ሕንጻ ወዘተ መጠሪያ ሆኖ እያገለገለ ይገኛል።

ከዚህም በተጨማሪ ጦሳ ተራራን ወሎዬ በጸሎቱ ሲመጀንበት (ጦሳ ተራራ መጀን)፣ እንከን የገጠመው፣ መሰናክል የበዛበት አፍቃሪ የመሰናክሉን ክብደት በንጽጽር ለመግለጽ፤

የጦሳን ተራራ ዝንጀሮ አይወጣውም፣
የተፋቀረ ሰው እንከን አያጣውም።

በማለት በስነቃል (በቃል ግጥም) ውስጥ ሲጠቀምበት ይታያል።

**ዳዉዶ፡-**

ዳውዶ በደሴ ከተማ ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ ጦሳ ተራራን ተንተርሶ የሚገኝ ሰፈር ስም ነው፡፡ ዳውዶን በተመለከተ ስለስያሜውና አሰያየሙ መረጃ አቀባዮች የሚከተለውን መረጃ ሰጥተዋል፡፡ ”በዚህ አካባቢ ሸህ ዳዉድ የሚባሉ በነዋሪው ዘንድ በመልካም ምግባራቸው ተወዳጅ የሆኑ የሃይማኖት አባት ይኖሩ ነበር፤ ሸህ ዳውደ ከሰፈራቸው አልፎ በከተማው በአብዛኛው ሰው የሚታወቁ፣ የሚወደዱና የሚከበሩ ነበሩ፡፡ ከዚህ በመነሳት በጦሳ ግርጌ በባህር ዛፍ ደን ተሸፍኖ የሚገኘውና ጥቂት ሰዎች ይኖሩበት የነበረው ሰፈር በስማቸዉ ዳዉዶ ተብሎ ተጠራ፤ ዛሬ ትልቅ መንደር ሆኖም የሚታወቀው በእሳቸው ስም ነው፡፡” (አቶ አያሌዉ ይማም፣ ወ/ሮ ዙሪያሽ ካሳ፣ አቶ ፈንታሁን ይመር፣ ሸህ ሰይድ የሱፍ…የቡድን ዉይይት፣ መጋቢት 10/2014 ዓም)፡፡

መረጃ አቀባዮቹ እንደገለጹት ዳውዶ ጦሳ ተረራን አሻቅቦ እያዬ በስጋት ቀጠና ውስጥ የሚገኝ የባህር ዛፍ ተክል የበዛበት አካባቢ ነው፡፡ በተፈጥሯዊ የመሬት መንሸራተት ወይም በዝንጀሮ መንጋ ከተራራው በሚወርድ የቋጥኝ ናዳ ለጥፋት የተጋለጠ አካባቢ ነው፡፡ ሆኖም የአካባቢው ስያሜ ከመልከዓምድራዊ ገጽታው ወይም ከነዋሪው ስጋት ጋር የተያያዘ ሳይሆን በአንድ ወቅት በአካባቢው ይኖሩ ከነበሩ ግለሰብ ስም ጋር የተቆራኘ ነው፡፡ “ለስሟ መጥሪያ ቁና ሰፋች” እንዲሉ የሸህ ዳዉድ ምግባር ምን ያህል በነዋሪው ልብ ውስጥ ቢገባ ይሆን? ስማቸው ህያው ሆኖ ይኖር ዘንድ ለአካባቢው በውክልና እንዲቆም የተደረገው? መረጃ አቀባዮቹ ግለሰቡ በለጋስነታቸው፤ በአስታራቂነታቸውና በስነ ምግባራቸው የታወቁና አንቱታን ያተረፉ ነበሩ በማለት የገለጹት ጥያቄውን የመለሰው ይመስላል፡፡

በሌላ በኩል ሸህ ዳውድ የመጀመሪያው ነዋሪ በመሆናቸው ሰፈሩ በስማቸው እንደተጠራ የሚናገሩ ሰዎች እንዳሉ አጥኚዋ ሰምታለች፤ በቦታው ስም ላይ (ዳውድ - ዳውዶ) ለሚታየው ለወጥ ስነልሳናዊ ምክንያት ማቅረብ ባይቻልም ነዋሪው ከውዴታውና አክብሮቱ የተነሳ ለቁልምጫ ሲል እንደፈጠረው መገምት ይቻላል፡፡ ዳውዶ ከሰፈር መጠሪያነት አልፎ የቀበሌ፣ የመስጅድ፤ የትምህረት ቤት እና የተለያዩ የንግድ ድርጅቶች ስም በመሆን ውክልናውን አስፍቶ ይገኛል፤ የስያሜው ምክንያትና ትርጓሜ፤ የአገልግሎቱና የውክልናው ስፋት እንደተጠበቀ ሀኖ ለለውጥ የሚያጋልጥ አሉታዊ አመለካከት ሳይፈጠርበት ተከታታይነትን ጠብቆ ይገኛል፡፡

**በርበሬ ገንዳ፡-**

ይህ የከተማው ክፍል ኮማሪቶችና ሴተኛ አዳሪዎች በብዛት የሚኖሩበት፣ መሸታ ቤቶች የተስፋፉበት ሰፈር ነበር። በመጠጥ (በአብዛኛው ጠጅ) ስካርና በሴትኛ አዳሪ ምክንያት የሚፈጠሩ አምባጓሮዎች የአካባቢዉ ልዩ ገፅታ ነበሩ። በወቅቱ የራስ ከበደ መንገሻ አጋፋሪ የነበሩት ፊታዉራሪ ጉድቢያዉ የሰፈሩን የዘወትር የሰካራም ግርግር፣ ረብሻ፣ ጨኸትና ኡ ኡታ ታዝበው፤ "ምን ይሄ መከራ የማይጠፋበት በርበሬ ገንዳ የሆነ ቦታ ነዉ።" አሉ። በእዚሁ ምክንያት ሰፈሩ እስካሁን በርበሬ ገንዳ እየተባለ ይጠራል። (አቶ ተፈራ መላኩ፣ ሽህ ሰይድ የሱፍ፣ ቃለመጠይቅ፣ ሀምሌ 29/2013 ዓ.ም)

በርበሬ ገንዳ ከሁለት ጥምር ቃላት የተገኘ ስም ነዉ ። ገንዳ የኦሮምኛ ቋንቋ ቃል ሲሆን ትርጉሙም ሰፈር፣ መንደር ወይም ቀበሌ ማለት ነዉ። የአማርኛ ቃል የሆነው በርበሬ ደግሞ በፍካሬው፣ ጠብ ጫሪ፣ ነገር ፈላጊ፣ አምባጓሮ ፈጣሪ ወዘተ የሚል ፍች ይሰጣል። በተገለጸው የቦታ ስያሜ ውስጥም በርበሬን የሰፈሩን ሁከት ለመግለፅ በዉክልና የገባ ይመስላል። አካባቢው ስያሜዉን ያገኘበት ምክንያትም፤ በወቅቱ ሰፈሩ የሴተኛ አዳሪዎችና የመሸታ ጠማቂዎች መኖሪያ በመሆኑ ረብሻና ጫከት የማይለየው መሆኑ ተጠየቁን ተገቢ ያደርገዋል።

በአሁኑ ጊዜ አካባቢው የንግድ ማእከል እና የመኖሪያ ቦታ ነዉ። በአካባቢው የስያሜዉ ምክንያቶች የሆኑት አሉታዊ ድርጊቶች ባይቀጥሉም ስያሜዉ ሳይለወጥ ተከታታይነቱን እንደጠበቀ ይገኛል። ምናልባት የተከታታይነቱ ወይም ለለውጥ ያለመጋለጡ ምክንያት የስሙ ትርጓሜ ከግለሰብም ሆነ ከቡድን ማንነት ጋር የማይገናኝ መሆኑ፣ የአሁኑ ነዋሪ የስያሜውን አንድምታ አለመገንዘቡ ወይም እንዲህ አይነት ጉዳዮች ደንታ የማይሰጡት መሆኑ ሊሆን ይችላል።

**ሙሽራዉ ድንጋይ፡-**

የዚህ የቦታ ስያሜ ከአፈ ታሪክ ትርክትና ትእምርት ጋር ይያያዛል። ለትርክቱ በማስረጃነት የሚጠቀሱት ደግሞ በቦታው ላይ የሚገኙትና በሙሽሮች የተመሰሉት የቆሙ ደንጋዮችና ወደ ድንጋይነት የቀየራቸው ርግማን ናቸው። ይህን አስመልክተው የመረጃ ምንጮች የሰጡት መረጃ የሚከተለው ነው።

"የአካባቢውን ስም በሚመለከት በአፈ ታሪክ የሰማነው በአካባቢው አንድ አዋቂ (ወልይ ሊሆን ይችላል) ሰው ነበሩ። ይህ ሰው በዚያ አካባቢ ያልፉ በነበሩ ሙሽሮች

ላይ በሆነ ምክንያት ይቀየማሉ፤ በዚህም ሙሽሮቹን ይረግሟቸውና ድንጋይ ይሆናሉ። በቦታው ላይም የቆሙ የድንጋይ ምስሎች ይታያሉ፤ ይህ ቦታ አሁንም ሙሽራው ድንጋይ እየተባለ ይጠራል።" (አቶ ተፈራ መላኩ፣ አቶ መሀመድ ይመር፣ አቶ ሙህዲን ሀሰን፣ ቃለመጠይቅ፣ ሀምሌ 29/2013 ዓ.ም) ።

በምልከታም ማረጋገጥ እንደተቻለው ቀለም ሜዳ እየተባለ በሚጠራው ቦታ በሰው ምስል የቆሙ ድንጋዮች ይገኛሉ፤ ከመረጃ አቀባዮች በተገኘው መረጃ መሰረት እነዚህ ድንጋዮች በአካባቢው ሲያልፉ የነበሩ ሰርገኞች አንድን ወልይ (ታላቅ ሰው) በሆነ ምክንያት በማስቆጣታቸው በእርግማን የተቀየሩ ምስሎች መሆናቸውን ያመለክታል። ከሰው ወደ ድንጋይ እንደተለወጡ የሚተረክላቸው ምስሎች አንድ ሙሽራን ያጀበ ሰርገኛ ሊኖሩት የሚችሉትን የሰዎች ብዛት የያዙ ይጠቁማሉ፤ የአካባቢው ሰዎች ምስሎቹን በማየት ሙሽሮችንና የሰርገኛ ሚና ያላቸውን በመጠቆም የሚገልጹበት ሁኔታም ይታያል። (ምልከታ፣ ነሀሴ/12/2013 ዓ.ም)

በዚህ የአፈ ታሪክ መረጃ መሰረት ሙሽራው ድንጋይ ለሚለው የቦታ ስያሜ በምክንያትነት የሚጠቀሱት ሁለት ጉዳዮች ናቸው፤ አንደኛው በአካል የሚታዩት የሙሽሮቹ ምስሎች ወይም ትዕምርቶች ሲሆኑ ሁለተኛው ደግሞ በአካባቢው ይኖሩ የነበሩት ታላቅ ሰው በሙሽሮቹ ላይ ያሳለፉትን እርግማን የሚተርከው አፈታሪክ ነው። በዚህ መሰረት ሁኔታው እንደተከሰተ ከሚታሰብበት ጊዜ ጀምሮ የአካባቢዉ ስም ሙሽራዉ ድንጋይ እየተባለ መጠራት ጀመረ። ይህ ስያሜ ለማህበረሰቡ ትዕምርታዊ አገልግሎት ያለዉ ይመስላል። የሙሽሮቹን ወደ ድንጋይነት መቀየር ቦታዉ ላይ ያለዉ ትክል ድንጋይ በዉክልናነት ተቀምጧል። ማህበረሰቡ ለትልልቅ ሰዎች ከፍተኛ የሆነ አክብሮት አለዉ። እርግማናቸዉም እንደሚደርስ ያምናል፤ በዚህም ልጆቻቸዉን መልካም ስነምግባርን፣ ታላላቆችን ማክበርን ለማስተማር ይገለገሉበታል። ይህ ሞራላዊና ማህበራዊ ፋይዳውም ስያሜዉ ለለውጥ ሳይጋለጥ ተከታታይነትን ጠብቆ እስካሁን እንዲዘልቅ ምክንያት ሊሆነው እንደቻለ መገመት ይቻላል።

**አጣሪ ገንዳ፡-**

አጣሪ ገንዳ የደሴ ከተማ ደቡብ ምዕራባዊ አካባቢ ነው። መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ከሰሜን እስከ ደቡብ ጫፍ በተዘረጋው የሲራራ ንግድ መስመር ደሴ በተለይም ቦሩ በማዕከልነት ይጠቀሳል፤ የአገሬው ተዋናይነትም ትልቅ ድርሻ አለው። ነጋዴው ጉዞው ብቻ ሳይሆን በተለይም በከተማ ኑሮውም ቡድናዊ ባህሪ

ያለው በመሆኑ በተቀራራቢ አካባቢ ይከትም ነበር፤ በዚህ የተነሳ ነጋዴዎች የሚኖሩበትን አካባቢ ማህበረሰቡ አጣሪ ገንዳ እያለ መጥራት መጀመሩን የተገኙት መረጃዎች ያሳያሉ:: (አቶ ተፈራ መላኩ፣ አቶ እብራሂም ሁሴን፣ አቶ ሁሴን አየለ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ሀምሌ 29/2013 ዓ.ም)

ከሰነድ ፍተሻ የተገኘ ሌላ መረጃ ደግሞ አጣሪ ገንዳ ማለት የነጋዴ መከማቻ ወይም ሰፈር ማለት ነዉ። በዘይላ በኩል ከሀረር በምስራቅ የሚገባዉና የሚወጣዉ ምርትና ሸቀጥ በመጀመሪያ አጣሪ ገንዳን መዳረሻ ያደረገ ነበር። በዚህ የመገበያያ ስፍራ ላይ ነገዴዎች ሸቀጦቻቸዉን የሚያጣሩበት/የሚሸጡበት እና የመንግስት ግብር ሰብሳቢዎች ቀረጥ የከፈለዉን ካልከፈለዉ እያጣሩ የሚያስተላልፉበት የገበያ ስፍራ በመሆኑ አጣሪ ገንዳ የሚለዉን ስያሜ ሊይዝ ችሏል። በማለት ያስረዳል (ፀጋዉ መኮነን፣ ሰነድ ፍተሻ፣ 2005 ዓ.ም)

ከላይ በተጠቀሱት መረጃዎች መካከል መጠነኛ የውክልና ልዩነት የሚታየ ይመስላል:: በመጀመሪያው መረጃ የቃሉ ውክልና ለመኖሪያ ቦታ ሲሆን የሁለተኛው ግን ለገበያ ሥፍራ ነው:: ሁለተኛው የሰነድ መረጃ ሚዛን የሚደፋ ቢመስልም ምንጩ ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው ሰዎች ናቸው ከመጀመሪያው የተለዩ አስረጅነት ያለው አይመስልም:: የተጣማሪ ቃላቱን ፍቺዎች (አጣሪ - ነጋዴ፤ ገንዳ - ሰፈር ወይም መንደር) ስናጤን የስያሜው ውክልና ለንግድ ቦታ ሳይሆን ለነጋዴ መንደር ወይም መኖሪያ ተገቢ ሆኖ እናገዋለን። ስለዚህም አጣሪ ገንዳ በንግድ ሥራ የተሰማሩ ቡድኖች በአካባቢው መኖር ከመጀመራቸው ጋር ተያይዞ የተሰጠ ስም መሆኑን እንገነዘባለን፤ ስያሜውም ከኦሮሞ መስፋፋት ጋር ተያይዞ በተፈጠረ የቋንቋዎች ንክኪ የተፈጠረውን ስነልሳናዊ ውሰት ከማሳየት ባሻገር ለታሪካዊ ምርምር መረጃም የሚሆን ይመስላል:: የቃላቱ ፍች ውሰተን፣ ማህበራዊ መስተጋብርን ከማመልከት ባሻገር ከማህበረሰብ ማንነት፣ ስነልቡና ወዘተ ጋር የተያያዘ አሉታዊ አንድምታ የሌለው መሆኑ አጣሪ ገንዳ የሚለዉ ስያሜ ተከታታይነቱን ጠብቆ ለመዝለቁ በምክንያትነት ሊጠቀስ ይችላል።

**ጀሚ፡-**

ጀሚ የተባለዉ ቦታዉ ላይ የእስረኞች መቀጫ ወህኒ ቤት ስለተሰራ ነዉ። በስርቆትና በዘረፋ፣ ሰዉ በመደብደብና በመግደል የተጠረጠረ ግለሰብ፣ በፍርድ ቤት ቅጣት የተወሰነበት ወንጀለኛ ከማህበረሰቡ ተገልሎ እንዲቆይ የሚደረግበት ሥፍራ ወህኒ ቤት፣ ጀሚ፣ ከርቸሌ እየተባለ ይጠራል። በወቅቱ ጀሚ የገደለ እድሜ ይፍታህና

ሞት፣ የሰረቀ ሌባ 40 ጅራፍ ወዘተ እንዲቀጣ እየተፈረደበት የሚታረምበት ተቋም መጠሪያ ነዉ፡፡ በዚህም አንድ ወንጀለኛ ተይዞ ሲታሰር ጀሜ ወረደ ተብሎ ይነገር ነበር፤ በዚህ ምክንያት የሰፈሩ ስም ጀሜ ተባለ፡፡ (ሸህ ሰይድ የሱፍ፣ አቶ እብራሂም ሁሴን፣ አቶ አያሌዉ ይማም፣ ወ/ሮ ዙሪያሽ ካሳ፣ ቡድን ዉይይት፣ መጋቢት 10/2014 ዓ.ም)

ከዉይይቱ የተገኘዉ መረጃ እንደሚያሳየዉ በአካባቢው ማህበረሰብ አጠራር ጀሜ ማለት ማረሚያ ቤት ነው፡፡ በንጉሱ ዘመን በወሎ ጠቅላይ ግዛት ውስጥ በወንጀል የተጠረጠሩና ወንጀል የሰሩ ሁሉ የሚታሰሩበትና ከከተማው ወጣ ባለ ቦታ የተሰራው ማረሚያ ቤት (ጀሜ) ወደሌላ ቦታ ከተዛወረ ዘመናትን አስቆጥሯል፤ አካባቢው ግን አሁንም ጀሜ በሚለው ስም እየተጠራ ይገኛል፡፡

ጀሜ የሚባለው አካባቢ ከደሴ ከተማ በስተደቡብ አቅጣጫ የሚገኝ ሲሆን ከቦታው ስፋት አኳያ በአሁኑ ጊዜ በሁለት ተከፍሎ ላይኛውና ታችኛው ጀሜ እየተባለ ይጠራል፡፡ ስያሜዉ ሳይለወጥ ተከታታይነትን ጠብቆ የሚገኝ ሲሆን ለዚህም ማህበረሰቡ ቃሉን በአሉታዊ አንድምታው ያልወሰድውና እንደችግር ያላየው መሆኑ በምክንያትንነት ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**አሸብር ጎራ፡-**

የስያሜውን ምክንያት እንዲገልጹ የተጠየቁት መረጃ ሰጪዎች የሰጡት መልስ የሚከተለው ነው፡፡ ድሮ የሞት ፍርድ የተበየነበት ወንጀለኛ በስቅላት ይቀጣ ነበር፤ ስቅላቱ ይፈጸም የነበረም ሰው ከሚኖርበት ራቅ ወዳለ ቦታ ተወስዶ ስለነበር ከከተማው በደቡብ አቅጣጫ የሚገኘው ተራራ ለዚህ እንደተመረጠ ይነገራል፡፡ የስቅላት ቅጣቱ በሚፈጸምበት ጊዜ በአካባቢው ጩኸትና ግርግር ይፈጠር ስለነበር ተራራው አሸብር ጎራ ተባለ (ሸህ ሰይድ የሱፍ፣ አቶ አያሌዉ ይማም፣ አቶ ፈንታሁን ይመር፣ ቃለመጠይቅ፣ መስከረም 16/2014) ፡፡

ከላይ ከቀረበው መረጃ መረዳት እንደሚቻለው ስያሜው ጩከት፣ ግርግርና ሽብር የሚበዛበት የሽብር አካባቢ መሆኑን ለማመልከት የተሰጠ ይመስላል፡፡ እዚህ ላይ ስለ ሰኞ ገበያ በቀረበው መረጃ ወንጀለኛ በስቅላት በገበያው መካከል ተሰቅሎ ለገበያ የመጣው ህዝብ እንዲማርበት ይደረግ እንደነበር ተመልክተናል፤ በዚህ መረጃ ግን በተቃራኒው ሰው በማያይበት ተራራ ላይ ስቅላት ይፈጸም እንደነበር መጠቀሱ በመካከላቸው አንድም የዘመን ልዩነት መኖሩን፣ አለያም በመረጃዎቹ ተዓማኒነት ላይ ጥያቄ ሊነሳ መቻሉን ያመለክታል፡፡ ይሁን እንጂ በስያሜው ትርጓሜና

በምክንያቱ ላይ ከተገኘው መረጃ ቦታው ከሰዎች መኖሪያ የራቀ፣ በአሁኑ ጊዜ የሙስሊሙ ማህበረሰብ የመቃብር ቦታ ሲሆን በደን የተሸፈነና አስፈሪ ድባብ የሚስተዋልበት መሆኑ ለስያሜው የተለየ ምክንያት ይኖረው ይሆን? የሚል ጥያቄ እንድናነሳ የሚያደርግ ይመስላል፡፡

**ሸርፍ ተራ፡-**

ከከተማዋ መቆርቆር ጋር አብሮ የተመሰረተና የንግድ እንቅስቃሴ ይደረግበት የነበረ ሰፈር ነዉ፡፡ታዲያ በዚህ የንግድ ቦታ ድፍን ብር ወደ ሸርፍ/ዝርዝር ብር የተዘረዘረዉን ብር ወደ ሳንቲሞች የሚሸረፍበት /የሚዘረዘርበት/ስፍራ ነበር፡፡ ሸርፍ ተራ በወቅቱ ከፍተኛ የሆነ ግብይትና የገንዘብ ምንዛሬ ልዉዉጥ ይደረግበት ስለነበር ቦታዉ ሸርፍ ተራ በመባል እስከ ዛሬ ድረስ ስያሜዉን እንደያዘ ይገኛል፡፡

ይህን አስመልክቶ ከቃለመጠይቅ የተገኘዉ መረጃ እንዲህ ይላል፡- ሸርፍ ተራ ከ1936 ወዲህ ነዉ የተመሰረተዉ ማለትም ማርትሬዛ (ጠገራ ብር) ከመገበያያነት ከተወገድ በኃላ ነዉ፡፡ ሸርፍ ተራ የተባለዉ የንግድና የምንዛሪ ልዉዉጥ ይደረግበት ስለነበረ ነዉ፡፡ እዚህ ስፍራ ላይ ጠገራ ብር ይለወጥበታል፣ የጦር መሳሪያ ይነገድበታል፣ የተለያዩ ሸቀጦች ይሸጡበታል፡፡ ቦታዉ ላይ ሁል ጊዜ ግርግር አይጠፋዉም፣ አሁንም ተመልክተሸ እንደሆነ ሰዉ ቀኑን ሙሉ ሲዋከብበት ይዉላል (አቶ ተፈራ መላኩ፣ ሸህ ሰይድ የሱፍ፣ አቶ ከበደ ሩፌ፣ ቃለመጠይቅ፣ ሀምሌ 29/2013) ፡፡

መረጃዉ እንደሚያሳየዉ ሸርፍ ማለት ዝርዝር ማለት ሲሆን ቦታዉ ላይ የጠገራ ብር ይቀየርበት ወይም ይዘረዘርበት ነበር፡፡ በተጨማሪም የተለያዩ የጦር መሳሪያዎችን እና ሸቀጦችን ይገበያዩበት እንደነበር ለማወቅ ተችሏል፡፡ በዚህ ምክንያትም ሸርፍ ተራ የሚለዉን ስያሜ ያገኘ ይመስላል፡፡ይህ ስፍራ አሁን ድረስ በከተማይቱ ከፍተኛ የሆነ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ የሚካሄድበት ቦታ ነዉ፡፡ ስያሜዉንም ሳይቀይር ለረጅም ጊዜ እንደያዘ ቆይቷል፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት ደግሞ ስፍራዉ ላይ አሁንም ድረስ ከፍተኛ የሆነ የገበያ እንቅስቃሴ ስላለ ይመስላል፡፡

**አሬራ ውሃ፡-**

አሬራ ዉሃ ህዝቡ አሳጥሮ አሬራ ይለዋል፡፡ አሰያየሙን በሚመለከት ሁለት አስተያየቶች ይሰጣሉ፡፡ አንደኛዉ የአካባቢዉ ስያሜ መነሻ ወ/ሮ መሬማ ከተባሉ ባለብዙ የቀንድ ከብት ባልተቤት ሴት ጋር እንደሚያያዝ ይነገራል፡፡ መረጃ ሰጪዎች ወ/ሮ መሬማ በአካባቢው የቀንድ ከብቶችን እያረቡ የሚኖሩና ወተት በብዛት

የሚያልቡ እንደነበሩ ይገልጻሉ፡፡ እንደዛሬው ወተት መሸጥ የተለመደ ስላልነበረ ቅቤዉን አዉጥተዉ አሬራዉን የሚጠጣው ስላልነበረ ይደፉት ነበር፡፡ ከዚህም በመነሳት ሰፈሩ አሬራ እየተባለ መጠራት እንደጀመሩ ይነገራል (አቶ ተፈራ መላኩ፣ ወ/ሮ ጥሩየሱፍ ወራቂ፣ አቶ መሀመድ ይመር፣ ቃለመጠይቅ፣ ሀምሌ 29/2013 ዓ.ም)፡፡

ሌሎች የሰነድ መረጃ ምንጮች ደግሞ አካባቢውን አዘቅዝቆ ከሚያየው የአዝዋ ገደል ተራራ ሥር የሚመነጨው ውሃ የአሬራ መልክ የያዘ ስለነበር ምንጩ አሬራ ዉሃ ተብሎ ተሰየመ፤ ከዚህ በመነሳትም አካባቢው አሬራ ውሃ እየተባለ መጠራት ጀመረ በማለት ይገልጻሉ (ሰነድ ፍተሻ፣ ፀጋዉ መኮነን፣ 2005)

አሬራ ውሃ ከደሴ ከተማ በሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ፤ የቦርከና ወንዝ በፈጠረው ሸለቆ ለሁለት ተከፍሎ ዶሮ መዝለያ እየተባለ በሚጠራው የአዘዋ ገደል ተራራ ግርጌ የሚገኝ አካባቢ ነው፡፡ ቀደም ሲል አካባቢው በበሃርዛፍ ደን ውስጥ አልፎ አልፎ የተሰሩ ጥቂት ቤቶች ብቻ የነበሩበት ሲሆን የከተማውን መስፋትና የህዝቡን ብዛት ተከትሎ በተካሄደው የቦታ ምሪት ዛሬ በመኖሪያ ቤት ተጨናንቆ ይታያል፡፡ ከላይ እንደተገለጸው የአካባቢውን ስያሜ በሚመለከት ከመረጃ አቀባዮች ሁለት የተለያዩ የአፈ ታሪክ መረጃዎች ተገኝተዋል፤ አንደኛው ከምንጩ ውሃ ቀለም ጋር፡ ሌላው ከብት አርቢዋ ከምታፈሰው አሬራ ጋር ተያይዞ የተነገረው ነው፡፡ ይህ ስያሜ ብዙ የማህበረሰብ ክፍልን አክቶ ለያዘው አዲስ ሰፈር መጠሪያ ሆኖ በማገልገል ላይ ይገኛል፡፡ ነባሩ ስያሜ ለለውጥ ሳይጋለጥ ተከታታይነትን ጠብቆ መቆየትና በማህበረሰቡ ዘንድ ቅቡል እንዲሆን ያደረገው ከማንነትና ከስነልቡና ተጽእኖ ጋር የተያያዘ አንድምት የሌለው መሆኑ በምክንያትነት ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**አገር ግዛት፡-**

‘ይህ አካባቢ በሀይለስላሴ ዘመነ መንግስት የአገር አስተዳደር ሚኒስትሩ መቀመጫ ነበር፡፡ አገር ግዛት የተባለዉ የጠቅላይ ገዥዉ መኖሪያና ቢሮ ቦታዉ ላይ ስለነበር ነዉ፡፡ የገዥዉም መኖሪያ እዛዉ አካባቢ ስለነበር የሰፈሩን ስም አገር ግዛት በማለት ተሰየመ” (አቶ ተፈራ መላኩ፣ ወ/ሮ ጥሩየሱፍ ወራቂ፣ አቶ መሀመድ ይመር፣ ቃለመጠይቅ፣ ሀምሌ 29/2013 ዓ.ም) ፡፡

አገር ግዛት በጦሳ ተራራ ግርጌና በሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ የሚገኝ የከተማው ክፍል ነው፡፡ በተገኘው መረጃ መሰረት አካባቢው ስያሜውን ያገኘው በቦታው ላይ ከተሰራው የወሎ ጠቅላይ ግዛት አስተዳደር ጽህፈት ቤት ነው፡፡ በወቅቱ በንጉሡ የሚሾመው

ግለሰብ ጠቅላይ ገዥ፤ የሚያስተዳድረው ክልልም ጠቅላይ ግዛት ይባል ስለነበር የቦታው ስያሜ ከዚሁ እንደመነጨ ይነገራል፡፡

አገር ግዛት ለአንድ መስሪያ ቤት መጠሪያነት ከመወከል አልፎ የአካባቢ፤ በአሁኑ ጊዜ ደግሞ ለአንድ ሰፈ ቀበሌ መጠሪያ በመሆን ውክልናውን አስፍቶ ይገኛል፡፡ በዚህም ተከታታይነቱን ጠብቋል ማለት ይቻላል፡፡

**መርሆ ግቢ፡-**

መርሆ ግቢ በሀይለስላሴ ዘመነ መንግስት የልዑል አልጋ ወራሽ አስፋዉ ወሰን ግቢ ወይም ቤተ መንግስት ነበር፡፡ በደርግ ጊዜ ደግሞ የደርግ የመጀመሪያ ሹማምንት ዘመቻ መምሪያ ሆኖ ነበር፡፡ በ1967 ዓ.ም በመላዉ ሀገሪቱ እድገት በህብረት በሚል ስያሜ ዘመቻ ተደርጎ በነበረበት ጊዜ ዘማቾች ከአዲስ አበባ እየመጡ ወደ ግቢዉ እንዲገቡ ተደርጎ ተጨማሪ መመሪያ እየተሰጣቸዉ ወደ ተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ይሰማሩ ነበር፡፡

በአጠቃላይ ይህ ቤተ መንግስት ከመነሻዉ እስከ ደርግ ዉድቀት ድረስ የተለያዩ የመንግስት መመሪያዎች የሚወጡበትና የተለያዩ የመንግስት አመራሮች ፖለቲካዊ ስራዎቻቸዉን የሚያከናዉኑበት ግቢ ነበር፡፡ በዚህም መርሆ ግቢ እየተባለ አሁን ድረስ ይጠራል፡፡ (አቶ ተፈራ መላኩ፣ አቶ እብራሂም ሁሴን፣ አቶ ሊበን አራጋዉ፣ ቡድን ዉይይት፣ መጋቢት 25/2014 ዓ.ም)

መረጃዉ እንደሚያሳየዉ በዘመኑ የነበሩ አመራሮች መመሪያዎችን ወይም ደንቦችን የሚያወጡት እዚህ ግቢ ዉስጥ ነዉ፡፡ በዚህም መርሆ ግቢ ማለት መርህ ወይም መመሪያ የሚወጣበት ቦታ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ጊቢዉ በጣም ሰፊ እና በዉስጡም የተለያዩ ክፍሎች አሉት፡፡ እንደ ባዛር እና መሰል ዝግጅቶች ይከወኑበታል፡፡ አሁን ላይ ጊቢዉ ለወይዘሮ ስኅን ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ እንደ ተጨማሪ ካምፓስ በመሆን እያገለገለ ይገኛል፡፡ ስያሜዉን ካገኘ ጀምሮ የአካባቢዉም ስም መርሆ ግቢ እየተባለ ይጠራል፡፡ ስያሜዉንም ሳይቀይር ተከታታይነቱን ጠብቆ ይገኛል፡፡

## 5.2. የቦታ ስሞች ለዉጥና የለዉጥ ምክኒያቶቻቸዉን የሚመለከት መረጃዎች ትንተና

የቦታ ስሞች በተለያዩ አጋጣሚዎች እና ምክንያቶች ይለወጣሉ፡፡ ማህበረሰቡ ስያሜን ሲሰጥ የመልከዓምድር አቀማመጥ፣ ማህበራዊ አጋጣሚ፣ ባህላዊ እሴቱን፣ ወዘተ

መነሻ አድርጎ ሲሆን ለስያሜ መለወጥም ልዩ ልዩ ምክንያቶች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ የስያሜ ለውጥ ምክንያቶች ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ ስነልቦናዊ፣ ሀይማኖታዊ፣ አስተዳደራዊ ወዘተ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ከአንድ ስርዓት ወደሌላ በሚደረግ ሽግግር አዲሱ ከማይቀበላቸው ርዕዮተ ዓለማዊ ሁኔታዎች ጋር ግንኙነት ያላቸው ነባር ስሞች እንዲለወጡ ይደረጋል፡፡ ከማህበራዊ ቡድኖች ማንነት ጋር የተያያዙና በአንደኛው ቡድን ስነልቡና ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ስያሜዎችም ለለውጥ ይጋለጣሉ፡፡ በአካባቢው ላይ የሃይማኖት ተቋማት ሲስፋፉ፣ የአንድ ዕምነት ተከታዮች በብዛት ሲሰፍሩና አዳዲስ መንደሮች ሲመሰረቱ የነበሩት ስሞች ተቀይረው በአዲስ ሊተኩ፣ ያልነበሩ አዳዲስ ሥያሜዎች ሊሰጡ ይችላሉ፡፡

ከዚህ አንጻር በዚህ ጥናት በደሴ ከተማ ለውጥ የተካሄደባቸው የቦታ ስሞችና የለውጥ ምክንያቶቻቸው ምን ይሆኑ? በሚሉት ጥያቄዎች ላይ ከመረጃ አቀባዮች የተሰበሰቡት መረጃዎች ቀጥሎ ተተንትነዋል፡፡

**ሙጋድ ወደ ጅብሩክ፡-**

ከመረጃ አቀባዮች በተሰበሰበው መረጃ መሰረት፤ ሙጋድ ቀደም ባለው ጊዜ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች የመስቀል ደመራ የሚያቃጥሉበት ቦታ ነበር፤ ከደመራዉ መንደድ ጋር ተያይዞ በአካባቢዉ ከሚፈጠረው ነበልባል ወይም የእሳት ሞገድ በመነሳት አካባቢው ሙጋድ እየተባለ ይጠራ ጀመር፡፡ ከ1928 እስከ 1933 ጣሊያን ሀገራችንን ወሮ በቆየበት ጊዜ ሙጋድ ላይ አንድ የንግድ ማእከል ተቋቋመ፤ ይህ የንግድ ማእከልም ጅብሩክ እየተባለ ይጠራ ጀመር፤ በዚህ ሁኔታ ሙጋድ የሚለዉ ቦታ ጅብሩክ በሚል ተተክቶ መጠራት ጀመረ (አቶ ተፈራ መላኩ፣ ወ/ሮ ጥሩ የሱፍ ወራቂ፣ አቶ መሀመድ ይመር፣ ቃለመጠይቅ፣ ሀምሌ 29/2013 ዓ.ም)፡፡

ሙጋድ የተባለዉ ስፍራ ሸርፍ ተራ አካባቢ የሚገኝ ሲሆን አሁን ላይ ስያሜዉ እንደተለወጠ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ሰነድ ፍተሻዉ እንደሚያሳየዉ ሙጋድ የሚለዉ የቦታ መጠሪያ ወደ ጅብሩክ እንደተለወጠ ነዉ፡፡ የለውጡ ምክንያት ደግሞ የንግድ እንቅስቃሴ መስፋፋት እና ቦታዉ ላይ ትልቅ የገበያ ማእከል መሰራቱ ነዉ፡፡ የገበያ ማእከሉ ጅብሩክ በማለት የተሰየመ ሲሆን ሙጋድ የሚለዉ ስያሜ እየተረሳ መጣ፡፡ አሁን ላይ ግን አራዳ አካባቢ ላይ የተሰራ የገበያ ማእከል አለ መጠሪያዉንም ሙጋድ የገበያ ማእከል በማለት ሰይመዉታል፡፡ ነገር ግን ሙጋድ የሚለዉ የሰፈር ስም ወደ ጅብሩክ መለወጡን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

**ወላሞ ሰፈር ወደ መንበረ ፀሀይ፡-**

ወላይታን የዘመናዊቷ ኢትዮጵያ ግዛት አካል ለማድረግ በተካሄደዉ ዘመቻ ራስ ሚካኤል ከነፊታዉራሪ ገበየሁ፣ ሊቀመኳስ አባተ፣ ደጃች ባልቻ፣ ራስ ወልደ ጊዮርጊስና አባጅፋር ጋር በመሆን ጠንካራዉን የወላይታዎች ምከታ ሰብረዉ መሪዋን ካዎጦናን ማርከዋል፡፡ ራስ ሚካኤል ከወላይታ ሲመለሱ በስጦታ መልክ የተበረከተላቸዉን የወላይታ ምርኮዎች ይዘዉ ነበር ወደ ደሴ የገቡት፡፡ እነዚህን ከወላይታ የመጡ ምርኮዎች በቤተመንግስቱ እንዲያገለግሉ የተለያዩ ሀላፊነቶች ተሰጥቷቸዋል፡፡ ከመካከላቸዉም እስከ ቀኝ አዝማች ማእረግ የደረሱ ነበሩ፡፡በሰአቱ እንዲደርሱና ስራቸዉንም በአግባቡ እንዲወጡ በማሰብ ከቤተመንግስቱ በቅርበት በስተምስራቅ በኩል በሚገኘዉ ቦታ ላይ ቤታቸዉን እንዲሰሩ ተደርጓል፡፡ ቦታዉ ላይ ወላይታዎች በመስፈራቸዉ ምክኒያት ወላሞ ሰፈር እየተባለ ሲጠራ ቆይቷል፡፡ ( ምስጋናዉ ታደሰ፣ ሰነድ ፍተሻ፣ 2013 ዓ.ም፣)

**መንበረ ፀሀይ፡-** የፀሀይ መዉጫ ማለት ሲሆን ወላሞ ሰፈር እየተባለ የሚጠራዉ ሰፈር በደርግ ዘመነ መንግስት ስያሜዉ እንዲቀየር ጥያቄ በመቅረቡ ምክኒያት መንበረ ፀሀይ ተብሎ ተሰይሟል፡፡ አሁን ድረስ ስያሜዉን እንደያዘ ይገኛል (አቶ ተፈራ መላኩ፣ አቶ መሀመድ ይመር፣ አቶ ሰይድ አበጋዝ፣ ቃለመጠይቅ፣ ሀምሌ 29/2013 ዓ.ም) ፡፡

መረጃዎቹ እንደሚያሳዩት ወላሞ ሰፈር ተብሎ የተሰየመዉ ንጉስ ሚካኤል ከወላይታ ያመጧቸዉን ምርኮኞች እንዲያገለግሏቸዉ በማሰብ ከቤተ መንግስታቸዉ አቅራቢያ በሚገኝ ቦታ ላይ ካሰፈሯቸዉ በኂላ ነዉ፡፡ የሰፈሩ ስያሜ በደርግ ጊዜ እንዲቀየር ተደርጓል፡፡ ቦታዉ ላይ በብዛት የደርግ ባለስልጣን ይኖሩበት ነበር እናም ወላሞ ሰፈር የሚለዉን ስያሜ በመቃወም እንዲቀየር ግፊት በማድረግ ስያሜዉ ወደ መንበረ ፀሀይ ተቀየረ፡፡ የለዉጡ ምክንያት ደግሞ የፖለቲካ ሽግግር በመኖሩ እንደሆነ ከመረጃዉ ለማወቅ ይቻላል፡፡ አካባቢዉ ላይ ፀሀይ ቀድማ ትወጣ ስለነበር ለስያሜዉ መነሻ ምክንያት የሆነ ይመስላል፡፡ በአራዳ ክፍለ ከተማ ስር ከሚገኙ ሶስት ቀበሌዎች ዉስጥ አንዱ መንበረ ፀሀይ ቀበሌ ነዉ ፡፡

የወላሞ ሰፈር የስያሜ ለዉጥ መነሻ ምክንያት፡- ይህ ቦታ የመልካአምራዊ አቀማመጡን ስናይ ኮረብታማ ስፍራ ሆኖ ፀሀይ ቀድማ የምትወጣበት በመሆኑ መንበረ ፀሀይ ለሚለዉ ስያሜ መነሻ የሆነ ይመስላል፡፡

ሌላዉ ለውጡ ያመጣዉ ተስፋ ሲሆን የጌታ እና የሎሌ፣ የገዥ እና የተገዥ ንጉሳዊ አገዛዝ የቀየረና የብሄር ብሄረሰቦችን እኩልነት የሚያረጋግጥ የሶሻሊስት ስርአት ለመተካት ለዉጥ የተካሄደ ሊሆን ይችላል፡፡

በተጨማሪም አካባቢዉ ላይ ከወላሞ ከመጡ ቡድኖች ዉጭ የሆነ ማንኛዉም ሰዉ በተለይም ከመጣዉ ስርአት ጋር ስልጣን የተጋሩ ሰዎች በአካባቢዉ መኖር መጀመራቸዉ የ(አናሳ) ብሄረሰቦች መገለጫ ተደርጎ የሚወሰደዉ ስያሜ (ወላሞ ሰፈር) እንዲቀየር ያላቸዉ ፍላጎት ለለዉጡ በምክንያትነት ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**ዘበኛ ሰፈር ወደ መድሃኒያለም፡-**

ዘበኛ ሰፈር ወይም የአሁኑ መድሃኒያለም ሰፈር ከወ/ሮ ስህን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ከፍ ብሎ የሚገኝ ሰፈር ነዉ፡፡ ይህ ሰፈር ስያሜዉን ከዘበኛ ሰፈር ወደ መድሀኒያለም ሰፈር የተቀየረ መሆኑን ከተገኘዉ መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ዘበኛ ሰፈር የእነ ራስ እምሩ፣የእነራስ ከበደ አሽከሮች የሚኖሩበት ሰፈር ነበር፡፡የመንግስት ጠባቂዎች በብዛት ይኖሩበት ስለነበር ዘበኛ ሰፈር እየተባለ ይጠራ ነበር፡፡

መድሃኒያለም፡- ዘበኛ ሰፈር በሚባለዉ አካባቢ የመድሀኒያለም ቤተክርስቲያን በመሰራቱ ምክንያት የሰፈሩ ስያሜ መድሀኒያለም እየተባለ መጠራት ጀመረ፡፡ (አቶ ተፈራ መላኩ፣ አቶ ሰይድ አበጋዝ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ሀምሌ 29/2013 ዓ.ም)

ከቃለ መጠይቁ የተገኘዉ መረጃ እንደሚያሳየዉ ዘበኛ ሰፈር የተባለበት ምክንያት ቦታዉ ላይ የእነራስ እምሩ ፣ የእነራስ ከበደ አገልጋዩች እንዲሁም የመንግስት ጠባቂዎች ወይም ዘበኞች ይኖሩበት ስለነበረ ነዉ፡፡ አሁን ላይ ዘበኛ ሰፈር ተብሎ የሚጠራዉ ሰፈር ወደ መድሀኒያለም መቀየሩን መረጃዉ አመላክቷል፡፡ የለውጡ ምክንያት ደግሞ ቦታዉ ላይ የመድሀኒያለም ቤተክርስቲያን በመገንባቱ ነዉ፡፡ የሀይማኖታዊ ተቋማት መስፋፋት ደግሞ ለስያሜ መነሻ ምክንያት ወይም ለስያሜ የለውጥ ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

**ጨዉ ተራ ወደ ጫት ተራ**

ጨዉ ተራ የተባለዉ ሰፈር ሽርፍ ተራ ዉስጥ ከሚገኙ መንደሮች አንዱ ነዉ፡፡ ቦታዉ ላይ የአሞሌ ጨዉ ንግድ ልዉዉጥ ይደረግበታል፡፡ በዚህም የአካባቢዉ ስም ጨዉ ተራ እየተባለ ይጠራ ነበር፡፡ አሁን አሁን ደግሞ አካባቢዉ ላይ ዙሪያዉን የጫት ገበያ በመስፋፋቱ ምክንያት ጨዉ ተራ የሚለዉ መጠሪያ ስያሜ እየቀረ

ጫት ተራ በሚል ተለዉጧል (አቶ ተፈራ መላኩ፣ አቶ ሰይድ የሱፍ፣ አቶ ሰይድ አበጋዝ ፣ ቃለ መጠይቅ፣ መስከረም 16/2014 ዓ.ም) ፡፡

መረጃ ሰጭዎች እንዳሉት ሸርፍ ተራ ከፍተኛ የሆነ የንግድ እንቅስቃሴ የሚስተናገድበት ሰፈር ነዉ፡፡ በአካባቢዉ ብዙ የንግድ ማእከሎች ያሉ ሲሆን ከነዛ ዉስጥ የአሞሌ ጨዉ ንግድ ልዉዉጥ አንዱ ነዉ፡፡ በዚህ የንግድ እንቅስቃሴ ምክንያት የመንደሩ ስም ጨዉ ተራ እየተባለ ይጠራ ነበር፡፡ ከረጅም አመታት ወዲህ አካባቢዉን የጫት ገበያ ያጥለቀለቀዉ በመሆኑ ጨዉ ተራ የሚለዉ መጠሪያ እየቀረ ጫት ተራ በሚል ተተክቷል፡፡ የዚህ ስያሜ ለውጥ ምክንያት ደግሞ የንግድ እንቅስቃሴ መቀያየር ወይም መስፋፋት ሊሆን ይችላል፡፡

**ግም ዉሃ ወደ ቡና ተራ**

በአካባቢዉ መሀል ለመሃል የሚወርድ ወራጅ ዉሃ ነበር፡፡ በወራጅ ዉሃዉ ላይ የማይደፋ የቆሻሻ አይነት አልነበረም፡፡ የስጋ እጥብጣቢዉ፣የልብስ እጣቢ እንዲሁም የሽንት ቤት ፍሳሽ ይለቀቅበት ነበር፡፡ በጣም ከመሽተቱ የተነሳ ሰዉ አያስቀርብም ፡፡ በዚህ ምክንያት የአካባቢዉ ስም ግም ዉሃ እየተባለ ይጠራ ነበር፡፡

አሁን ላይ በአካባቢዉ የቡና እና የበርበሬ መጋዘኖች በብዛት ተከፍተዉ ከፍተኛ የሆነ የንግድ እንቅስቃሴ አለ፡፡ በዚህ ምክንያት የአካባቢዉ ስያሜ ግም ዉሃ መባሉ እየቀረ ወደ ቡና ተራ በሚል የስያሜ ለዉጥ ተደርጓል፡፡ (ሸህ ሰይድ የሱፍ፣ አቶ ተፈራ መላኩ፣ ወ/ሮ ዙሪያሽ ካሳ፣ ቃለ መጠይቅ፣ መስከረም 16/2014 ዓ.ም)

መረጃዎቹ እንደሚያሳዩት ግም ዉሃ ለሚለዉ ስያሜ መነሻ የሆነዉ በአካባቢዉ ላይ የነበረዉ ወራጅ የሆነ ቆሻሻ ዉሃ ምክንያት ነዉ፡፡ ይህ ቦታ አሁን ላይ የንግድ እንቅስቃሴ ይካሄድበታል፡፡ በመሁኑም አካባቢዉ ላይ ባለዉ ከፍተኛ የሆነ የቡና ንግድ እንቅስቃሴ ምክንያት ግም ዉሃ እየተባለ የሚጠራዉ አካባቢ አሁን ላይ ቡና ተራ እየተባለ ይጠራል፡፡ የለውጡ ምክንያት ደግሞ ቦታዉ ላይ የቡና ንግድ እንቅስቃሴ መስፋፋት ነዉ፡፡

**ቁስ መንደር ወደ ሀያት ሰፈር፡-**

ሃያት ሰፈር ከሰኞ ገበያ ወደ ደቡብ አቅጣጫ ሲሄዱ የቢለን ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያንን አልፎ የሚገኝ በአንጻራዊ በቅርብ ጊዜ የተስፋፋ መንደር ነበር፡፡ የቀድሞ መጠሪያውን (ቁስ መንደር) ያገኘበት ምክንያት የጊዩርጊስ ቤተክርስቲያን አገልጋይ የነበሩት ቀሳውስት የሰፈሩበት፤ ህጻናትና ዳቆናት ፊደልና የሀይማኖት ትምህርት የሚማሩበት

ስለነበር መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ከቤት ክርስቲያኑ በኃላ የሚገኘው አካባቢ ቢለን እየተባለ የሚጠራና የገበሬ የእርሻ መሬት ነበር፡፡ ከ1996 ዓ.ም ወዲህ የከተማውን መስፋት ተከትሎ አካባቢው በደሴ ከተማ አስተዳደር ስር እንዲካተት በመደረጉ ህዝቡን በማህበራት በማደራጀት የእርሻ ቦታዉ እየተሸሸነሸነ ለቤት መስሪያ ተሰጠ፤ በዚህም የተነሳ ብዙ ቤቶች ተሰሩ፡፡ የአዲሱ መንደር ነዋሪዎች በአብዛኛው የእስልምና እምነት ተከታዮች በመሆናቸው ቂስ መንደር የሚለውን ስም ሐያት ሰፈር በሚል አዲስ ስያሜ እንደተኩት መረጃ ሰጭዎች ይገልጻሉ፡፡ (ሸህ ዑመር ሁሴን፣ አቶ ሁሴን አህመድ፣ አቶ ኤልያስ ሙሉጌታ፣ ቃለመጠይቅ፣ ግንቦት 15/2013 ዓ.ም)

ከቀረበው መረጃ መገንዘብ እንደሚቻለው ቂስ መንደር ይባል ለነበረው የቦታ ስያሜ መለወጥ ምክንያት የሆነው አካባቢው በቤተ ክርስቲያኑ ዙሪያ ከተሰሩ ጥቂት የቀሳውስት ቤቶች ባሻገር ሰፊ ቦታ የሸፈነ የከተማ ክፍል መመስረቱ፤ በአካባቢዉ ላይ ሰፊ የመኖሪያ ቤት ግንባታ መስፋፋቱና ሰፋሪዎቹም በአብዛኛው ሙስሊም መሆናቸው ነው፡፡ ይህም ለቦታ ስያሜ መለወጥ በምክንያትነት ከሚጠቀሱት ሁኔታዎች መካከል የነዋሪዎቹ ሃይማኖት አንዱ መሆኑን ያመለክታል፡፡

**ሚካኤል ሰፈር ወደ አቡየ ሰፈር፦**

በዚህ ቦታ ላይ ዘመናት ያስቆጠረ ሚካኤል የሚባል ቤተክርስቲያን ነበር፡፡ ቤተክሪስቲያኑ የሚካኤል እና የአቡየ ታቦታት ተደርበው የሚገኙበት እንደነበር መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ የታቦቶቹ ሥርዓተ ቅዳሴና ክብረ በዓላትም በየእለተ ቀናቸዉ ይከናወን ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ቤተክርስቲያኑም ሆነ አካባቢው ለዘመናት የዘለቀው ሚካኤል የሚለውን ስያሜ ይዞ ነው፡፡ በ1983 ዓ.ም የተከሰተውን የስርዓት ለውጥ ተከትሎ የሚካኤል ታቦት ጀሜ አካባቢ አዲስ ወደ ተሰራ ቤተክርስቲያን ሲዛወር የአቦየ ታቦት እዚያው እንዲቀር ተደረገ፡፡ በዚህም ምክንያት ሚካኤል የሚለው የቤተክርስቲያኑ ስም አቡዬ ሲባል የሰፈሩም ስም አቡዬ በሚለው ሊተካ ቻለ፡፡ (መምሬ ተስፋየ ትርፌ፣ መምሬ ትእዛዙ አያሌዉ፣ አቶ አያሌዉ ይማም፣ አቶ ፈንታሁን ይመር፣ ቡድን ዉይይት፣ መጋቢት 10/214 ዓ.ም)

ከዉይይቱ የተገኘዉ መረጃ እንደሚያሳየዉ ድርብ ታቦቶችን ይዞ የኖረው ቤተክርስቲያንና የአካባቢው መንደር ስያሜውን ያገኘው ከአንደኛው ታቦት ነበር፤ አንደኛው ታቦት (ሚካኤል) ራሱን ችሎ ወደሌላ ሲዛወር ግን የቤተክርስቲያኑም ሆነ የአካባቢው ሰፈር ስያሜ በቦታው ላይ እንዲቀር በተደረገው ታቦት ስም (አቦዬ)

እንዲተካ ተደርጓል። ሚካኤል የሚለዉ ሰፈር አቡዬ ተብሎ ተሰይሟል። ይህ የሆነበት ምክንያት የሚካኤል ታቦት ራሱን ችሎ ቤተክሪስቲያን ተሰርቶለት ወደሌላ አካባቢ መሄዱና የአቡየ ታቦት ቦታው ላይ መቅረቱ መሆኑን መረዳት ተችሏል። ይህም የሀይማኖት ተቋማት መስፋፋት ለአዲስ ስያሜ መፈጠር ብቻ ሳይሆን ለስያሜ ለዉጥም ምክኒያት እንደሚሆን የሚያመላክት ይመስላል።

**አሳማ ሜዳ ወደ ቄራ፡-**

አሳማ ሜዳ እየተባለ የሚጠራዉ ሰፈር አሁን ላይ ቄራ ወደሚል ስያሜ ተቀይሯል። ይህ የሆነበት ምክንያት ደግሞ አካባቢዉ ላይ ለከተማዉ የእርድ አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅት (ቄራ) የተቋቋመ በመሆኑ አሁን ላይ አሳማ ሜዳ የሚለዉ ስያሜ ተለዉጦ ቄራ እየተባለ ይጠራል (አቶ ተፈራ መላኩ፣ አቶ አስፋዉ ተሰማ፣ አቶ ሙህዲን አሰን…የቡድን ዉይይት፣ መጋቢት 25/2014 ዓ.ም)

አሳማ ሜዳ ወይም የአሁኑ ቄራ ተብሎ የሚጠራዉ ሰፈር በከተማይቱ መሀል ቦታ ላይ ወይም አዉቶብስ ተራ ወረድ ብሎ የሚገኝ ሰፈር ነዉ። መረጃ ሰጭዎች እንዳሉት የስያሜዉ ለዉጥ ምክኒያት አካባቢዉ ላይ የቄራ (የእርድ አገልግሎት መስጫ ተቋም) መቋቋሙ ነዉ። በፊት ቦታዉ ላይ የነበረዉ የአሳማ ማርቢያ በአሁኑ ሰአት አገልግሎቱን አቁሟል። በዚህም አሳማ ሜዳ የሚለዉ ስያሜ ቀርቶ ቄራ እየተባለ መጠራት እንደጀመረ ከቡድን ዉይይቱ የተገኘዉ መረጃ ያመላክታል። ቄራ ለከተማይቱ ነዋሪዎች ማህበራዊ አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም ነዉ በመሆኑም ስያሜዉ ማህበራዊ ፋይዳ እንዳለዉ አመላካች ነዉ።

**ፈረንጅ አምባ ወደ በር፡-**

ይህ አካባቢ ከድሮዉ ፖሊስ መምሪያ እስከ ሰኞ ገበያ መገንጠያ ድረስ ያለዉን አካባቢ የሚይዝ ሲሆን ከዋናዉ አስፓልት በላይ የአርመኖችና የግሪኮች መኖሪያ ቦታ ነበር።በዚህም የሰፈሩ ስያሜ ፈረንጅ አምባ እየተባለ ይጠራ ነበር። አሁን ደግሞ አካባቢዉ ላይ ወደ ምእራብ ወረዳ መገንጠያ እና ወደ አዲስ አበባ መዉጫ አካፋይ መንገድ ስለነበር በር በማለት ስያሜዉ ተለወጠ። (አቶ እብራሂም ሁሴን፣ አቶ ሁሴን አየለ፣ አቶ ተፈራ መላኩ፣ ቃለ መጠይቅ፣ መስከረም 16/2014 ዓ.ም)

የፈረንጅ አምባ ሰፈር ስያሜ መቀየር ምክኒያት በአካባቢዉ ይኖሩ የነበሩት አርመኖችና ግሪኮች ቦታዉ ላይ ባለመኖራቸዉ ለስያሜዉ ለውጥ መነሻ የሆነ ይመስላል። በተጨማሪ ደግሞ በር የሚለዉን ስያሜ እንዲያገኝ ያደረገዉ አካባቢዉ

ላይ የተለያየ መዉጫ እና መግቢያ መንገድ ያለዉ በመሆኑ በር በማለት አሁን ድረስ መጠሪያዉ ሆኗል፡፡

**ቁራጭ መንደር ወደ አበበች ሰፈር፡-**

ይህ መንደር የሚገኘዉ ጀሜ ተብሎ በሚጠራዉ ሰፈር ለብቻዉ ተገንጥሎ የሚገኝ ነዉ፡፡ መንደሩ ትንሽ ከመሆኑ የተነሳ እና ባሉት ዉስን መኖሪያ ምክንያት ስያሜዉን እንዳገኘ ከቃለ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ያመላክታል፡፡

ቁራጭ መንደር የተባለበት ምክንያት ከሰፈሩ ራቅ ብሎ የሚገኝ ብቸኛ መንደር ስለሆነ ነዉ፡፡ ሰፈሩ ጀሜ ክልል ላይ የሚገኝ ቢሆንም ከሰፈሩ ራቅ ብሎ የሚገኝ እና ትንሽ በመሆኑ የተነሳ ቁራጭ መንደር በማለት ይጠሩታል፡፡ ይህ ስም ግን ነዋሪዉን ያስከፋል፡፡ ቁራጭ መንደር ስትይ የሚሰማሽ የመንደሩ ነዋሪ እኔን ጨምሮ በጣም ይናደዳል፡፡ አሁን ግን ስያሜዉ ወደ አበበች ተቀይሯል፡፡ የዚህ ምክኒያት ደሞ ሰፈሩ ላይ በጣም ብዙ ቤቶች ተሰሩ የነዋሪዉም ቁጥር ጨመረ በዚህ ምክንያት ደመቀች አበበች ተባለች (ወ/ሮ ዙሪያሽ ካሳ፣ ወ/ሮ አሰገደች ገመች፣ አቶ እብራሂም ሁሴን፣ ቃለ መጠይቅ፣ መስከረም 16/2014 ዓ.ም)፡፡

ከቃለ መጠይቁ የተገኘዉ መረጃ እንደሚያሳየዉ ቁራጭ መንደር ወደ አበበች መንደር እንዲቀየር ምክንያት የሆነዉ አካባቢዉ ላይ የመሰረተ ልማት መስፋፋት፣ የመኖሪያ ቤቶች ግንባታ እና የነዋሪዉ ቁጥር መጨመር ለስያሜዉ መነሻ ምክንያት የሆነ ይመስላል፡፡ የመንደሩ ነዋሪ ቁራጭ መንደር የሚለዉን ስያሜ ያልተቀበለዉ መሆኑ ሌላዉ ለስያሜዉ መቀየር መነሻ የሆነ ይመስላል፡፡ መንደሩ ላይ ብዙ ቤቶች መሰራታቸዉና የሰዉ ብዛት በፊት የነበረዉን ገፅታ ቀይሮታል በመሆኑም የመንደሩ ነዋሪ መንደራችን ደመቀች/አበበች በማለት ደስታዉን የገለፀበት ከዛም አልፎ ለመንደሩ መጠሪያ የሆነበት አጋጣሚ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል፡፡

## 5.3. በቦታ ስሞች ዙሪያ የማኅበረሰቡን አመለካከት የሚያሳዩ መረጃዎች ትንተና

### 5.3.1. በቦታ ስሞች ተከታታይነት ላይ የማህበረሰቡ አመለካከት

#### 5.3.1.1. አዎንታዊ አመለካከት

ስሞች የሚሰዩትም ሆነ የሚለወጡት የማህበረሰቡን ታሪካዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ባህላዊ አጋጣሚዎችን መሰረት አድርገው ነው፡፡ ከተጠቀሱት ሁኔታዎች በአንዱ ወይም በተወሰኑት ምክንያትነት የሚሰየሙት ስሞች በሁኔታዎቹ መለወጥ

ምክንያት ሊለወጡ ወይም በዘላቂነት አገልግሎታቸው ሊቀጥል ይችላል፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው ለስሞች ለውጥም ሆነ ተከታታየነት ምክንያቶቹ የስሞቹ ትርጉም ከታላሚው ማህበረሰብ ማህበረ ባህላዊ ዕሴቶችና ርዕዮተ ዓለማዊ ማንነት ጋር መስማማት/ መቃረናቸው ሊሆን መቻሉን ነው፡፡

የስሞች አገልግሎት ላይ መዘውተር፣ ከትውልድ መሻገር፣ ተከታታይነት ከተጠቃሚው ማህበራዊ ቡድን አዎንታዊ አመለካከት ጋር በእጅጉ ይቆራኛል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ አገልግሎት ላይ መዋል ከጀመሩበት ጊዜ እስካሁን ያልተለወጡ ስሞችን በሚመለከት የተጠቃሚው አመለካከት ምን እንደሆነ ለተጠየቁት ጥያቄ ከመረጃ ሰጭዎች የተገኘው ምላሽ የሚከተለውነው፡፡

ከተማው ከተቆረቆረ ጀምሮ ብዙዎቹ የመንደርና የአካባቢ ስሞች አልተለወጡም፣ ህዝቡም እንዲለወጡ የሚፈልግ አይመስለንም፣ ለምን ቢባል የጎዱት ነገር የለማ! ጉዳት የሌለው ነገር ለምን ይለወጣል፤ እንደቅርስ መታየት አለበትኮ! በእኛ በኩል ህዝቡ ይለወጥልኝ የሚል ጥያቄም ሃሳብም የለውም፤ ስለዚህ አመለካከቱ በአዎንታ የሚታይ ነው፡፡ ነገር ግን አንዳንድ ስድብና አካባቢን የሚያሳንሱ ስሞች ቢለወጡ ህዝብ አይጠላም (አቶ ሰይድ የሱፍ፣ አቶ ሁሴን አየለ፣ አቶ ተፈራ መላኩ፣ ቃለ መጠይቅ፣ መስከረም 16/2014 ዓ.ም) ፡፡

ከቀረበው መረጃ እንደምንረዳው ሰዎች የለመዱትና ለዘመናት ሲጠቀሙበት የኖሩት ስያሜ እንደተጠበቀ እንዲቀጥል ይፈልጋሉ፤ ለዚህም ምክንያታቸውን ተከታታይነትን ጠብቆ መቀጠሉ የሚያስከትለው ጉዳት የለም፤ እንዲያውም መለወጡ ታሪክንና ቅርስን እንደማጥፋት ይቆጠራል በማለት ይገልጣሉ፡፡ እርግጠም ነባር ስያሜዎች ሲቀይሩ እግረ መነንገዱን የተሰየሙበት የተለያየ አጋጣሚ፣ ታሪካዊና ባህላዊ አሻራ ከቅየራው ጋር ተያይዞ የመጥፋት እና የመረሳት አደጋ ሊደርስበት ይችላል፤ ነባር ስያሜያቸውን እንደያዙ መቀጠላቸው በርካታ ታሪካዊ፣ ባህላዊና ርዕዮተ ዓለማዊ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

በዚህ ጉዳይ ላይ ማንኛውም ማህበረሰብ በለመደው የቦታ ስም ተከታታይነት ወይም ዘላቂነት ላይ አመለካከቱን ቢጠየቅ ‹‹ካለመዱት መልዓክ የለመዱት ሰይጣን›› በሚለው ብሂሉ አዎንታዊ ምላሽ ሊሰጥ እንደሚችል ይገመታል፡፡ ይህ ማለት ግን ማህበረሰቡ ለውጥን ይቃወማል ማለት አይደለም፤ ስነልቡናውን፣ ስሜቱንና

ማንነቱን የሚጎዱ ሆነው ሲያገኛቸው በአመለካከቱ ብቻ ሳይሆን በአካልም ሊታገላቸውና ሊያስወግዳቸው፣ በሚሻለው ሊተካቸው ይችላል፡፡

#### 5.3.1.2. አሉታዊ አመለካከት

በስሞች ቀጣይነትን ተከታታይነት ላይ የተጠቃሚው አመለካከት አሉታዊ የሚሆንባቸው በርካታ ምክንያቶች ሊኖሩ ይችላሉ፤ የስሞቹ ትርጉም ወይም አንድምታ ከማንነት አንጻር የአንድን ቡድን ዝቅተኛነት (አናሳነት) የሚገልጽ፣ ጉድለትን በማሳየት ስነልቡናዊ ጫና የሚፈጥር፣ ወዘተ ከሆነ በውክልናው መቀጠሉን የሚፈልግ አይኖርም፤ ለውጥን ይሻል፤ መለወጥ በማይችልበት ስርዓት ውስጥ ከሆነም ተቃውሞውን ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ይገልጻል፡፡

በዚህ ጉዳይ ላይ የደሴ ከተማን የቦታ ስሞች በሚመለከት ማህበረሰቡ አሉታዊ አመለካከት እንዳለውና ካለው ምክንያቱ ምን እንደሆነ ተጠይቀው መረጃ ሰጭዎች የሰጡት ምላሽ እንደሚከተለው ተጨምቆ ቀርባል፡፡

የአንዳንድ ሰፈሮች ስሞች በአጠቃላዩ ህዝብ ሳይሆን በዚያ አካባቢ ነዋሪዎች ላይ ስነልቡናዊ ተጽእኖ ያሳድራሉ፤ በእነዚህ ስሞች አገልግሎት ቀጣይነት ላይ የሚኖረው አመለካከት አሉታዊ ነው፡፡ ለምሳሌ በንጉሱ አገዛዝ ለባላበቶች አገልጋይ ሆነው ከደቡብ የመጡ ሰዎች የሚኖሩበት አከባቢ ‹‹ወላሞ ሰፈር‹‹፣ የከተማው ቆሻሻ ፍሳሽ የሚወርድበት አካባቢ ‹‹ግም ውሃ‹‹ ወዘተ በሚሉ ስያሜዎች መጠራታቸው የነዋሪዎቹን ስሜት የሚጎዳ ስለሆነ አመለካከታቸው አዎንታዊ ይሆናል ተብሎ አይታሰብም (አቶ አያሌዉ ይማም፣ ወ/ሮ ዙሪያሽ ካሳ፣ አቶ ፈንታሁን ይመር፣ ሽህ ሰይድ የሱፍ...የቡድን ዉይይት፣ መጋቢት 10/2014 ዓም) ፡፡

እነዚህ በመረጃ ሰጪወቹ የተጠቀሱት ስሞች፤ የመጀመሪያው በርዕዮተ ዓለማዊ ለውጥ (በደርግ)፣ ሁለተኛው በታሪክ ሂደት ተለውጠዋል፤ ማህበረሰቡ አመለካከቱን የሚገልጽበት፣ በስሞቹ ቀጣይነት ላይ ተቃውሞውን የሚያሰማበት ዕድል ባለማግኘቱ የተቀበለ መስሎ ኖሮ ቢሆን እንጂ አመለካከቱ አዎንታዊ ነበር ማለት የሚቻል አይመስልም፡፡ ስያሜዎቹ የቡድኑን ስነልቡና እና ማንነት የማይገልጹ እና እንዲሁም ትርጉማቸውም በአካባቢው በሚኖረው ማህበረሰብ ቅቡል የማይሆኑ በመሆናቸው መቀየራቸው ተገቢ ነበር ሲሉ የመረጃ ምንጮች ገልጸዋል፡፡ እነዚህ ስያሜዎች አንድምታቸው ጸያፍ ከመሆኑም ባሻገር የስያሜያቸው መነሻ ለማህበረሰቡ አስፈላጊነት የሌለው ስለሆነ በነበሩበት መቀጠል የለባቸውም፡፡ አካባው መጠራት ያለበት ማህበረሰቡን ሊወክል በሚችልና ማህበረሰቡ በሚቀበለው ስም እንጂ

የነዋሪውን ክብር ዝቅ በሚያደርግና እንዲሁም ሌሎች በሰየሙለት ለዚያውም ክብሩን፣ ባህሉንና እሴቱን  በማይጠብቅ ስያሜ መስማማትና ያንን ማስቀጠል የለበትም ብቻ ሳይሆን እንዲህ አይነት ስያሜዎች ታስቦባቸው በእቅድ ጭምር መቀየር የሚገባቸው ናቸው፡፡ በዚህም ከቦታዎቹ ስያሜ ትርጉምና የስያሜ መነሻ አጋጣሚ የተነሳ በዛው መቀጠላቸውን ሰዎች የማይቀበሉት መሆናቸውን እንረዳለን፡፡

### 5.3.2. በቦታ ስሞች ለውጥ ላይ የማህበረሰቡ አመለካከት

#### 5.3.2.1. አዎንታዊ አመለካከት

**ግም ውሃ፡-**

በዚህ ስም የሚጠራው አካባቢ የከተማው ፍሳሽ ቆሻሻ የሚወገድበት የከተማው ደቡባዊ ክፍል ነው፡፡ ከየአቅጣጫው በቱቦ የሚመጣው ፍሳሽ ቐሻሻ አካባቢው ላይ ሲደርስ እይታን በማይከለክል ሁኔታ በመንደሩ መሃል ሲወርድ በግልጽ ይታያል፡፡ ቦታው ለሚኖር ቀርቶ አልፎ ለሚሄድም የሚቀፍ ነው፡፡ የመልክን ጥፉ በስም ይደግፉ የሚለውን ብሂላችን እዚህ ላይ ሊተገበር ይገባው ነበር፤ ስሙን የተሸለ በማድረግ መጽናናት ይቻል ከሆነ፡፡ ስሙም ግብሩም አንድ በመሆኑ የነዋሪው አመለካከት አሉታዊ መሆኑ ቀደምሲል ተገልጻል፤ የስያሜው መለወጥ ያስከተለውን የአመለካከት ለውጥ ለማወቅ ጥያቄ ከቀረበላቸው መረጃ ሰጪዎች የተገኘው መረጃ የሚከተለው ነው፡፡

ስያሜዉን በአዎንታ የተቀበሉ ወይም እንዲቀየር የማይፈልጉ የሰፈሩ ነዋሪዎች ይኖራሉ ብሎ ማሰብ ይከብዳል፡፡ እየኖሩበትም ስያሜዉን እንዳልወደዱት እና በመቀየሩም ደስተኛ እንደሆኑ ከምናውቃቸው ነዋሪዎች ተገንዝበናል፤ ይህም በስም ለውጡ ላይ የሁሉም አመለካከት አዎንታዊ እንደሚሆን እንገምታለን፡፡ ግን ለሁሉም ጉዳይ ደንታ ቢሶች፣ ምንም የማይመስላቸው የሉም ማለት አይደለም (አቶ ተፈራ መላኩ፣ አቶ ሁሴን አየለ፣ ሸህ ሰይድ የሱፍ፣ ቃለ መጠይቅ፣ መስከረም 16/2014 ዓ.ም) ፡፡

**ቁራጭ መንደር፡-**

ጀሜ በሚባለው አካባቢ ከዋናው መንደር ፈንጠር ብሎ የሚገኝና በጣት የሚቆጠሩ ሰዎች ከሰፊው ማህበራዊ ቡድን ተነጥለው የሚኖሩበት ሰፈር ነው፡፡ በዚህ ምክንያት ነዋሪዎቹ ባይቀበሉትም ሌላው ማህበረሰብ ለቦታው ቁራጭ መንደር የሚል ስያሜ ሰጥቶታል፡፡ በዚህ ስያሜ ደስተኛ ያልሆኑት ነዋሪዎች በበኩላቸው በሌላው

ማህበረሰብ ዘንድ ባይለመድም ለአካባቢያቸው ‹‹አበበች›› የሚል ስያሜ እንደሰጡት በቅርብ ርቀት የሚኖሩት መረጃ አቀባዮች ተናግረዋል (አቶ ፈንታሁን ይመር፣ አቶ እብራሂም ሁሴን፣ አቶ ሰይድ የሱፍ፣ ወ/ሮ ዙሪያሽ ካሳ፣ ወ/ሮ አሰገደች ገመች ቃለመጠይቅ፣ መስከረም 16/2014 ዓ.ም)፡፡

መረጃው እንደሚያመለክተው የሰፈሩ ነዋሪዎች ለነባሩ ስያሜ ያላቸው አመለካከት አሉታዊ ነው፤ አሉታዊ አመለካከታቸውን ለመቀየር የማንንም ውሳኔ መጠበቅ ሳያስፈልጋቸው የመንደራቸውን ስም በመረጡት መተኪያ መወከላቸውንና አወንታዊ አመለካከት ማዳበራቸውን ከመረጃው እንረዳለን፡፡ የሰፈራቸውን የመድመቅ፣ የማደግ ተስፋ በሚገልጽ አዲስ ስም (አበበች) ከመተካት የበለጠ ለራስ ምን አዎንታዊ ስሜት ይኖራል፡፡

**ወላሞ ሰፈር፡-**

ይህ ሰፈር ከወላይታ የመጡ ሰዎች ቦታዉ ላይ ከሰፈሩ በኋላ የተሰጠ ስያሜ ነዉ፡፡ አሁን ላይ ስያሜዉ ወደ መንበረ ፀሀይ ተቀይሯል፡፡ በስያሜዉ ለዉጥም የማህበረሰቡ አመለካከት ይህን ይመስላል፡፡

በጊዜዉ ስያሜዉ መቀየሩ ለአካባቢዉ ነዋሪ ደስታን ፈጥሮለታል፡፡ ቦታዉ ላይ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ይኖሩበታል፡፡ በዛን ሰአት ወላሞ የሚለዉን መጠሪያ እንደ ስድብ ይቆጠር ስለነበር ነዋሪዉን ያሸማቅቅ ነበር፡፡ የስያሜዉ ለዉጥ ግን ምን ያህል ደስታ እንደፈጠረ የአካባቢዉ ነዋሪ ብቻ ነዉ የሚያዉቀዉ፡፡ የአሁኑ ስያሜ መንበረ ፀሀይ የፀሀይ መዉጫ ማለት ነዉ፣ የማህበረሰቡን አመለካከት የቀየረ፣ የታላሚውን ቡድን የማንነት ስነልቡናዊ ስብራት የጠገነ በመሆኑ የማህበራዊ ቡድኑ አመለካከት አዎንታዊ እንደሚሆን እናስባለን (አቶ ተፈራ መላኩ፣ አቶ እብራሂም ሁሴን፣ አቶ ፈንታሁን ይመር፣ አቶ አያሌዉ ይማም፣ ቃለ መጠይቅ፣ መስከረም 16/2014 ዓ.ም)

በዚህ መረጃ መሰረት የወላኢታ ማህበረሰብ ስያሜውን የማንነቱ መገለጫ ሳይሆን በሌሎች የተጫነበት የበታችነት መገለጫና ስድብ አድርጎ ስለሚገነዘበው ስሜቱን እንደጎዳው፣ አመለካከቱን አሉታዊ እንዳደረገው መገንዝብ ይቻላል፡፡ ሌላው የማህበረሰብ ክፍልም በዚህ ስያሜ በሚጠራው አካባቢ መኖሩ የሚያስደስተው አይሆንም፤ በዚህ ምክንያትም በስያሜው መለወጥ ላይ ታላሚው ቡድንም ሆነ አጠቃላይ ነዋሪው የሚኖረው አመለካከት አዎንታዊ መሆኑ የሚያጠራጥር አይመስልም፡፡

ከደርግ ስርአት ከመጣ በኋላ ግን ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች እንዲሁም የደርግ ባለስልጣናት ቦታዉ ላይ መኖር በመጀመራቸዉ ምክንያት ስያሜዉ እንዲቀየር ግፊት በማድረግ ወላሞ ሰፈር የሚለዉ ወደ መንበረ ፀሀይ እንዲቀየር ምክንያት ሆነ፡፡ መንግስት የብሄር ብሄረሰብን እኩልነት ከማወጁ በፊት ወላሞ የሚለዉ መጠሪያ በዘመኑ እንደ ስድብ በመቆጠሩ ምክንያት ስያሜዉ የአካባቢዉን ነዋሪ ያሸማቅቅ እንደነበር ከመረጃዉ ለማወቅ ተችሏል፡፡ የስያሜዉ ለዉጥም ማህበረሰቡን አስደስቷል፡፡በመሆኑም ማህበረሰቡ ለስያሜዉ ለዉጥ አወንታዊ አመለካከት እንዳለዉ መገንዘብ ይቻላል፡፡

### 5.3.2.2. አሉታዊ አመለካከት

የቦታዎችን ስያሜ ለውጥ በተመለከተ በማህበረሰቡ ዘንድ አንድ አይነት አመለካከት እንዲኖር አይጠበቅም፡፡ በዚህ የተነሳም አንዳንድ መረጃ ሰጪዎች የቦታዎች ስያሜ በየጊዜው እና አሳማኝ ባልሆነ ምክንያት ጭምር የሚቀየር ከሆነ አንድን አካባቢ በአንድ በታወቀ ስም ለማስተዋወቅ አስቸጋሪ እንዲሆን ከማድረጉም በላይ አካባቢውን በአንድ ስያሜ ያውቁት የነበሩ የቅርብም ሆኑ የሩቅ ሰዎች ከሆነ ጊዜ በኋላ ወደ አካባቢው ሲመጡ መደነጋገር እንዲፈጠርባቸው ስለሚያደርግ፣ እንዲሁም ቦታዎቹ ስያሜያቸውን ያገኙበት ታሪካዊ፣ ፖለቲካዊና መንፈሳዊ አጋጣሚዎች አብረው ሊጠፉ ስለሚችሉ በየምክንያቱ የቦታዎችን ስም መቀየሩ አስፈላጊ አለመሆኑን በአስተያየት ገልጸዋል (አቶ ፈንታሁን ይመር፣ አቶ አያሌዉ ይማም፣ አቶ ሰይድ የሱፍ፣ ቃለመጠይቅ፣ መስከረም 16/2014 ዓ.ም)፡

የእነዚህ መረጃ አቀባዮች አስተያት የተጠየቁትን ጭብጥ ባለማስተዋል በአጠቃላይ በቦታ ስም ለውጥ ላይ አመለካከታቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ በተለይ ለውጥ በተካሄደባቸው ስሞች ላይ የማህበረሰቡ አመለካከት ምን ሊሆን እንደሚችል የሰጡት ምላሽ ባለመሆኑ ትንታኔ አልቀረበበትም፡፡

ሌሎች መረጃ ሰጪዎች በነዋሪዉ ዘንድ ተቀባይነት የሌላቸው፣ የማንነትና የስነ ልቦና ተጽእኖ የሚያሳድሩ ስሞች ለውጥ አወንታዊ አመለካከትን እነደሚያኅለብት፣ ችግሩ እየተለየ በቀጣይነት ለውጥ ሊደረግ እንደሚገባ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል (አቶ ተፈራ መላኩ፣ አቶ አስፋዉ ተሰማ፣ አቶ ሙህዲን አሰን...የቡድን ዉይይት፣ መጋቢት 25/2014 ዓ.ም) ፡፡

# ምዕራፍ ስድስት፡-ማጠቃለያ እና የይሁንታ ሀሳብ

በዚህ ምዕራፍ የማጠቃለያ ሀሳቦች እና የይሁንታ ሀሳቦች በዝርዝር ቀርበዉበታል፡፡

## 6.1. ማጠቃለያ

ይህ ጥናት ዋና አላማ አድርጎ የተነሳዉ በደሴ ከተማ የሚገኙ የቦታ ስሞች ተከታታይነትና ለውጥ መመርመር ሲሆን፣ ተከታታይነትን ጠብቀዉ የቆዩ የቦታ ስሞችን መግለፅ፣ የቦታ ስሞች ለዉጥ እና የለውጥ ምክንያቶችን መግለፅ፣ የቦታ ስሞች ታሪካዊ፣ ትዕምርታዊ፣ ስነልሳናዊ፣ ማህበራዊ፣ እና ፖለቲካዊ ፋይዳ መግለፅ እና የቦታ ስሞች ተከታታይነትና ለውጥ ላይ የማህበረሰቡን አመለካከት መግለፅ የሚሉ ንኡሳን አላማዎችን ያካተተ ጥናት ነዉ፡፡ ደሴ ከተማ ደቡብ ወሎ ዉስጥ ካሉት ዋና ከተሞች አንዱ ነዉ፡፡ ይህ ከተማ በአምስት ክፍለ ከተማ በአስራ ስምንት የከተማ ቀበሌ እና በ ስምንት የገጠር ቀበሌ የተዋቀረ ሲሆን ለዚህ ጥናት ከገጠር ቀበሌዎች ዉጭ ሁለም የከተማ ቀበሌዎች በጥናቱ ተካተዋል፡፡

ይህን ጥናት ለማካሄድ መረጃዎች ከቀዳማይና ከካልዓይ የመረጃ ምንጮች የተሰበሰቡ ሲሆን በቀዳማይ የመረጃ ምንጮች በቃለ መጠይቅ፣ በምልከታ፣ እና በቡድን ተኮር ዉይይት መረጃዎች የተሰበሰቡ ሲሆን በካልዓይ የመረጃ ምንጭ ደግሞ በሰነድ ፍተሻ አማካኝነት መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ ለመረጃ አቀባይነት የተሳተፉ ሰዎች የተመረጡት ጠቋሚ የናሙና አመራረጥ ዘዴን በመጠቀም ሲሆን በዚህም አስራ ስምንት ወንድ እና ሶስት ሴቶች በድምሩ ሀያ አንድ ሰዎች ተመርጠዉ በጥናቱ ተሳትፈዋል፡፡ ለጥናቱ የተመረጡት ሰዎች በአካባቢዉ ላይ ለጅም ጊዜ የኖሩ እና ታሪክ የሚያዉቁ ናቸዉ፡፡ ከቃለ መጠይቅ የተገኘዉን መረጃ በሰነድ ፍተሻ እና በቡድን ተኮር ዉይይት የማጣራት ስራ ተሰርቷል፡፡ ቡድን ተኮር ዉይይቱም ሰባት አባላት ያሉት ሁለት ቡድን በማዋቀር ሁለት ጊዜ ዉይይት አድርጓል፡፡

በመረጃ ትንተናዉ ተከታታይነትን ጠብቀዉ የሚገኙ የቦታ ስሞች፣ የቦታ ስያሜ ለውጥና የለውጥ ምክንያቶች፣ የቦታ ስያሜ ፋይዳ፣ የቦታ ስሞች ተከታታይነትና ለውጥ ላይ የማህበረሰቡ አመለካከት ምን ይመስላል የሚሉ ዝርዝር ጉዳዮች ተዳሰዋል፡፡

**የጥናቱ ግኝቶች**

- በጥናቱ የተፈተሸት በደሴ ከተማ ስር የሚገኙ የቦታ ስሞች መልክአምድርን፣ ተፈጥሮን፣ አፈታሪክንና መሰል ጉዳዮችን በመቅዳት ወይም ምክንያት በማድረግ የተሰየሙ ሆነው ተገኝተዋል፤ ከእነዚህ ስያሜዎች መካከል አበዛኞቹ ለለውጥ ሳይጋለጡ ተከታታይነትን ጠብቀዉ የተገኙ ናቸው። ለዚህም ምክንያት ሆነው የተገኙት የግለሰብንም ሆነ የቡድንን ማንነት፣ ስነልቡናና ማህበረ ባህላዊ ዕሴት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚያሳድሩ አለመሆናቸው መሆኑን ከመረጃዎች ትንተና ማረጋገጥ ተችሏል።
- በጥናቱ ከተካተቱት የቦታ ስያሜዎች መካከል በተወሰኑት ላይ ለውጥ እንደተካሄደባቸው ከተሰበሰቡት መረጃዎች መለየት ተችሏል፤ ለውጥ የተካሄደባቸው ስሞች በሌላእንዲተኩ በምክንያትነት የተለዩት በማህበራዊ ቡድኖች ማንነት፣ ስነልቦናና ስሜት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ማሳደራቸው እንደሆኑ መገንዘብ ተችሏል። በምትካቸው የተወከሉት ስያሜዎችም አካባቢዊ ሁኔታዎችን በመከረጅ የተወሰዱ ሆነው ተገኝተዋል፤ ለምሳሌ አበበች ሰፈር የመንደሩን የማደግ ተስፋ፣ መንበረ ጸሐይ አካባቢው በጸሐይ መውጫ አቅጣጫ የሚገኝ መሆኑ፣ ሃይማኖታዊ ሁነትን ወዘተ መጥቀስ ይቻላል።
- ማህበረሰቡ የስያሜዎቹን ትርጉምና አንድምታ በማስተዋልም ይሁን በልማድ በተከታታይነታቸው ላይ አሉታዊ ስሜት ያሳደረ አይመስልም፤ ከቀዳሚው ትውልድ የተቀበለውን በነበረበት ሁኔታ የማስቀጠል ልምዱን የመለወጥ ፍላጎት አያሳይም። ይሁን እንጂ ከማንነትና ስሜታዊ ሁኔታዎች ጋርግንኙነት ባላቸው ስሞች በተለይ የአካባቢው ነዋሪ አመለካከት አሉታዊ መሆኑን መረጃዎች አመላክተዋል።
- በጥናት አካባቢዉ የተጠቀሱት የቦታ ስሞች አሰያየም የማህበረሰብን መስተጋብር፣ ታሪካዊ ሁነት፣ ስነልሳናዊ ፋይዳ አጉልቶ የሚያሳይ ሆኖ ተገኝቷል። ለምሳሌ በቦታ ስሞቹ ውስጥ የተካተቱት የኦሮምኛ ቃላት የሁለቱ ብሄሮች ማህበራዊ ትስስር ወይም መስተጋብር ዘመናትን ያስቆጠረ መሆኑን፣ በሁለቱ ቋንቋዎች መካከል የተፈጠረው ንክኪና ውሰት የአማርኛ ቋንቋ የቃላት መድብል እንዲያድግ ማድረጉን፣ በአጠቃላይ ማህበራዊ፣ ስነልሳናዊና ታሪካዊ ፋይዳው ጉልህ መሆኑን የሚያሳይ ሆኖ ታይቷል።

## 6.2. የይሁንታ ሀሳቦች

የፎክሎር አንዱ ባህሪ ተለዋዋጭነት ነዉ፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ነባሮቹ ፎክሎሮች እንዳይጠፉ በመሰነድ ከትዉልድ ወደ ትዉልድ ማስተላለፍ ተገቢ ነዉ፡፡ የቦታ ስሞች በተለያዩ ምክንያቶች እየተለወጡ ወይም ደብዛቸዉ እየጠፋ ይሄዳል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የማህበረሰቡ ታሪክ ፣ ባህል አብሮ ይጠፋል፡፡ በመሆኑም የቦታ ስያሜ መነሻ ምክኒያቶች፣ የቦታ ስያሜ ለውጥ እና የለውጥ ምክንያቶቻቸዉ በደንብ ተጠንተዉ ቢቀመጡ ለብዙ ጥያቄዎች መልስ መሆን እንደሚችሉ አያጠራጥርም፡፡

ይህ ጥናት በተደረገበት አካባቢ አብዛኛዎቹ ስሞች ተከታታይነታቸዉን ጠብቀዉ የቆዩ ቢሆንም የተወሰኑት ደግሞ የስያሜ ለውጥ አድርገዋል፡፡ ይህ ደግሞ የቦታ ስሞች እየተለወጡ በሄዱ ቁጥር ተሰንደዉ ካልተቀመጡ ሙሉ በሙሉ ታሪካቸዉ ሊጠፋ ይችላል፡፡ በደሴ ከተማ እና አካባቢዋ ካሉት በርካታ የቦታ ስሞች ዉስጥ በዚህ ጥናት የተካተቱት ጥቂቶቹ ብቻ ናቸዉ፡፡ ስለዚህ ቀሪዎቹ የቦታ ስሞች ጥናት ቢደረግባቸዉና ተሰንደዉ ከትዉልድ ትዉልድ እንዲሸጋገሩ ቢደረግ መልካም ነዉ፡፡

በዚህ ጥናት ዉስጥ ትኩረት ያልተሰጠበት የቦታ ስሞችን ከማንነት አኳያ መፈተሽ ራሱን ችሎ ሊጠና የሚችል መሆኑንና ሰፊ ርእሰ ጉዳይ መሆኑን አጥኝዋ መረዳት ችላለች ስለዚህ ቀጣይ ጥናቶች በርእሰ ጉዳዩ ላይ ጥልቅ ጥናት ሊያካሂዱበት እንደሚገባ ማስታወስ አስፈላጊ ሆኗል፡፡

# ዋቢ ፅሁፎች


መፅሀፍ ቅዱስ። (1998) ።ብሉይ ኪዳን ምእራፍ አንድ፣ ኦሪት ዘፍጥረት 2፡18፣20። አዲስ አበባ፣ ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት።

ሙሉ አየለ። (2011 ዓ.ም) ። "የቦታ ስያሜዎችና የማህበረሰቡ ማንነት ትስስር በሁለት እጁ እነሴ ወረዳ"። ለሁለተኛ ዲግሪ ከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት፣ ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ።

ምስጋናዉ ታደሰ። (2013 ዓ.ም) ። ሚካኤል ንጉስ ወሎ ወትግሬ። አዲስ አበባ፣ ማንኩሳ ማተሚያ ቤት።

ሰሎሞን ተሾመ። (2011 ዓ.ም) ። *ፎክሎር ምንነቱና የጥናቱ የትኩረት አቅጣጫ።* አዲስ አበባ፣ ፋር ኢስት ትሬዲንግ ኃ.የተ.የግ.ማ ።

ሰሎሞን ይርጋ። (2010) ። "በዋልድባ ገዳም ዉስጥ የሚገኙ የቦታ ስያሜዎች አሰጣጥ ይዘታዊ ትንተና"። ለመጀመሪያ ዲግሪ ከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት። ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ።

ሰሚራ ሰይድ። (2008ዓ.ም) ። "የቦታ ስያሜ እና የስያሜያቸዉ መነሻ ምክንያት በአንጋጫ ወረዳ"። ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት። ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ።

ቅዱስ ቁርአን። ሱረቱል በቀራ ምዕራፍ ሁለት አንቀፅ 31-33።

ዘሪሁን አስፋዉ። (2004ዓ.ም) የስነፁሁፍ መሰረታዊያን። አዲስ አበባ። በንግድ ማተሚያ ድርጅት።

አዬ ወርቁ። (2005 ዓ.ም) ።"በጎንጅ ቆለላ ወረዳ የቦታ ስያሜዎች አፈታሪካዊ አመጣጥ ይዘታዊ ትንተና"። ለመጀመሪያ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት። ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ።

አስቴር ሙሉ። (2007ዓ.ም) ። "*ተከታታይነትና ለዉጥ በወሎ አዝማሪዎች የኑሮና የዘፈን ልምድ"* ። ለአማርኛ ቋንቋ ስነ ፁሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።

የደሴ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ፅ/ቤት። (2012 ዓ.ም) ። የደሴ ከተማ አስተዳደር የ2012 ዓ.ም የልማት አመልካቾች መፅሄት። ደሴ። ሻሎም ህትመትና ማስታወቂያ።

ደሴ/ወሎ። (2010ዓ.ም) ። *ሀገር አቀፍ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የንግድ ትርኢትና ባዛር*። ደሴ። ሻሎም ህትመትና ማስታወቂያ።

ደሴ የፍቅር፣የዉበትና የጥበብ አምባ። (2007) ። ለ7ኛዉ የከተሞች ሳምንት የተዘጋጀ *መፅሄት*። ደሴ። ዳና ማተሚያ ቤት።

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል። (1993 ዓ.ም*) ። አማርኛ መዝገበ ቃላት*። አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

ያለው እንዳወቀ። (2009ዓ.ም) ። *የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር*። አዲስ አበባ፣ ተፈራና ስዩም ማተሚያ ቤት።

ያለዉ እንዳወቀ። (1998ዓ.ም) ። *የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር*። አዲስ አበባ፣ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

ጥሩ አለም ስማቸዉ። (2012ዓ.ም) ። "ማንነት በእነብሴ ሳርምድር ወረዳ የቦታ ስያሜ ዉስጥ"።ለሁለተኛ ዲግሪ ከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት። ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ።

ፀጋዉ መኮነን። (2005ዓ.ም) ። የደሴ ከተማ መንደሮች እና አካባቢዎች ስያሜ አወጣጥ ታሪክ። ዳሰሳ ጥናት። ያልታተመ።

Andersson, T.(1994). The existential conditions of place names, place names worthy of caring for papers read at the symposium place name culture organized by the National Heritage Board. Stockholm 5-7 may 1993.Stockholm 1994.

Armada, BJ. (1998). Memorial Agon, An Interpretive Tour of the National Civil Right Museum, the southern communication Journal. 63-3,235-43.

Baker, Ronald L. (1972).The Role of Folk Legends in Place-Name Research.*The Journal of American Folklore,* Vol. 85, No. 338, pp. 367-373.

B. Helleland, C.-E. Ore & S. Wikstrøm (eds.) *Names and Identities*, Oslo Studies in Language 4(2),

Bascom, W.(1954). *Four Functions of Folklore. Journal of American Folklore*. Vol. 67.No. 266.

Danesi, M. (2004). Message Sign and Meanings Abasic Textbook in semiotice and communication (3rd ed), University of Toronto.

Frank proschan.(1997). Semiotics in Thomas A. Green (edr) Folklore. An Encyclopedia of Beliefs, Customs, Tales, Music and Art.

Gerschenkron, Alexander. (1962). "On the Concept of Continuity in History." *Proceedings of the American Philosophical Society* Vol. 106, No. 3 pp. 195—209.

Giddens, A. (1996). Modernity and self-identity, self and society in late Modern age. Kobenhavn, Hans Reitzels forlag.

Goldstein, Kenneth. (1964). *A Guide for Field Workers in Folklore*. American Folklore Society by Folklore Associates, INC.

Guyot and Seethal. (2007). Identity of places of Identites,change of place names in post apartheid south Africa.the south African Geographical Journal.89(1).pp 55-63.

(https://opentextbc.ca/introductiontosociology2ndedition/chapter/chapter-4-society-and-modern-life.

Olsen, M. (1939). Norge [Norway]. In olsen.m.(ed.),stedsnavn.Nordisk kultur 5, 5-52.

Okpewho, I. (1992). *African Oral Literature*. Bloomington: Indianapolis University Press.

Osla volume 4(2), 2012(112).

Posner, Roland. (2004*). Basic Tasks of Cultural Semiotics*. *INST*, p.56-89.

Sims,M.C and Stephens, M. (2005). Liveing folklore, an introduction to the study of people and their Ttridition. United State University press.

Stewart George ,R .(1967). Names on the land .united states of America . Houghton Mifflin Company.

Tilley, C. (1994). A phenomenology Of Landscape, Places, Paths and Monuments. Oxford Providence, Berg, USA.

# አባሪዎች

## አባሪ አንድ፡ ለቁልፍ መረጃ አቀባዮች የቀረበ ጥያቄ

1. ይህ ቦታ ስያሜዉን መቼ እና እንዴት አገኘ?
2. የዚህ ቦታ ስያሜ መነሻ ምክንያት ምንድን ነዉ?
3. ይህ ቦታ ካሁን በፊት ሌላ ስያሜ ነበረዉ ወይ? ካለዉ ምን ይባል ነበር?
4. የተለወጡ የቦታ ስያሜዎች አሉ ወይ ካሉ የለውጡ መነሻ ምክንያት ምንድን ነዉ?
5. ለረጅም ጊዜ ስያሜያቸዉን እንደያዙ የቆዩ የቦታ ስያሜዎች አሉ ወይ ካሉስ ስያሜያቸዉ ያልተቀየረበት ምክንያት ምንድነዉ ?
6. በዚህ ቦታ ላይ የተከናወኑ አስገራሚ ክስተቶች ነበሩ ወይ ካሉ ቢገልፁልኝ?
7. የዚህ ቦታ መጠሪያ የአሁኑ ወይስ የድሮዉ ቢሆን ይመርጣሉ ለምን? በዚህ ላይ የአካባቢዉ ማህበረሰብ ምን አመለካከት አለዉ?
8. የቦታ ስያሜ መለወጥ እና ሳይለወጥ ለረጅም ጊዜ መቆየቱ ምን ጥቅም አለዉ ብለዉ ያስባሉ? ምንስ ጉዳት አለዉ ብለዉ ያስባሉ?
9. የቦታ ስሞች ተከታታይነትና ለውጥ ላይ የማህበረሰቡ አመለካከት ምን ይመስላል?

## አባሪ ሁለት፡ የመረጃ አቀባዮች ስም ዝርዝር

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ፆታ | እድሜ | ስራ | አድራሻ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ተፈራ መላኩ | ወ | 90 | ጡረታ መምህር | ሸዋ በር | |
| 2 | ሸህ ሰይድ የሱፍ | ወ | 75 | የሀይማኖት አባት | ጀሜ | |
| 3 | መምሬ ተስፋየ ትርፌ | ወ | 60 | የቤተክርስቲያን አገልጋይ | አቡየ/ሳላይሽ | |
| 4 | ወ/ሮ ዙሪያሽ ካሳ | ሴ | 80 | የቤት እመቤት | ሳላይሽ/ጀሜ | |
| 5 | አቶ ሁሴን አየለ | ወ | 95 | የሀገር ሽማግሌ | ሳላይሽ/ጀሜ | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 6 | ወ/ሮ ጥሩየ የሱፍ ወራቂ | ሴ | 85 | ጡረተኛ | ሳላይሽ | |
| 7 | አቶ ከበደ ሩፌ | ወ | 75 | ነጋዴ | አገር ግዛት | |
| 8 | አቶ አያሌዉ ይማም | ወ | 56 | ወታደር | ጀሜ | |
| 9 | አቶ ፈንታሁን ይመር | ወ | 68 | ጡረታ መምህር | ሳላይሽ | |
| 10 | አቶ ጋሹ ሀይሌ | ወ | 83 | ጡረታ መምህር | ሼል | |
| 11 | ወ/ሮ አሰገድ ገመች | ሴ | 54 | የቤት እመቤት | ሳላይሽ | |
| 12 | አቶ እብራሂም ሁሴን | ወ | 76 | ጡረታ | ጀሜ | |
| 13 | አቶ ሙህዲን አሰን | ወ | 62 | ወታደር | ሳላይሽ | |
| 14 | አቶ ሊበን አራጋዉ | ወ | 70 | ገበሬ | ሳላይሽ | |
| 15 | አቶ አስፋዉ ተሰማ | ወ | 82 | ጡረታ | ጀሜ | |
| 16 | ሸህ ዑመር ሁሴን | ወ | 69 | ጡረታ | ቢለን | |
| 17 | አቶ ሁሴን አህመድ | ወ | 75 | ገበሬ | ቢለን | |
| 18 | አቶ ኤልያስ ሙሉጌታ | ወ | 35 | የመንግስት ሰራተኛ | ቢለን | |
| 19 | አቶ ሰይድ አበጋዝ | ወ | 70 | ነጋዴ | አራዳ | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 20 | አቶ መሀመድ ይመር | ወ | 69 | ነጋዴ | ሙጋድ | |
| 21 | መምሬ ትእዛዙ አያሌዉ | ወ | 56 | የቤተክሪስቲያን አገልጋይ | አቡየ/ሳላይሽ | |

**በመጀመሪያ ዙር ቡድን ተኮር ዉይይት የተሳተፉ መረጃ አቀባዮች**

| ተ.ቁ | ስም | ጾታ | እድሜ | ስራ | አድራሻ | ምርመር |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | መ/ሬ ትእዛዙ አያሌዉ | ወ | 56 | የቤተ/ያን አገልጋይ | አቦየ/ሳላይሽ | |
| 2 | መ/ሬ ተስፋየ ትርፌ | ወ | 60 | የቤተ/ያን አገልጋይ | አቦየ/ሳላይሽ | |
| 3 | አቶፈንታሁን ይመር | ወ | 68 | ጡረታ መምህር | ሳላይሽ/ጀሜ | |
| 4 | አቶ አያሌዉ ይማም | ወ | 56 | ጡረታ ወታደር | ጀሜ | |
| 5 | ሽህ ሰይድ የሱፍ | ወ | 75 | የሀይማኖት አባት | አራዳ | |
| 6 | ወ/ሮ ዙሪያሽ ካሳ | ሴ | 80 | የቤት እመቤት | ጀሜ | |
| 7 | ወ/ሮጥሩ የሱፍ ወራቂ | ሴ | 85 | ጡረተኛ | ጀሜ | |

**በሁለተኛ ዙር ቡድን ተኮር ዉይይት የተሳተፉ መረጃ አቀባዮች**

| ተ.ቁ | ስም | ጾታ | እድሜ | ስራ | አድራሻ | ምርመር |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ተፈራ መላኩ | ወ | 90 | ጡረታ መምህር | ሽዋ በር | |
| 2 | አቶእብራሂም ሁሴን | ወ | 76 | ጡረታ | ጀሜ | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 3 | አቶ ሊበን አራጋዉ | ወ | 70 | ገበሬ | ሳላይሽ | |
| 4 | ወ/ሮ አሰገደች ገመች | ሴ | 54 | የቤት እመቤት | ሳላይሽ | |
| 5 | አቶ አስፋዉ ተሰማ | ወ | 82 | ጡረታ | ጀሜ | |
| 6 | አቶ ሙህዲን ሀሰን | ወ | 62 | ወታደር | ሳላይሽ | |
| 7 | አቶ ሁሴን አየለ | ወ | 95 | የሀገር ሽማግሌ | ሳላይሽ/ጀሜ | |

**አባሪ ሶስት፡ ተከታታይነታቸዉን ጠብቀዉ የሚገኙ የቦታ ስሞች**

- ሼል
- ሮቢት
- ወሎ ባህል አምባ
- ኮሽምበር
- ቅዳሜ ገበያ
- ተቋም
- ሰፈረ ሰላም
- ነፍሶ ሀገር
- ዳንዲ ቦሩ
- ቢለን
- ፒያሳ
- መገናኛ
- ጢጣ
- ዶልፊን
- ፔፕሲ
- መላኩ

- ቦርከና
- መንገሻ ጎራ
- አዝዋ ገደል
- አየር ጤና
- ቁርቁር
- ቦሩ ስላሴ
- ጢጣ ጥሩሲና
- አምፋሪት
- ቼሬ ሜዳ
- ቆርቆሮ ሰፈር
- በሬ ተራ
- ዶሮ መዝለያ
- አድማ ብተና
- መናህሪያ
- ስላሴ በር
- ኪዳነምህረት
- ባድራ ጊቢ
- አራዳ
- ቧንቧ ዉሃ
- ጎንደር በር
- ተርሚናል
- ዲቭዥን
- ኩሩ

## አባሪ አራት፡ የተለወጡ የቦታ ስሞች

- ነፃነት አደባባይ ወደ መናፈሻ
- ቀለም ሜዳ ወደ ዩኒቨርሲቲ
- ጨርጨሪት ወደ ጮርቃ መንደር
- ፖሊስ መምሪያ ወደ ዶ/ር አረጋ ጎዳና
- ቢለን ጊዮርጊስ ወደ ቢለን
- ሳማ መንደር ወደ እቴጌ መነን
- ሀረርጌ ሰፈር ወደ ሜጠሮ
- እርሻ ሰብል ወደ አዉራ ጎዳና